# ጽኑ መሠረት

ጸሐፊው:- ትሬቨር ምክኢልዌን

ተርጓሚው:- ጌቱ ግዛው

## ክፍል ሁለት

## ሁለተኛ መጽሐፍ

LAPSLEY / BROOKS FOUNDATION, INC.
1701 N. GREENVILLE AVE. ST. 810
RICHARDSON, TEXAS 75081, USA

Copyright © 1996 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia: Originally published in English under the title of BUILDING ON FIRM FOUNDATIONS, Copyright © 1988 by New Tribes Mission, Sanford, U.S.A. All rights reserved.

# ማውጫ


ትምህርት 22፡- እግዚአብሔር ይስሐቅን ሰጠ። ........................ 1

ትምህርት 23፡- እግዚአብሔር ያዕቆብን ሲመርጥ ዔሳውን ግን ሳይመርጥ ቀረ። .................................. 11

ትምህርት 24፡- እግዚአብሔር ዮሴፍን መራው፥ ጠበቀውም። ...... 20

ትምህርት 25፡- እግዚአብሔር ዮሴፍን ከፍ አደረገው እስራኤልንም ወደ ግብፅ ወሰደ። .......................... 24

ትምህርት 26፡- እግዚአብሔር በግብፅ በባርነት የነበሩትን እስራኤላውያንን ጠበቀ። ...................... 29

ትምህርት 27፡- እግዚአብሔር፥ሙሴን ሕዝቡን ነፃ እንዲያወጣ ጠራው። .................................. 35

ትምህርት 28፡- ሙሴና አሮን ፈርዖንን ገጠሙ። ፈርዖን አልታዘዝም አለ። እግዚአብሔር በግብፅ ላይ መቅሠፍት ላከ። ........... 43

ትምህርት 29፡- የሞት መቅሠፍትን ማለፍ........................ 54

ትምህርት 30፡- እግዚአብሔር እስራኤልን በቀይ ባሕር ታደጋቸው። ... 64

ትምህርት 31፡- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን መናና ውኃን ሰጣቸው። 73

ትምህርት 32፡- ለአሥርቱ ሕግጋት መሰጠት የተደረገ ዝግጅት። ..... 79

ትምህርት 33፡- አሥርቱ ትእዛዛት። ............................ 88

ትምህርት 34፡- የማደሪያው ድንኳን። ..........................107

ትምህርት 35፡- እግዚአብሔር የጥጃ ምስል በመሥራታቸው በእስራኤላውያን ላይ ፈረደባቸው። ..................118

ትምህርት 36፡- እስራኤላውያን ባለማመናቸው ምክንያት እግዚአብሔር ወደ ከነዓን እንዳይገቡ አደረገ። .....................124

ትምህርት 37፡- እግዚአብሔር፥ ለእስራኤላውያን ከዓለት ውኃ አፈለቀላቸው። ..........................................131

ትምህርት 38፡- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደ ተስፋዪቱ ምድር ወሰዳቸው። ............................................140

ትምህርት 39፡- እግዚአብሔር፥ በሳኦል ምትክ ዳዊትን መረጠ። እግዚአብሔር የቤተ መቅደሱን ሕንፃ ሥራ እንዲሠራ ሰሎሞንን መረጠ። ......................................149

ትምህርት 40፡- እግዚአብሔር ዮናስንና ሌሎች ሰዎችን መልእክተኞቹ ይሆኑ ዘንድ መረጣቸው። ..............157

ትምህርት 41፡- ስለሚመጣው ነፃ አውጪ እግዚአብሔር የገባቸው የተስፋ ቃሎች። ..........................................166

ትምህርት 42፡- እግዚአብሔር፥ እስራኤልንና ይሁዳን ቀጣ፥ ነገር ግን ቅሬታዎችን ከባቢሎን ታደገ። ..........................174

# ትምህርት 22

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 21፡ 1-3፥ 22፡ 1-19

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር ይስሐቅን ሰጠ።

ይስሐቅ ከሞት ዳነ።

## የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር፥ ለአብርሃምና ለሣራ ልጅ እንደሚሰጣቸው የገባላቸውን ቃል ኪዳን ፈጸመ (21፡ 1-3)።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ለ. እግዚአብሔር፥ አብርሃምን ልጁን ይስሐቅን እንዲሠዋለት ጠየቀው (22፡ 1፥ 2)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ሐ. አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ (22፡ 3-5)።

. ሰው፥ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

መ. ይስሐቅ ጠየቀ፥ አብርሃም መልስ ሰጠ (22፡ 6-8)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ሠ. አብርሃም ይስሐቅን አሰረው (22፡ 9፥ 10)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ረ. እግዚአብሔር በይስሐቅ ፈንታ በግ አዘጋጀ (22፡11-13)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ሰ. አብርሃም፥ እግዚአብሔር ነፃ አውጪ እንደሚልክ በማመን በእግዚአብሔር ተደገፈ (22፡14-19)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

## የትምህርት 21 ጥያቄዎችን ከልስ።

### የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. እግዚአብሔር፥ ለአብርሃምና ለሣራ ልጅ እንደሚሰጣቸው የገባላቸውን ቃል ኪዳን ፈጸመ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

አብርሃምና ሣራ ልጅ ሊወልዱ ከማይችሉበት ዕድሜ ላይ ቢደርሱም እንኳ እግዚአብሔር ወንድ ልጅን እንደሚሰጣቸው ተናገራቸው። በዚህ ጊዜ አብርሃም የ100 ዓመት ሰው ነበር። የሣራ ዕድሜ ደግሞ 90 ዓመት ነበር። ሣራ ልጅ አልወለደችም ነበር። ልጅ እንደምትወልድ እግዚአብሔር በነገራት ጊዜ ሣራ ሳቀች። በእርሷ ዕድሜ ልጅ መውለድ የማይቻል እንደሆነ ታውቅ ነበር።

ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም። እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ያደርጋል።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር፥ ወንድ ልጅን ይሰጠው ዘንድ ለአብርሃም ቃል ከገባለት ብዙ ዓመታት አልፈዋል። ቢሆንም እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ አልዘነጋም፥ አሳቡን አልቀየረም። እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ መሠረት ሣራ ወንድ ልጅ ወለደች። አብርሃምና ሣራ ልጃቸውን ይስሐቅ ብለው ሰየሙት። ዘፍጥረት 21፡ 1-3 አንብብ።

በጊዜ ቅደም ተከተል ማሳያ ሠንጠረዥ ላይ፡- ይስሐቅ፥ ዔሳው፥ ያዕቆብ፥ ዮሴፍ የሚሉትን ስሞች አሳይ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር፥ ለአብርሃምና ለሣራ ልጅ ሊሰጣቸው እንደሚችል የወሰነበት ምክንያት እርሱ የሰዎች ሁሉና የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ለሚገኙ ሰዎች ሕይወትን ሰጥቷል። ለእኛና ለእናንተ ቀደምት አባቶች ሕይወትን የሰጠ እርሱ ነው። ለእናንተና ለልጆቻችሁ ሕይወትን ሰጥቷል፥ ይህች ዓለምና በውስጧ ያሉት ነገሮች ሁሉ የእግዚአብሔር ናቸው።

## ለ. እግዚአብሔር አብርሃምን ይስሐቅን ሠዋልኝ ሲል አዘዘው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ብዙ ዓመታት አለፉ፥ ይስሐቅም ወጣት ሆነ። በአባቱና በእናቱ ዘንድ ተወዳጅ ልጅ ነበር።

እግዚአብሔር ነፃ አውጪ ስለሆነው አዳኝ የሰጠው ተስፋ በሙሉ የሚፈጸመው በይስሐቅና በዝርያዎቹ በኩል እንደሚሆን አብርሃም ያምን ነበር።

አንድ ቀን እግዚአብሔር አብርሃምን ጨርሶ ያልተጠበቀ አስቸጋሪና ከባድ የሆነ ነገር ነገረው። እግዚአብሔር አብርሃምን አንድ ያልተለመደ ነገር እንዲያደርግ ጠየቀው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘፍጥረት 22፡ 1-2 አንብብ። እግዚአብሔር፥ አብርሃምን ሊፈትነው ፈለገ። ፈተናው ከእርሱና ከይስሐቅ የበለጠ የሚወደው ማንን እንደሆነ ለማረጋገጥ ነበር።

እግዚአብሔር፥ አብርሃምን ይስሐቅን ወስዶ እንዲሠዋለት ለማዘዝ ምን ሥልጣን ነበረው?

ከጐረቤትህ አንዱ ወይም ማንኛውም ሰው በሚስትህ፥ በልጆችህ፥ በቤትህ፥ በእርሻ ቦታህ፥ ወይም በንብረትህ ላይ ምን ማድረግ እንዳለብህ ሊነግርህ ይችላልን? አይችልም። ለምን? ምክንያቱም የአንተ ናቸው። ባለቤታቸው አንተ እንጂ ሌላ ሰው አይደለም።

ይስሐቅ ታዲያ የአብርሃም ልጅ አልነበረምን? የአብርሃም ንብረት አልነበረምን? አብርሃም፥ በልጁ በይስሐቅ ላይ ሥልጣን አልነበረውምን? አዎ! ይስሐቅ የአብርሃም ልጅ ነበር። ነገር ግን ለይስሐቅ ሕይወትን የሰጠ ማን ነበር? ለአብርሃምና ለሣራ ይስሐቅን የሰጣቸው ማን ነው? እግዚአብሔር ነበር። ይስሐቅ የእግዚአብሔር ነበር።

ሕይወትን የሰጣችሁ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው። ለሚስቶቻችሁ፥ ለልጆቻችሁና ለእንስሳቱ ሕይወትን የሰጠ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው። በምድር ላይ ያሉ ነገሮችን ሁሉ የፈጠረ ማን ነው? ፀሐይን የፈጠረ፥ ቤታችንን ለመሥራት እንድንችል ዛፎች ይበቅሉ ዘንድ ያደረገ፥ እንድንመገባቸው አትክልትና ፍራፍሬዎች እንዲያድጉ ዝናብን የሚሰጥ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

ለይስሐቅ ሕይወትን የሰጠ እግዚአብሔር ነበር። ለእያንዳንዱ ሰውና ለነገሮች ሁሉ ሕይወትን የሰጠ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ በነገሮች ሁሉና በሰዎች ሁሉ ላይ ሥልጣን አለው።

## ሐ. አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ።

ዋና አሳብ:- ሰው እግዚአብሔርን ደስ እንዲያሰኝና እንዲድን እምነት ያስፈልገዋል።

ለአብርሃም ምን ዓይነት አስደንጋጭና አስገራሚ ነገር ነበር! ምን ዓይነት ከባድ ፈተና ነው። አብርሃም ከይስሐቅና ከእግዚአብሔር የበለጠ የሚወደው ማንን ነበር?

እግዚአብሔር፥ ስለ ይስሐቅና ስለ ተስፋ ቃሎቹ የነበረውን አሳብ ለወጠን? አብርሃም፥ ይስሐቅን ከገደለው የእግዚአብሔር የተስፋ

ቃሎች እንዴት ሊፈጸሙ ነበር? እግዚአብሔር አሳቡን ቀየረን? ነፃ አውጪው የሚመጣው ከይስሐቅ ዘር እንዳይሆን እግዚአብሔር ውሳኔ አደረገን?

አብርሃም ይስሐቅን እንዲሠዋ ቢነገረውም እንኳ እግዚአብሔርን አልተጠራጠረም፤ ደግሞም አንዳችም ነገር አልጠየቀም። እግዚአብሔር እንደማይዋሽ ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር አንድ የተስፋ ቃልን ሰጥቶ አሳቡን ሊለውጥ እንደማይችል ያውቅ ነበር። በእግዚአብሔር በመታመን እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን እንደማይለውጥ አመነ።

መምህር ሆይ፡- የእግዚአብሔርን ታማኝነትና አደራ ጠባቂነት ከሰው ተለዋዋጭነትና ቃል አባይነት ጋር የሚያወዳድር በአካባቢው የሚታወቅ መግለጫ ስጥ።

አብርሃም፥ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ይስሐቅን ቢገድልም እንኳ እግዚአብሔር ይስሐቅን ከሞት ያስነሣው እንደነበር አመነ። ይህ ለሰው የማይቻል ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር ሊያደርገው እንደሚችል ታመነ።

መመህር ሆይ፡- ዕብራውያን 11፡17-19 ተመልከት

አብርሃም አዳምና ሔዋን በዔድን ገነት ከነበራቸው ሁኔታ የተለየ አቋም ይዞ ነበር። በዔድን ገነት እግዚአብሔር ለአዳም እንዲህ ብሎት ነበር። «መልካምንና ክፉን ከማያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና»። ሰይጣን «አትሞቱም» ባላቸው ጊዜ ግን አዳምና ሔዋን ሰይጣንን አመኑ። የእግዚአብሔርን ቃል ስለተጠራጠሩ ሳይታዘዙ ቀሩ። አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን አላመኑም ነበር። አብርሃም ግን እግዚአብሔርን አመነ። እግዚአብሔር ቃሉን እንደሚጠብቅ አመነ።

አብርሃም በእግዚአብሔር ስላመነና በእርሱ ስለተደገፈ እግዚአብሔር ሂድ ወዳለው ስፍራ ለመሄድ ወዲያውኑ ተዘጋጀ ዘፍ. 22፡3-5 አንብብ።

መ. ይስሐቅ ጠየቀ፥ አብርሃምም መልስ ሰጠ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ እንዲያሰኝ እምነት ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 22፡6-8 አንብብ። ይስሐቅ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ለመሠዋት እንደሚሄዱ ያውቅ ነበር። ነገር ግን የሚሠዉትን በግ ለምን እንዳልያዙ አያውቅም ነበር። አብርሃም እግዚአብሔር እንዲያደርገው ያዘዘውን ነገር ለይስሐቅ አልነገረውም ነበር። አብርሃም፥ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር እንደሚያዘጋጅ አምኖ ነበር። ዘፍጥረት 22፡8 አንብብ።

ልናደርጋቸው ከምንችላቸው ነገሮች ሁሉ የላቀው በእግዚአብሔር ማመን ነው። የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ብቻ አይረዳንም። የእግዚአብሔርን ቃል በልባችን በመቀበል በእርሱ መደገፍ አለብን።

አንድ ሰው ቢታመምና መድኃኒት ፍለጋ ወደ እኔ ቢመጣ ስለ መድኃኒቱ ጥቅምና ፈውስን እንዴት እንደሚያመጣ ብናገር ብቻ ይጠቅመዋልን? ስለ መድኃኒቱ መስማት ብቻ ፈውስን ሊያመጣ ይችላልን?

የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ብቻ አይደለም። የእግዚአብሔርን ቃል ብንሰማ ነገር ግን ባናምን ሰይጣን ለሔዋን ያለውን ነገር ማድረጋችን ነው። እግዚአብሔርን ውሸታም ማለታችን ነው። እግዚአብሔር እርሱን ያላመኑትን ሰዎች ሊቀበል አይችልም። እግዚአብሔር የሚቀበለው እንደ አብርሃም እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ በማመን በእርሱ የሚደገፉትን ነው።

## ሠ. አብርሃም ይስሐቅን አሰረው።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

ዘፍጥረት 22፡9፥ 10 አንብብ። ይስሐቅ ሊያመልጥ የሚችልበት ሁኔታ አልነበረም። እጅና እግሩን ታስሮ በመሠውያው ላይ ተጋድሞ ነበር። አብርሃምም ሊያርደው ካራ አነሣበት። አብርሃም ይስሐቅን

እንዲሠዋለት እግዚአብሔር ያዘዘውን ተግባራዊ ሊያደርገው ነው። ይስሐቅ አንድ ጊዜ ከመሠውያው ጋር ታስሯልና ከእንግዲህ የማምለጥ ዕድል አልነበረውም። እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ይስሐቅን እንዲሠዋለት አንዴ አዝዞት ነበር።

እግዚአብሔር የኖኅ መርከብን በር በዘጋ ጊዜ የሆነው እንደዚሁ ነበር። የኖኅ ቤተሰብ እንስሳቱና አእዋፍ በሙሉ በመርከቡ ውስጥ በሚያስተማምን ሕልውና ላይ ነበሩ። እግዚአብሔርን ባለማመናቸው ምክንያት ወደ መርከቡ ሊገቡ ያልቻሉት ሰዎች ግን ምንም ማምለጫ አልነበራቸውም። እግዚአብሔር በሰዶምና ገሞራ ከተማዎች ላይ እሳት በላከ ጊዜ በከተማይቱ ላሉት ሰዎች ከዚህ እሳት የማምለጫ መንገድ አልነበረም። የሎጥ ሚስት እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ወደ ሰዶም ከተማ ዞር ባለች ጊዜ ምንም ማምለጫ አልነበራትም። እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቦቹን ከጥፋት ውኃ አዳነ። እግዚአብሔር ሎጥንና ሴት ልጆቹን ሰዶምና ገሞራን ካጠፋው እሳት አዳነ። ስለዚህ ይስሐቅን ከመታረድ ሊያድን የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነበር።

በኃጢአታችን ምክንያት ሊመጣብን ካለው ሞትና የዘላለም ፍርድ ራሳችንን የምናድንበት መንገድ አለን? በጭራሽ የለም! ራሳችንን ማዳን አንችልም። እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትን ሁሉ ይቀጣል። ከእግዚአብሔር ሊያመልጥ የሚችል ማንም የለም።

እግዚአብሔር ይስሐቅን ሊያድነው ይችላልን? የእግዚአብሔር ቃል ቀጥሎ ምን እንደተፈጸመ ይነግረናል።

## ረ. እግዚአብሔር የይስሐቅን ቦታ የሚታካ በግ አዘጋጀ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ዘፍጥረት 22፡10-12 አንብብ። አዎን እግዚአብሔር ይስሐቅን አዳነ። እግዚአብሔር አብርሃምን ይስሐቅን እንዳያርድ ነገረው።

ይስሐቅ ለመዳን የሚችለው ሌላ ለእግዚአብሔር ሊሠዋ የሚችል መሥዋዕት በምትክነት ከተገኘ ብቻ ነበር። አብርሃም ደግሞ ይስሐቅን የሚተካ መሥዋዕት አልነበረውም። እግዚአብሔር ግን በይስሐቅ ፈንታ

ሌላ መሥዋዕት አዘጋጀለት። አብርሃም መሥዋዕቱን ማቅረብ አይችልም ነበር። እግዚአብሔር በጸጋው በይስሐቅ ፈንታ የመሥዋዕት በግ ሰጠ። ዘፍጥረት 22፡ 13 አንብብ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር አንድ በግ በጫካ ውስጥ በቀንዱ ተጠልፎ እንዲያዝ አደረገ። የተያዘው በሰውነቱ ሌላ ክፍል ቢሆን ኖሮ እራሱን ለማስጣል ሲታገል ይጐዳ ነበር። ቢጐዳ ኖሮ ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት አይሆንም ነበር። እግዚአብሔር በመሥዋዕትነት የሚቀበለው ጤነኛና ጠንካራ የሆነ እንስሳትን ነበር። እግዚአብሔር እርሱ ፍጹም ስለሆነ የሚቀበለው መሥዋዕት ፍጹም ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን ጠበቀ። እግዚአብሔር በይስሐቅ አማካይነት ለአብርሃም ብዙ ዝርያዎችን ሰጥቷል።

አብርሃም ይስሐቅን ከመሠውያው ላይ ፈትቶ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን በግ በምትኩ አሰረው። ይህ በግ በይስሐቅ ምትክ ተሠዋ። አብርሃም በጉን አርዶ ለእግዚአብሔር የሚሆን መሥዋዕት አድርጐ አቃጠለው።

በጉ በይስሐቅ ምትክ ሞተ። በጉ የይስሐቅ ምትክ ነበር። እግዚአብሔር ይስሐቅን አዳነው። እግዚአብሔር በይስሐቅ ፈንታ በጉ እንዲሞት አደረገ።

ሰ. አብርሃም፥ እግዚአብሔር ነፃ አውጪ እንደሚልክ በእግዚአብሔር ታመነ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 22፡14-19 አንብብ። አብርሃም በይስሐቅ ፈንታ የተሠዋውን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጀበትን ቦታ «እግዚአብሔር ያዘጋጃል» ብሎ ጠራው። እግዚአብሔር በይስሐቅ ምትክ የሚሞት በግ አዘጋጀ። በተጨማሪም አብርሃም እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከሰይጣን ኃይልና ከኃጢአት ቅጣት ለማዳን ነፃ አውጪ እንደሚልክ አመነ።

## ጥያቄዎች

1. አብርሃም የ100 ዓመት ሣራ ደግሞ የ90 ዓመት ሰዎች ቢሆኑም እንኳ እግዚአብሔር ልጅን ሊሰጣቸው የቻለው ለምን ነበር?

   ሀ. በሁሉም ስፍራ ለሚገኙ ሰዎች ሕይወት የሚሰጥ እርሱ ስለሆነ ነው።

   ለ. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለሆነና የሚፈልገውን ማናቸውንም ነገሮች ማድረግ ስለሚችል ነው።

2. እግዚአብሔር፥ አብርሃምን ልጁን ይስሐቅን እንዲሠዋለት ሊያዘው የቻለው ለምን ነበር?

   ሀ. እግዚአብሔር የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ስለሆነ ለፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ ባለቤት ስለሆነ ነው።

   ለ. ለይስሐቅ ሕይወትን የሰጠው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

3. አብርሃም የታላቅ ሕዝብ አባት እንደሚሆንና ነፃ አውጪው ከእርሱ ዘር እንደሚመጣ እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን የለወጠ መስሎት ነበር? አልመሰለውም። አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ፥ በእርሱም ተደገፈ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የገባውን የተስፋ ቃል ሊያጥፍ እንደማይችል በእግዚአብሔር ሙሉ እምነት ስለነበረው ነው።

4. አብርሃም እግዚአብሔር ምን ሊያደርግ ይችላል ብሎ አሰበ? አብርሃም በታዘዘው መሠረት ይስሐቅን ቢሠዋውም እንኳ እግዚአብሔር ከሞት ሊያስነሣው እንደሚችል አስቦ ነበር።

5. አብርሃም፥ ይስሐቅን መሠውያ ላይ ካሰረው በኋላ ይስሐቅ ራሱን ከሞት ሊያድን የሚችልበት መንገድ ነበረውን? አልነበረውም። ይስሐቅ ራሱን ከሞት ለማዳን አይችልም ነበር።

6. በኃጢአታችሁ ምክንያት ከሚገባችሁ ደመወዝ ማለትም ከሞትና ከዘላለም ቅጣት ራሳችሁን የምታድኑበት መንገድ አለን? የለም። ማንም ሰው ራሱን ከእግዚአብሔር ቅጣት ማዳን አይችልም። ማንም ከእግዚአብሔር ለማምለጥ አይችልም።

7. ለአብርሃም በመናገር ይስሐቅን ከሞት ያዳነው ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

8. ከእግዚአብሔር በቀር ይስሐቅን ከሞት ሊያድን የሚችል ነበርን? በጭራሽ አልነበረም።

9. የይስሐቅን ስፍራ እንዲወስድ የመሥዋዕት በግ ያዘጋጀ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

10. በጫካው ውስጥ የነበረው በግ በቀንዱ የተያዘው ለምን ነበር? እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ የሚቀበለው ጠንካራና ጤነኛ የሆነ መሥዋዕት ብቻ ስለነበር ነው።

11. እግዚአብሔር በጉን አዘጋጅቶ የሰጠበትን ስፍራ አብርሃም «እግዚአብሔር ያዘጋጃል» በማለት የጠራው ለምን ነበር? አብርሃም እግዚአብሔር ይስሐቅን ለማዳን በግ እንዳዘጋጀ አንድ ቀን የሰው ልጆችን ከሰይጣን ኃይልና ከዘላለም ቅጣት የሚያድን ነፃ አውጪ እንደሚልክ በማመኑ ነው።

# ትምህርት 23

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 24፡67፤ 25፡20-34፤ 27፡41-44፤ 28፡10-15፤ 29፡1፤ 31፡13፤ 32፡28

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር ያዕቆብን ሲመርጥ ዔሳውን ግን ሳይመርጥ ቀረ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. ይስሐቅ ርብቃን አገባ (25፡20)።

ለ. እግዚአብሔር፥ ስለ ያዕቆብና ስለ ዔሳው ሁሉን ነገር ከመወለዳቸው በፊት ያውቅ ነበር። (25፡21-23)

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ሐ. ዔሳውና ያዕቆብ ተወለዱ (25፡24-26)።

መ. ዔሳው የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች አላመነም ወይም ዋጋ አልሰጣቸውም (25፡27)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሠ. ያዕቆብ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች አጥብቆ ወደደ፥ አመነባቸውም (25፡27-34)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ረ. ዔሳው ያዕቆብን ለመግደል አቀደ (27፡4)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሰ. ያዕቆብ ወደ አብርሃምና ርብቃ ትውልድ አገር ተመለሰ (27፡42-44፤ 28፡10)።

ሸ. የያዕቆብ ሕልም (28፡11፥ 12)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ቀ. እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለይስሐቅ የሰጣቸውን የተስፋ ቃሎች ለያዕቆብ አስተላለፈ (28፡13-15፤ 29፡1)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

በ. እግዚአብሔር፥ ለያዕቆብ ወደ አገሩ እንዲመለስ ነገረው (31፡13፤ 32፡28)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

የትምህርት 22 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ።

መምህር ሆይ፡- በእያንዳንዱ ትምህርት ውስጥ ከሁሉ የላቀው አስፈላጊ ነገር የመሠረታዊው እምነት ትምህርት ዋና አሳብ መሆኑን አትርሳ። ዝም ብለህ ታሪክ ብቻ አታስተምር። እያንዳንዱን ዋና አሳብ ትምህርቱ በቀረበበት መንገድ ልብ ብለህ አጢነው፤ ደግሞም ጕልቶ የተገለጠውን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት አትኩሮት ሰጠው።

### ሀ. ይስሐቅ ርብቃን አገባ።

ሣራ አርጅታ ሞተች።

ይስሐቅ በእናቱ ሞት እጅግ አዘነ። አባቱ ሚስት ባገኘለትና በዳረው ጊዜ ግን ከእናቱ ሞት ተጽናና (ዘፍጥረት 24፡67፤ 25፡20)።

የይስሐቅ ሚስት ርብቃ የተወለደችው እግዚአብሔር አብርሃምን ወደ ከነዓን ሳይመራው በፊት ይኖርበት በነበረው አገር ነበር።

መምህር ሆይ፡- በካርታ ላይ መስጴጦምያን አሳያቸው። አብራሃምም ደግሞ ሞተ።

### ለ. እግዚአብሔር ስለ ያዕቆብና ስለ ዔሳው ሁሉን ነገር ከመወለዳቸው በፊት ያውቅ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ዘፍጥረት 25፡21-23 አንብብ። እግዚአብሔር ያዕቆብና ዔሳው ምን ዓይነት ሰዎች ሆነው እንደሚያድጉ ገና ከመወለዳቸው በፊት ያውቅ ነበር።

እግዚአብሔር ገና በእናታችን ማኅፀን ሳለን ሁሉ ነገራችንን ያውቃል፤ ከእርሱ የተሰወረ ነገር የለም።

ሐ. ዔሳውና ያዕቆብ ተወለዱ።

ዘፍጥረት 25፡24-26 አንብብ።

መ. ዔሳው የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች አላመነም ወይም ዋጋ አልሰጣቸውም።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 25፡27። ዔሳው ታዋቂ አዳኝ ነበር። የዱር እንስሳትን ባሉበት ቦታ በማጥመድና በመግደል ጊዜውን ያሳልፍ ነበር።

ስለ ነፃ አውጪው አዳኝ የተነገሩት ተስፋዎች የይስሐቅ የበኩር ልጁ ለሆነው ለዔሳው መተላለፍ ነበረባቸው። ነፃ አውጪው ከዘሮቹ አንዱ እንደሚሆን ይታወቅ ነበር። ዔሳው ግን በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች አላመነም ነበር። እንደ አብርሃምና ይስሐቅ በእግዚአብሔር ሊታመን ሲገባው ሳያደርገው ቀረ። ዔሳው እንደ ቃየን ነበር። ኃጢአተኛ መሆኑንና በእግዚአብሔር ተቀባይነትን ማግኘት እንደሚያሻው እንደሆነ አልተመለከተም ነበር። የራሱን መንገድ ብቻ በመሄድ ለዚህ ዓለም ነገሮች ብቻ ይኖር ነበር። እግዚአብሔር ሊሰጠውና ሊያስተምረው ከሚፈልገው ነገር ይልቅ እነዚህ ነገሮች በሕይወቱ የበለጠ ዋጋ ነበራቸው።

እናንተስ? እንደ ቃየንና ዔሳው ናችሁ ወይስ እንደ ያዕቆብ?

መምህር ሆይ፡- እንደነዚህ ዓይነት ቀጥተኛ ጥያቄዎችን ስትጠይቃቸው መልስ ይሰጡህ ዘንድ ጊዜ አትስጣቸው። ውስጣዊ አሳባቸውን በጉባኤ እንዲናገሩ አታስገድዳቸው። ጌታ በልባቸው ያለውን እውነት ወደ ትክክለኛ ራስን መውቀስና እምነት ለማምጣት እንዲጠቀምበት ብቻ ፍቃድ።

ሠ. ያዕቆብ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች አጥብቆ ወደደ፥ አመነባቸውም።

ዋና አሳብ፦ ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 25፡27 አንብብ። ያዕቆብ፥ እንደ አብርሃምና ይስሐቅ ያለ ሰው ነበር። በድንኳኑ በጸጥታ የሚኖር ሰው ነበር። ያዕቆብ በጎችንና ከብቶችን ይጠብቅ ነበር።

ያዕቆብ የእምነት ሰው ነበር። ኃጢአተኛ እንደሆነና እግዚአብሔር ነፃ አውጪ ሊልክለት እንደሚያስፈልገው ተቀብሎ ነበር። በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ላይ ከፍተኛ እምነት የነበረውና የእግዚአብሔርን ምሕረትና እንክብካቤ የሚፈልግ ሰው ነበር።

ዘፍጥረት 25፡28-34 አንብብ። በዔሳው ሕይወት ውስጥ የተፈጸመው ይህ አጋጣሚ የዔሳው ከፍተኛ ፍላጐት ለዚህ ዓለምና ለዕለት መኖር እንደሆነ አሳይቷል። ዔሳው የበኩር ልጅ ስለነበር ከአባቱ እጥፍ ርስት በውርስ ሊያገኝ መብቱ ነበር። አባቱ ሲሞት የቤተሰቡ ራስ ወይም መሪ የመሆን መብት ነበረው። የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ኪዳኖች የሚጠብቅ ከእግዚአብሔር የሆነውን ነፃ አውጪ ለማግኘት የሚቀጥለው ሰው እርሱ ነበር። ዔሳው ግን በአንድ ጊዜ ይህን ሁሉ ለአንድ ሰሐን ምግብ ብሎ ለወጠ።

ዔሳው እንደ ቃየን ዓይነት ሰው ስለነበር ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰይጣንን ተከተለ። እርሱ የማያምንና ሥነ-ምግባር የጎደለው፥ ብልሹ ሰው ነበር።

መምህር ሆይ፦ ዕብራውያን 12፡16ን ልብ በል።

እናንተስ ከእግዚአብሔር እውነት ዞር በማለት እንደ ቃየንና እንደ ዔሳው የራሳችሁን መንገድ እየተከተላችሁ ነውን? ወይስ እንደ አቤል፥ ሄኖክ፥ ኖኅ፥ አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ ኃጢአተኝነታችሁን በመቀበል እግዚአብሔር ነፃ አውጪ እንደሚሰጥ ታምናላችሁ?

ረ. ዔሳው ያዕቆብን ለመግደል አቀደ።

ያዕቆብ፥ አባቱ ይስሐቅ ከአብርሃም የወረሳቸውን የተስፋ ቃሎች ለመውረስ ፈለገ። በዚህ ምክንያት ያዕቆብ የነፃ አውጪው ቀደምት አባት ሆነ። እግዚአብሔር፥ ያዕቆብና ዔሳው ገና ከመወለዳቸው በፊት ይህ መብት ለያዕቆብ እንዲሰጥ ወስኖ ነበር። በመጨረሻ፥ እግዚአብሔር እንዳቀደው ያዕቆብ የብኩርና ሥልጣን ተሰጠው።

ዋና አሳብ:- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዔሳው፥ወንድሙ ያዕቆብ ይህን ሥልጣን ስለወሰደበት እጅግ ተቆጣ። በመሠረቱ ዔሳው በነፃ አውጪው የተስፋ ቃሎች ላይ ፍላጐት አልነበረውም። ነገር ግን በኩር በመሆን የሚገኘውን ሥልጣንና መብቶች ይፈልግ ነበር። ስለዚህ ዔሳው አባቱ እንደ ሞተ ያዕቆብን ለመግደል ዐቀደ። ዘፍጥረት 27፡41 አንብብ።

## ሰ. ያዕቆብ ወደ አብርሃምና ርብቃ ትውልድ አገር ተመለሰ።

የያዕቆብና የዔሳው እናት ርብቃ ዔሳው ያዕቆብን ለመግደል እንዳሰበ አወቀች። ስለዚህ ያዕቆብ ሸሽቶ ወደ ወንድሟ ቤት እንዲሄድ መከረችው። ዘፍጥረት 27፡42-44 አንብብ።

ስለዚህ ያዕቆብ የአባትና እናቱን ቤት ትቶ ወደ መስጴጦምያ ምድር ረጅም ጉዞ ማድረግ ጀመረ። ይህ አያቱ አብርሃም የመጣበት ምድር ነበር። ዘፍጥረት 28፡10 አንብብ።

## ሸ. የያዕቆብ ሕልም

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ከከነዓን እስከ መስጴጦምያ ያለው ርቀት በጣም ረጅም ስለነበር ያዕቆብ እግረ መንገዱን በተራራዎች አጠገብ መተኛት ነበረበት። ዘፍጥረት 28፡11 አንብብ።

አንድ ቀን ማታ ያዕቆብ ተኝቶ ባለበት እግዚአብሔር ለያዕቆብ ሕልምን ሰጠው።

በዚያን ዘመን አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለሰዎች በሕልሞች በኩል ይናገር ነበር። አሁን ግን ቃሉ የተሟላ ስለሆነ ፈቃዱን በቃሉ ውስጥ ይነግረናል።

ዘፍጥረት 28፡12 አንብብ። በዚህ ሕልም አማካይነት እግዚአብሔር ለያዕቆብ ያሳየው የሚመጣው ነፃ አውጪ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያገናኝ መሰላል እንደሚሆን ነው።

በውጪ አገር አንዳንድ ቤቶች ከመሬት ከፍ ብለው የተሠሩ ስለሆነ ያለመሰላል መውጣት አይቻልም። እነዚህ ሰዎች ቤታቸውን ትተው ወደ ዓሣ ማጥመድ ሲሄዱ ውሾች ምግባቸውን እንዳይሰርቁባቸው መሰላሉን ወደ መሬት አውርደው ይሄዳሉ። መሰላሉ ወደ ላይኛው ፎቅ ከፍላቸው የሚወጡበት ነው። ያለመሰላሉ በስተቀር ወደ ቤቶቻቸው መግቢያ መንገድ የለም።

ይህ የሚያሳታውሰን በመጀመሪያ አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር በአንድነት እንደነበሩ ነው። እግዚአብሔር ከአዳምና ሔዋን ጋር ይራመድ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅ ነበሩ። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በጣሱ ጊዜ እነርሱና ልጆቻቸው በሙሉ እናንተና እኛን ጨምሮ ከእግዚአብሔር ተለየን፤ ወደ እግዚአብሔር የመድረሻው መንገድ ወይም መሰላል ተወገደ። ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ሊመለሱ የሚችሉበትና ኅብረት ማድረግ የሚችሉበትን መንገድ እግዚአብሔር ራሱ ካላዘጋጀ በቀር ሌላ መንገድ ሊኖር አይችልም ነበር። እግዚአብሔር ግን ሰይጣንን በመደምሰስ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቅ ነፃ አውጪ እንደሚልክ ተስፋን ሰጠ። ይህ ነፃ አውጪ ያዕቆብ ያየው ምድርና ሰማይን የሚያገናኘው ዓይነት መሰላል ነበር። በዚህ ነፃ አውጪ አማካይነት ሰዎች እንደገና ከእግዚአብሔር ጋር የሚሆኑበትና ከእርሱ ጋር አንድነት የሚፈጥሩበት ሁኔታ ተመቻችቷል።

መምህር ሆይ፡- ዮሐንስ 1፡51 ተመልከት።

እግዚአብሔር ያዕቆብን በዚህ ሕልም አማካኝነት ሊያስተምረው የፈለገው ነገር ምን እንደሆነ እንድትረዱ የሚያግዝ አንድ ታሪክ እነግራችኋለሁ።

ሁለት ጓደኛሞች አንድ የጋራ ጠላት ነበራቸው። ይህ የጋራ ጠላታቸው በጓደኝነታቸው ይቀና ነበር። ስለዚህ ግንኙነታቸውን ለመደምሰስ ወሰና ነበር።

ይህንን ለማድረግ ወደ አንደኛው ሰው ይሄድና ጓደኛው በእርሱ ላይ ከፉ ሤራ እያሤረበት መሆኑን ነገረው። ስለ ጓደኛው የሚነግረው ነገር ሁሉ እውነት እንደሆነ አምኖ እንዲቀበል ለማድረግ ጥረት አደረገ። ሰውዬውም ይህ ጠላት የነገረውን አመነና ከቀድሞ ጓደኛው ጋር የነበረውን ወዳጅነት አቋረጠ። ጓደኝነታቸውም ፈረሰ።

ይህ ጠላት ስለ እርሱ ውሸት የተናገረበት ሌላኛው ሰው ግን ከቀድሞ ወዳጁ ጋር የነበረውን ጓደኝነት ለማደስ ፈለገ። ስለዚህ ጠላት የከፋ ወሬ ቢያስወራበትም፥ ዳሩ ግን ከእርሱ ጋር ግንኙነቱን ያቋረጠውን የቀድሞ ወዳጁን ይወደው ስለነበር፥ይህ መልካም ሰው ከዚያ ከኰረፈው ጓደኛው ጋር እንዲያስታርቀው ልጁን ላከበት። ሰውዬውም የተላከውን የወዳጁን ልጅ ቃል ሰማ፤ በልጁ አማካይነት ወዳጅነታቸው እንደገና ሰመረ።

እግዚአብሔር፥ ለያዕቆብ ያሳየው ይህንን ነበር። በሰይጣን ውሸትና በአዳም ያለመታዘዝ ሰዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ቢለዩም እንኳ እግዚአብሔርና ሰው የሚታረቁበትንና እንደገና አንድነታቸውን የሚመሠርቱበትን መንገድ የሚያበጅ ነፃ አውጪ እንደሚልክ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገባ።

መምህር ሆይ፡- ከላይ በተሰጠው ዓይነት መግለጫ ከተጠቀምክ በገለጻህ ከዚህ በላይ ገፍተህ አትሂድ። የወንጌልን ጉዳይ የጌታ ኢየሱስ ሕይወትን እስከታስተምር ድረስ አቆየው። ከምታስተምረው ቡድን ቀድሞ የሚሄድን ግለሰብ ለብቻው ለማንቃትና ለንስሐ ለማዘጋጀት ካስፈለገህ እንደዚህ ዓይነቱ መግለጫ ለተቤዢው ነፃ አውጪ ታሪክ በጣም ጥሩ መግቢያ ነው።

## ቀ. እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለይስሐቅ የሰጣቸውን የተስፋ ቃሎች ለያዕቆብ አስተላለፈ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘፍጥረት 28፡13-15 አንብብ። እግዚአብሔር ነፃ አውጪ የመላክ ዕቅዱን ይሠራበት ዘንድ ቀጠለ። እግዚአብሔር በዔድን ገነት ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ነፃ አውጪው ተስፋ ከሰጠ ብዙ ዓመታት ያለፉ ቢሆንና የነፃ አውጪው ቀዳሚ አባት የሆነው አብርሃም ቢሞትም

እግዚአብሔር ዕቅዱን አልረሳም። እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሚመጣው ነፃ አውጪ ከእርሱ ዝርያዎች አንዱ እንደሚሆን ነገረው። ያዕቆብም ለአያቱ ለአብርሃምና ለአባቱ ለይስሐቅ የተሰጡት ተስፋዎች ለእርሱ እንደተላለፉ እርግጠኛ ሆነ።

ዘፍጥረት 29፡1 አንብብ።

## በ. እግዚአብሔር ለያዕቆብ ወደ አገሩ እንዲመለስ ነገረው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር፥ ለያዕቆብ ከተናገረው ከብዙ ዓመታት በኋላ ለአብርሃም ሰጥቶት ወደነበረው ምድር እንዲመለስ እንደገና ተናገረው። ዘፍጥረት 31፡13 አንብብ።

ያዕቆብ ሁለት እህትማማቾችን በማግባት የአሥራ ሁለት ልጆች አባት ሆነ።

እግዚአብሔር ያዕቆብን ጠበቀው፤ ምክንያቱም ነፃ አውጪው የሚመጣው ከእርሱ ዝርያዎች በአንዱ ስለነበረ ነው።

እግዚአብሔር፥ የያዕቆብን ስም ወደ እስራኤል ለወጠው። ዘፍጥረት 32፡28 አንብብ።

### ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር፥ ያዕቆብና ዔሳው ከመወለዳቸው በፊት እንኳ ምን ዓይነት ሰዎች እንደሚሆኑ ያወቀው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ስለ ሰዎች ሁሉ ስላለፈው ስለ አሁኑና ስለ ወደ ፊቱ ሁኔታዎች ሁሉን ነገር ስለሚያውቅ ነው።

2. እግዚአብሔር፥ ለአብርሃም የሰጠውን የተስፋ ቃሎች ያዕቆብ እንዲወርስ የመረጠው ያዕቆብ ኃጢአተኛ ስላልነበረ ነውን? አይደለም። ያዕቆብ ኃጢአተኛ ነበር። ነገር ግን በእግዚአብሔር ስለታመነ ነው።

3. በዔሳውና በያዕቆብ መካከል የነበረው ትልቅ ልዩነት ምን ነበር? ዔሳው፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን የነፃ አውጪ ተስፋ ዋጋ አልሰጠውም ነበር። ዔሳው ኃጢአተኛ እንደሆነና

በእግዚአብሔር ምሕረት መታመን እንዳለበት ሳይቀበል ቀረ። ዔሳው የሚኖረው ለዕለታዊና ለቁሳዊ ጥቅም ነበር። ያዕቆብ ግን ኃጢአተኛ እንደሆነ በማወቅ በእግዚአብሔር ታመነ። ያዕቆብ እግዚአብሔር ስለ ነፃ አውጪ የሰጠውን ተስፋዎች ዋጋ ሰጥቶ ፈለጋቸው።

4. እግዚአብሔር ስለ ነፃ አውጪ አዳኝ ተስፋ፥ በዔድን ገነት የሰጠውንና ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን ያልረሳው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር የማይለወጥና ሁልጊዜ የተናገረውን የማይረሳ ስለሆነ ነው።

5. ያዕቆብ፥ እግዚአብሔር በሰጠው ሕልም የተመለከተው ምን ነበር? ከምድር እስከ ሰማይ የተዘረጋ መሰላል ነበር። እግዚአብሔር ከመሰላሉ በላይ ቆሞ ነበር። የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡና ይወርዱበት ነበር።

6. የዚህ ሕልም ትርጉም ምን ነበር? ትርጉሙ:- የያዕቆብ ዝርያ የሆነው ነፃ አውጪ ሰማይና ምድርን እንደ መሰላል ሆኖ እንደሚያገናኝ ነው። በነፃ አውጪው አማካይነት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና ወደ አንድነት የሚመጡበት መንገድ እንደሚከፈት ነው።

7. እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሰጠው አዲስ ስም ማን ነበር? እስራኤል ነበር።

8. ያዕቆብ፥ በመስጴጦምያ ብዙ ዓመታት ከኖረ በኋላ እግዚአብሔር ወደ የት እንዲሄድ ነገረው? እግዚአብሔር የነገረው ለአያቱ ለአብርሃም ወደ ሰጠው ወደ ከነዓን ምድር እንዲመለስ ነበር።

9. ያዕቆብ ስንት ልጆች ነበሩት? አሥራ ሁለት።

# ትምህርት 24

የትምህርት ክፍል፡- ዘፍጥረት 37-39

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር ዮሴፍን መራው፥ ጠበቀውም።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. ያዕቆብ ወደ ከነዓን ተመለሰ (37፡ 1)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ለ. ዮሴፍ፥ የያዕቆብ ውድ ልጅ (37፡ 2፥3)።

ሐ. የዮሴፍ ትላልቅ ወንድሞች ዮሴፍን ጠሉት (37፡ 4)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

መ. የዮሴፍ ሕልሞች (37፡ 5-11)።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ሠ. ዮሴፍ ወደ ግብፅ ተሸጠ (37፡ 12-35)።

ረ. ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት አገለገለ (39፡ 1-19)።

ሰ. ዮሴፍ ወደ ወኅኒ ተጣለ (39፡ 20-23)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

## የትምህርት 23 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. ያዕቆብ ወደ ከነዓን ተመለሰ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘፍጥረት 37፡1 አንብብ። እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን በሙሉ ለያዕቆብ ጠበቀ። ያዕቆብን በሰላም ወደ አገሩ እንዲደርስ አደረገው።

መመህር ሆይ፡- የዮሴፍ ታሪክ እስራኤላውያን ወደ ግብፅ እንዴት እንደወረዱ የሚናገር አገናኝ ታሪክ ነው። የዚህ ትምህርት አብዛኛውን ክፍል ምንም ዓይነት ማብራሪያ ሳይሰጥበት ታሪኩን ከመጽሐፍ ቅዱስ በጥንቃቄ በማንበብ ብቻ መረዳት ይቻላል። ነገር ግን አዳማጮችህ ታሪኩን ለመረዳታቸው እርግጠኛ ሁን፥ ለሚነሱ ጥያቄዎች ዕድል ለመስጠት እንዲያመች ረጋ በል። በካርታው ላይ ግብፅን አመልክታቸው።

## ለ. ዮሴፍ፥ የያዕቆብ ውድ ልጅ።

ዘፍጥረት 37፡2፥ 3 አንብብ። የዮሴፍ ወንድሞች ክፉ ነገር በሚያደርጉበት ጊዜ ዮሴፍ ለአባቱ ይነግር ነበር።

## ሐ. የዮሴፍ ታላላቅ ወንድሞች ዮሴፍን ጠሉት።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 37፡4 አንብብ። ዮሴፍ ወንድሞቹ ክፉ በሚያደርጉበት ጊዜ ለአባቱ ይነግር ስለነበርና አባቱ ያዕቆብ ከሁሉ አብልጦ ይወደው ስለነበር ወንድሞቹ በሙሉ ጠሉት።

ሰዎች የሚቈጡትና አንዱ ሌላውን የሚጠላው እያንዳንዱ ሰው ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተወለደና ልቡ ክፉ ስለሆነ ነው። ቁጣ፥ ጥላቻና ብዙ ክፉ ነገሮች በልባችሁና በአእምሮአችሁ የሚፈጠሩበት ምክንያት ይህ ነው። ሁላችሁም ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ ተወልዳችኋልና ራሳችሁን ልትለውጡ የምትችሉበት መንገድ የለም።

## መ. የዮሴፍ ሕልሞች

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ዘፍጥረት 37፡5-11 አንብብ። እግዚአብሔር በዮሴፍና በያዕቆብ ቤተሰብ ምን እንደሚሆን በትክክል ያውቅ ነበር። ዮሴፍ የወደፊት ሁኔታውን ማየት አይችልም ነበር። ሕልሞቹ እንዴት እንደሚፈጸሙ

አያውቅም ነበር። ነገር ግን ዮሴፍ በቤተሰቡ ላይ መሪና ገዥ እንደሚሆን እግዚአብሔር ግልጽ አደረገ።

እግዚአብሔር የወደፊቱን ነገር በሙሉ ያውቃል። የዮሴፍን የወደፊት ሁኔታ እንዳወቀ የእኛንም የወደፊት ዕድል ያውቃል።

ሠ. ዮሴፍ ወደ ግብፅ ተሸጠ።

ዘፍጥረት 37፡ 12-35 አንብብ።

ረ. ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት አገለገለ።

ዘፍጥረት 39፡ 1-19 አንብብ።

ሰ. ዮሴፍ ወደ ወኅኒ ተጣለ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ዘፍጥረት 39፡20-23 አንብብ። ዮሴፍ ወንድሞቹ ቢጠሉትና የጲጥፋራ ሚስት ውሸት ብትናገርበትም እንኳ በእውነተኛው ሕያው አምላክ መደገፉን ቀጠለ። ኃጢአተኛ መሆኑንና ይቅርታ ሊያገኝ የሚችለው በእግዚአብሔር ምሕረት ብቻ መሆኑን ያውቅ ነበር። እንደ አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ታመነ።

መምህር ሆይ፡- ዕብራውያን 11፡22 ተመልከት።

አንድ ሰው እግዚአብሔር የተናገረውን ካላመነ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይችልም። ልታደርጉአቸው ከምትችሉአቸው ነገሮች ሁሉ የላቀው የእግዚአብሔርን ቃል እውነት መቀበልና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጻፋቸው ነገሮች ሁሉ ላይ መደገፍ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር፥ ዮሴፍን በእስር ቤት በተጣለ ጊዜ እንኳ አልጣለውም። እግዚአብሔር ለዮሴፍ ሕይወት አስደናቂ ዕቅድ ስለነበረው ተገቢውን እንክብካቤ ያደርግለት ነበር። አሁን ዮሴፍ በወኅኒ ተጥሎ እያለ የቤተሰቡ መሪና ገዥ የመሆኑ ጉዳይ ፈጽሞ የማይቻል የሚመስልበት ሁኔታ ተከሰተ። ነገር ግን እግዚአብሔር አይለወጥም። እርሱ የገባቸውን ቃል ኪዳኖች ሁልጊዜ ይፈጽማል። እርሱ

አሳባቸውን እንደሚቀይሩ፥ የገቡትን ቃል ኪዳኖች እንደሚረሱና ውሸትን እንደሚናገሩ ሰዎች አይደለም።

## ጥያቄዎች

1. ለያዕቆብ ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ ወደ ከነዓን የመለሰው ማን ነበር? እግዚአብሔር።

2. የያዕቆብ ተወዳጅ ልጅ ማን ነበር? ዮሴፍ።

3. አባቱ ከሁሉ አብልጦ የሚወደው ልጅ ዮሴፍ ስለነበር ወንድሞቹ ምን አደረጉ? በዮሴፍ በመቅናት ጠሉት።

4. የዮሴፍ ሕልም ምን ነበር? ዘፍጥረት 37፡7-9 አንብብ።

5. የእነዚህ ሕልሞች ትርጉም ምንድን ነበር? ዮሴፍ በቤተሰቦቹ ሁሉ ላይ የበላይ የመሆን ሥልጣን እንደሚያገኝ ነበር።

6. የዮሴፍን የወደፊት ጉዳይ በማወቅ ስለ ወደ ፊት ዕድሉ በሕልም ያስታወቀው ማን ነበር? እግዚአብሔር ነበር።

7. እግዚአብሔር ስለ ወደፊት ሁኔታችሁ ምን ያህሉን ያውቃል? ሁሉንም ያውቃል።

8. የዮሴፍ ታላላቅ ወንድሞች ምን አደረጉ? ዮሴፍን በባርነት ወደ ግብፅ ሸጡት።

9. ዮሴፍ በግብፅ ምን ደረሰበት? የዮሴፍ አሳዳሪ የነበረው ሰው ሚስት በሐሰት ስለወነጀለችው ወደ ወኅኒ ተጣለ።

10. ዮሴፍ በወኅኒ እያለ ማን ተገቢ እንክብካቤ አደረገለት? እግዚአብሔር።

11. እግዚአብሔር ለዮሴፍ የተጠነቀቀለት ለምን ነበር?
    ሀ. ዮሴፍ ኃጢአተኛ ቢሆንም እንኳ በእግዚአብሔርና በምሕረቱ ስለታመነ፥
    ለ. እግዚአብሔር ስለ ነፃ አውጪው የገባቸውን የተስፋ ቃሎች ስላመነ።
    ሐ. እግዚአብሔር ለዮሴፍ ሕይወት አስደናቂ የሆነ ዕቅድ ስለነበረው ነው፥

## ትምህርት 25

የትምህርት ክፍል:- ዘፍጥረት 41፡1-8፥ 14-16፥ 25-49፤ 42፡1-20፤ 43፡1-5፥ 11-17፥ 45፡1-11፥ 25-28፤ 46፡5-7

አጠቃላይ ርእስ:- እግዚአብሔር ዮሴፍን ከፍ አደረገው እስራኤልንም ወደ ግብፅ ወሰደ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች:-

ሀ. የፈርዖን ሕልሞች (41፡1-8)።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ለ. ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልሞች ተረጐመ (41፡14-16፥ 25-37)።

. ሰው ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሐ. ዮሴፍ ከፈርዖን ቀጥሎ ያለው የሥልጣን ስፍራ ተሰጠው (41፡38-49)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

መ. የዮሴፍ ወንድሞች ምግብ ፍለጋ ወደ ግብፅ መጡ (42፡1-20)።

ሠ. ዮሴፍ እውነተኛ ማንነቱን ገለጠ (43፡1-5፥ 11-17፤ 45፡1-11)።

ረ. እስራኤል ወደ ግብፅ ወረዱ (45፡25-28፤ 46፡5-7)።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

የትምህርት 24 ጥያቄዎችን ከልስ።

### የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. የፈርዖን ሕልሞች።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ዘፍጥረት 41፡1-8 አንብብ። እግዚአብሔር ባለፉት ዘመናት ለሰዎች በሕልም እንደተናገረ ሁሉ ለፈርዖንም በግብፅ ምን እንደሚፈጸም በተመሳሳይ ሁኔታ ቢገልጽለትም፥ አሁን ለእኛ የሚናገርበት የተለመደው መንገድ ግን ይህ አይደለም። ለምን? እግዚአብሔር ወደ ፊት የሚሆነውን ነገር አሁን አያውቅም ማለት ነውን? አይደለም። እርሱ ሁሉን ያውቃል። እርሱ አልተለወጠም፥የወደፊቱን ነገር ሁሉ አሁንም ያውቃል። ታዲያ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ለሰዎች በሕልም የማይናገር ከሆነ ስለ ወደ ፊቱ እንድናውቀው የሚፈልገውን ነገር እንዴት ይነግረናል? እንድናውቀው የሚፈልገውን ነገር በቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያስተምረናል።

የግብፅ ንጉሥ የነበረው ፈርዖን እውነተኛውንና ሕያው የሆነውን አምላክ አያውቅም ነበር። ግብፃውያን፤ ፀሐይ፥ ጨረቃን፥ ከዋክብትን፥ እንስሳትን፥ ተሳቢ ፍጥረታትንና አባይ በመባል የሚታወቀውን የአገሪቱን ትልቅ ወንዝ ያመልኩ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ባያመልኩትም እንኳ ዓላማዎቹን ከፍጻሜ ለማድረስ ይህንን ንጉሥና አገሩን ተጠቀመበት።

እግዚአብሔር፥ እርሱን ባያመልኩም እንኳ የሰዎች ሁሉና የዓለም አገሮች በሙሉ ገዥ ነው። ዓላማዎቹን ወደ ፍጻሜ ለማምጣት እርሱ በመረጠው በማናቸውም መንገድ ይጠቀማል።

ለመሆኑ በቤታችሁ የሚገኘውን ጦር ወይም መሶብ ወይም ቅርጫት ለምን ልትጠቀሙብት እንደምትችሉና እንደማትችሉ ሌሎች ሰዎች ሊያዟችሁ ይችላሉን? አይችሉም! ሁሉንም ለምትፈልጉት ነገር ልትጠቀሙባቸው ትችላላችሁ። የሠራችኋቸው እናንተ እንደ መሆናችሁ ባለቤቶቻቸውም እናንተ ናችሁ።

እግዚአብሔር የሰዎች ሁሉ ፈጣሪ ነው። ሕይወትን የሰጠንና የሚጠብቅልን እርሱ ነው፤ የፈጠረን እርሱ ነው። ስለዚህ የእርሱ ነን። እግዚአብሔር በእኛ ላይ የሚፈልገውን ነገር ያደርጋል። ነገር ግን

እግዚአብሔር ጻድቅ ስለሆነ በሰዎች ላይ የሚያደርገው ማንኛውም ነገር ትክክል ነው።

መምህር ሆይ፡- የንጉሥን ሥልጣን ግለጽ። የግብፅ ነገሥታት ፈርዖን የሚል መጠሪያ እንደነበራቸው ንገራቸው።

ለ. ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልሞች ተረጐመ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ዘፍጥረት 41፡14-16፥ 25-37 አንብብ። ዮሴፍ የንጉሡን ሕልሞች በራሱ ለመፍታት አይችልም ነበር። ነገር ግን የሕልሞቹን ፍቺዎች እንደሚሰጠው በእግዚአብሔር ታመነ። እግዚአብሔር ለዮሴፍ በአገሪቱ ሊሆን ያለውን ነገር ለንጉሡ እንዲያሳውቅ መገለጥን ሰጠው።

እግዚአብሔር በእርሱ የሚታመኑትን ፈጽሞ አይጥልም።

ሐ. ዮሴፍ ከፈርዖን ቀጥሎ ያለው የሥልጣን ስፍራ ተሰጠው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘፍጥረት 41፡38-49 አንብብ። ዮሴፍ በአስቸጋሪ ልምምዶች ውስጥ ያለፈ ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር ነገሮችን ይቈጣጠር ነበር። ጌታ ዮሴፍን አልረሳውም ነበር። እግዚአብሔር በልጅነቱ ጊዜ የሰጠው ሕልሞች ተፈጻሚነት የሚያገኙበት ጊዜ አሁን ደረሰ።

እግዚአብሔር ሁልጊዜ ያቀደውን ያደርጋል። ማንም ሊቃወመው አይችልም። ሊያደርገው ያቀደው ነገር የሚከናወንበት ጊዜ ሲደርስ ዮሴፍን ከወኅኒ ቤት አውጥቶ ከፍተኛ ሥልጣን ሰጠው። ይህም በልጅነቱ ጊዜ እግዚአብሔር ላሳየው ሕልሞች ተፈጻሚ መሆን ማረጋገጫ ነው።

መ. የዮሴፍ ወንድሞች ምግብ ፍለጋ ወደ ግብፅ ወረዱ።

ዘፍጥረት 42፡1-20 አንብብ።

ሠ. ዮሴፍ እውነተኛ ማንነቱን ገለጠ።

ዘፍጥረት 43፡1-5፥ 11-17፤ 45፡1-11 አንብብ።

ረ. እስራኤል ወደ ግብፅ ወረዱ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ዘፍጥረት 45፡25-28፤ 46፡5-7 አንብብ። ከብዙ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሮቹ ወደ ግብፅ እንደሚወርዱ ነግሮት ነበር። በርካታ መቶ ዓመታት ያለፉ ቢሆንም እግዚአብሔር ቃል የገባውን አከናወነ። እግዚአብሔር የተናገራቸው ነገሮች በሙሉ እንደ ቃሉ ይፈጸማሉ።

መምህር ሆይ፡- ዘፍጥረት 15፡13 ተመልከት።

ከዚህን ጊዜ ጀምሮ የያዕቆብ ወይም የእስራኤል ዝርያዎች፥ የእስራኤል ልጆች፥ወይም እስራኤላውያን ወይም እስራኤል በመባል ይታወቁ ጀመር።

## ጥያቄዎች

1. ለዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም እንዲፈታ ጥበብን የሰጠ ማን ነው? እግዚአብሔር።

2. የፈርዖን ሕልም ትርጉም ምን ነበር? እግዚአብሔር ለንጉሡ፥ በአገሩ ሰባት የጥጋብ ሰባት የረሃብ ዘመን እንደሚኖር ሲያስታውቀው ነበር።

3. እግዚአብሔር ሰዎች በማያውቁበትና በማያመልኩበትም ስፍራ እንኳ የሚፈልገውን ነገር ማድረግ ይችላልን? አዎን! እርሱ ኃያል ስለሆነ የሚፈልገውን ማድረግ ይችላል።

4. እግዚአብሔር ለዮሴፍ በወጣትነቱ የሰጠውን ሕልም ፍች እንዴት ፈጸመለት? ጌታ የንጉሡን ሕልሞች እንዲፈታ ለዮሴፍ ጥበብን በመስጠት ከንጉሡ ቀጥሎ ያለውን ሁለተኛ ስፍራ እንዲይዝ አደረገ።

5. ያዕቆብ ቤተሰቡን በሙሉ ወደ ግብፅ ይዞ የወረደው ለምንድን ነው?

   ሀ. ያዕቆብ ዮሴፍ በግብፅ እንዳለ በመስማቱ፥

ለ. በግብፅ ብዙ ምግብ ስለነበረ፥

ሐ. ንጉሡ፥ ያዕቆብን ወደ ግብፅ እንዲመጣና እንዲኖር ስለጋበዘው።

6. የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ ዝርያዎች ማን በመባል ይታወቁ ነበር? የእስራኤል ልጆች፥ እስራኤላውያን፥ እስራኤል።

## ትምህርት 26

የትምህርት ክፍል፡- ዘጸአት 1፡1-22፤ 2፡1-22

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር በግብፅ በባርነት የነበሩትን እስራኤላውያንን ጠበቀ።

እግዚአብሔር ሙሴን መረጠ፥ ጠበቀው፥ የሚያስፈልገውን ሁሉ ሰጠው።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. ዮሴፍና የእርሱ ትውልድ የነበሩት ሰዎች ሁሉ በግብፅ ሞቱ (1፡1-6)።

ለ. እስራኤላውያን በቁጥርና በሃብት እያደጉ ሄዱ (1፡7)።

ሐ. የአዲሱ ንጉሥ የተንኮል ዕቅዶች (1፡8-11)።

. ሰይጣን ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው። ሰዎችን ይጠላል።

መ. እግዚአብሔር ለእስራኤል ተጠነቀቀ (1፡12-22)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ሠ. የሙሴ መወለድና የእናቱ ዕቅድ (2፡1-4)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ረ. የፈርዖን ልጅ ሙሴን ልጇ አድርጋ ለማሳደግ ወሰደችው (2፡5-10)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ሰ. ሙሴ ሙሉ ሰው በሆነበት ጊዜ (2፡11-22)።

. ሰይጣን ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው። ሰዎችን ይጠላል።

የትምህርት 25 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ።

### ሀ. ዮሴፍና የእርሱ ትውልድ የነበሩት ሰዎች ሁሉ በግብፅ ሞቱ።

ዘጸአት 1፡1-6 አንብብ። የራቡ ጊዜ ቢያልፍም ዮሴፍ፥ ወንድሞቹና ቤተሰቦቹ አባታቸው ከሞተ በኋላ እንኳ በግብፅ መኖራቸውን ቀጠሉ። እግዚአብሔር፤ ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ወደ ሰጣቸው ምድር አልተመለሱም። ዮሴፍና የእርሱ ትውልድ የነበሩት ሰዎች ሁሉ በግብፅ እንደሞቱ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

መምህር ሆይ፡- ወደ ካርታው አመልከት።

### ለ. እስራኤላውያን በቁጥርና በሃብት እያደጉ መጡ።

ዘጸአት 1፡7 አንብብ። የእስራኤል ልጆች በግብፅ መኖራቸውን ቀጠሉ፥ ቁጥራቸው በከፍተኛ ደረጃ እያደገ መጣ ሃብታቸውም እየጨመረ ሄደ። የበርካታ ላሞች ፍየሎችና በጐች ባለቤት ሆኑ። ለእንስሶቻቸው የሚሆን በቂ ግጦሽ ስለነበረና ንጉሡም ለእነርሱ መልካም ስለነበር የግብፅ ኑሮ ያስደስታቸው ነበር። ነገር ግን ብዙ ሳይቆይ ሁኔታዎች ተቀየሩ።

### ሐ. የአዲሱ ንጉሥ የተንኮል ዕቅዶች።

ዋና አሳብ፡- ሰይጣን ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው። ሰዎችን ይጠላል።

ዘጸአት 1፡8-11 አንብብ። ንጉሡን በክፉ ዕቅድ እንዲመራ ያነሣሣው ማን ይመስላችኋል? እግዚአብሔርንና ሰውን የሚጠላው ኃይለኛ ክፉ መንፈስ ማን ነው? ሰይጣን የእስራኤልን ሕዝብ ለማጥፋት የፈለገው ለምን ይመስላችኋል? ሰይጣን፥ እግዚአብሔር እርሱን በመደምሰስ ሰውን ከእርሱ ኃይል ነፃ የሚያወጣ አዳኝ እንደሚልክ የሰጠውን የተስፋ ቃል ያውቅ ነበር። እንደዚሁም ይህ ነፃ አውጪ አዳኝ የሚወለደው ከእስራኤል ሕዝብ እንደሆነ እግዚአብሔር የገባውን የተስፋ ቃል ያውቅ ነበር። ደግሞም ነፃ አውጪው አዳኝ

ከአብርሃም ዘር እንደሚሆን ሰይጣን ያውቅ ነበር። ሰይጣን የእስራኤልን ሕዝብ ለማጥፋት ይፈልግ የነበረው እግዚአብሔር በዓለም ያለውን ዕቅድ ለመፈጸም የመረጠው ሕዝብ መሆኑን ያውቅ ስለነበር ነው። ሰይጣን ማንም ሰው ከእርሱ ኃይል ነፃ እንዲወጣና ከእግዚአብሔር ቅጣት እንዲድን አይፈልግም።

የሰይጣን ፍላጐት እናንተ ሁላችሁ ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ መኖራችሁን እንድትቀጥሉና በእግዚአብሔር የቅጣት እጅ እንድትወድቁ ነው። ሁላችሁንም ስለሚጠላ የእግዚአብሔርን ቃል እንድትሰሙ አይፈልግም። ሰይጣን እስራኤልን ለማጥፋት ፈርዖንን መሣሪያ እንዳደረገ ሁሉ፥ እናንተም የእግዚአብሔርን መልእክት ሰምታችሁ እንዳታምኑ በሌሎች ሰዎች በመጠቀም ይከላከላል። ነገር ግን እግዚአብሔር ቃሉን እንድትሰሙና በሰይጣን ውሸቶች ከመጥፋት እንድትድኑ ይፈልጋል።

## መ. እግዚአብሔር ለእስራኤል ተጠንቅቋል።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር ሕዝቡን እስራኤልን አልረሳም። እነሆ ይንከባከባቸው ነበር። የሰይጣንን ዕቅድ ያውቅ ነበርና እስራኤልን ጠበቀ። ዘጸአት 1፡12-22 አንብብ።

መምህር ሆይ፡- ይህን ክፍል በምታነብበት ጊዜ ምናልባት ግልጽ አይሆን ይሆናል ብለህ የምታስበውን የትኛውንም ክፍል አብራራ።

የእግዚአብሔር ዕቅድ ሕዝቡን ከፋ ከሆነው ንጉሥና ሰይጣን ካቀደባቸው ጥፋት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ከግብፅ አውጥቶ ሊሰጣቸው ወዳቀደው ምድር ይመራቸው ዘንድ ጭምር ነበር።

## ሠ. የሙሴ መወለድና የእናቱ ዕቅድ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

የጊዜ ቅደም ተከተል በሚያሳይ ሠንጠረዥ ላይ፥ «ሙሴ፥ አሮን፥ ኢያሱ» የሚሉትን ስሞች አሳይ።

ዘጸአት 2፡ 1-4 አንብብ። የዚህ ሕፃን ልጅ ወላጆች በእግዚአብሔር ታመኑ። እግዚአብሔር ለልጃቸው ጥንቃቄ እንደሚያደርግ አመኑ።

## ረ. የፈርዖን ልጅ ሙሴን ልጇ አድርጋ ለማሳደግ ወሰደችው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘጸአት 2፡5-10 አንብብ። እግዚአብሔር ሙሴን ለመጠበቅ የከፉውን ንጉሥ ሴት ልጅ ተጠቀመባት።

እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን ከባርነት ነፃ ለማውጣት በሙሴ ለመጠቀም ዐቅዶ ነበር። እግዚአብሔር፥ ሙሴ ዋስትና የሚያገኘው ከየትኛውም ስፍራ ይልቅ በንጉሡ ቤት እንደሆነ ያውቅ ነበር። በተጨማሪ ሙሴ ወደ ፊት ሕዝቡን ለሚመራበት ሥራው በርካታ ነገሮችን ከንጉሡ ቤት ሊማር እንደሚችል ያውቅ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር ከሰይጣን ይበልጣል። እግዚአብሔር ከማንኛውም ነገርና ከማንኛውም ሰው ይበልጣል። ያቀደውን ለመፈጸም የሚከለክለው የለም።

እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው። ልንደገፍበት እንችላለን። ለሕዝቡ ለእስራኤል ይጠነቀቅ እንደነበር ለእናንተም ይጠነቀቃል። ከሰይጣን ኃይል እንዴት እንደምታመልጡና ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁ ግንኙነት እንዴት እንደሚስተካከል ለማወቅ ቃሉን ስሙ።

## ሰ. ሙሴ ሙሉ ሰው በሆነበት ጊዜ

የሚቀጥለው የታሪኩ ክፍል የሚናገረው ሙሴ ሙሉ ሰው ወደመሆን በደረሰበት ጊዜ ምን እንደተፈጸመ ነው። ይህንንም የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን። ዘጸአት 2፡ 11-22 አንብብ።

እስራኤላውያን በከፉው ንጉሥ ቀንበር ሥር ወድቀው ነበር። ሊያመልጡትም አይችሉም ነበር። ሙሴ ሊረዳቸው ቢሞክርም እንኳ አልተሳካለትም። ከዚህ ከፉ ንጉሥ ሊታደጋቸው የሚችል ማንም አልነበረም።

8. አንተ፥ ወይም እኔ ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው፥ ሰይጣን በእናት ላይ በመንፈሱ አማካይነት ከሚያደርግባችሁ ቁጥጥር ነፃ ልናወጣችሁ እንችላለንን? አንችልም።

9. ከሰይጣን ቁጥጥር ነፃ ሊያወጣችሁ የሚችል ብቸኛው ኃይል ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

## ትምህርት 27

የትምህርት ክፍል፡- ዘጸአት 2፡23-25፤ 3፡1-20፤ 4፡1-20

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር፥ ሙሴን ሕዝቡን ነፃ እንዲያወጣ ጠራው።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር በባርነት ወደ ነበሩት የእስራኤል ሕዝብ ተመለከተ፥ ጩኸታቸውንም ሰማ (2፡23-25)።

- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።
- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ለ. ሙሴ የሚቃጠለውን ቁጥቋጦ ተመለከተ (3፡1-3)።

- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ሐ. እግዚአብሔር መልእክቱን ለሙሴ ሰጠ (3፡4-12)።

- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።
- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው።
- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

መ. «እኔ ነኝ» (3፡13-18)።

- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ሠ. እግዚአብሔር ንጉሡ ምን እንደሚያደርግ ያውቅ ነበር (3፡19፥ 20)።

- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ረ. እግዚአብሔር ለሙሴ ምልክቶችን ሰጠ (4፡1-12)።

ሰ. እግዚአብሔር ለሙሴ ረዳት ይሆን ዘንድ አሮንን ሾመ (4፡13-17)።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሸ. ሙሴ ጌታን ታዘዘ (4፡18-20)።

የትምህርት 26 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

### ሀ. እግዚአብሔር በባርነት ሥር ወደነበሩት የእስራኤል ሕዝብ ተመለከተ፥ ጩኸታቸውንም ሰማ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘጸአት 2፡23 አንብብ። እስራኤላውያን ለ400 ዓመታት በባርነት ሥር ነበሩ። እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን የሚፈጽምበትን ጊዜ ማቀድ ጀመረ። እግዚአብሔር ለአብርሃም ከገባቸው ቃል ኪዳኖች አንዱ፥ ለ400 ዓመታት በግብፅ በባርነት ቢቆዩም እንኳ በአራተኛው ትውልድ ነፃ እንደሚያወጣቸው ነበር፤ ዘፍጥረት 15፡13-16 አንብብ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

እስራኤላውያን፥ ከግብፅ ነፃ ልንወጣ የምንችልበት ጊዜ ይመጣ ይሆንን? ከሚል የሐዘን ጥርጣሬ ላይ ሳይወድቁ አልቀሩም። ነገር ግን እግዚአብሔር ለእርዳታ ያሰሙትን ጩኸት ሰማ። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ይወዳቸው ስለነበር አዘነላቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘጸአት 2፡24፥ 25 አንብብ። እግዚአብሔር፤ ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት የገባቸውን ቃል ኪዳኖች አልዘነጋም።

እግዚአብሔርን በዓይኖቻችን ልናየው ስለማንችልና፥ በጆሮዎቻችን ልናደምጠው ስለማንችል የተስፋ ቃሎቹን የረሳ የሚመስልበት ጊዜ አለ። ብዙ ዓመታት ሲያልፉ ምንም ነገር የማያደርግ ቢመስልም እንኳ እርሱ ፈጽሞ አይዘነጋም። እግዚአብሔር ቸኩሎ አያውቅም። በጊዜው፥ ያቀደውንና ቃል የገባውን በሙሉ ይፈጽማል። ጀምሮ የሚያቋርጠው ምንም ነገር የለም።

## ለ. ሙሴ የሚቃጠለውን ቁጥቋጦ ተመለከተ

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ዘጸአት 3፡1-3 አንብብ። ይህ ቁጥቋጦ ተራ ቁጥቋጦ ነበር። ጨርሶ ያልተለመደው ግን ቁጥቋጦው እየነደደ ተቃጥሎ አለማለቁ ነበር። እግዚአብሔር በቁጥቋጦ ውስጥ ስለነበር የቁጥቋጦው እሳት ቁጥቋጦውን ሊያቃጥለው አልቻለም።

እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው። እግዚአብሔር ሊያደርገው የሚችለውን ነገር ማንም ሊያደርገው አይችልም።

የሚነድደው ቁጥቋጦ ለሙሴ ሕዝቡ እስራኤል የነበሩበትን አስጨናቂ ሁኔታዎች የሚያሳይ ነበር። እንደሚነደው ቁጥቋጦ ሁሉ እስራኤላውያንም ሙሉ በሙሉ ሊጠፉ በሚችሉበት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ። እግዚአብሔር በቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ ቁጥቋጦው ተቃጥሎ እንዳያልቅ እንደተከላከለ፥ የአብርሃም ዘር ከነበሩት ከእስራኤላውያንም ጋር ነበር። እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ስለነበር ሰይጣንና ፈርዖን ሊያጠፏቸው (ሊያቃጥሏቸው) አልቻሉም።

## ሐ. እግዚአብሔር መልእክቱን ለሙሴ ሰጠ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ዘጸአት 3፡4 አንብብ። ሙሴ፥ እግዚአብሔር ከእሳቱ መካከል እስኪናገረው ድረስ በቁጥቋጦው ውስጥ መኖሩን አላወቀም ነበር።

እግዚአብሔር የሙሴን ቋንቋ ያውቅ ነበር። ሙሴ የሚናገረው አማርኛ አልነበረም።

እግዚአብሔር የማያውቀው ቋንቋ የለም። እግዚአብሔር ሁሉንም ቋንቋዎች እንደማወቁ ሁሉ የእናንተንም ቋንቋ ያውቃል። እግዚአብሔር፥ የምታስቡትንና የምትናገሩትን ሁሉ ያውቃል፥ ያዳምጣል። በሹክሹክታ የተነገረውን እንኳ ቢሆን እግዚአብሔር ይሰማል፥ ይረዳልም።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው።

ዘጸአት 3፥5፥ 6 አንብብ። እግዚአብሔር፥ ሙሴን ለፍጹሙና ለታላቁ ፈጣሪ ያለውን አክብሮት ጫማውን በማውለቅ እንዲያሳይ ነገረው። በባዶ እግር መሆን የትሕትናና ራስን የማስገዛት ምልክት ነው። በዚያን ጊዜ ባሪያዎች የሚሄዱት በባዶ እግራቸው ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲያደርግ የወደደውን ይመርጣል። ዕቅዶቹን ለመፈጸም ጊዜው በሚደርስበት ወቅት የሚከለክለው የለም።

እግዚአብሔር፥ ለሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነፃ በማውጣት ለአብርሃም ወደ ሰጠው ምድር እንዲመራቸው እንደ መረጠው ነገረው፤ ዘጸአት 3፡7-1 አንብብ።

ሙሴ፥ ቀደም ብሎ ሕዝቡን ለመርዳት ያደረገው ጥረት እንዳልተሳካ ስለተመለከተ በራሱ ኃይል ንጉሡን ለመጋፈጥና እስራኤልን ከባርነት ነፃ ለማውጣት እንደማይችል ተረድቶ ነበር፤ ዘጸአት 3፡11 አንብብ።

እግዚአብሔር፥ ለሙሴ ከእርሱ ጋር እንደሚሆን ነገረውና ምልክትን ሰጠው። የሚቃጠለውን ቁጥቋጦ ፊት ለፊት ወደ አየበት ወደዚህ ተራራ መልሶ እንደሚያመጣው እግዚአብሔር ለሙሴ ቃል ኪዳን ገባለት። ይህ ተራራ የሲና ተራራ ወይም የኮሬብ ተራራ በመባል ይታወቅ ነበር፤ ዘጸአት 3፡12 አንብብ።

መ. «እኔ ነኝ»

መምህር ሆይ፡- የአዳማጮችህ ስሞች ትርጉም ያላቸው ከሆነ ለሚቀጥሉት ቁጥሮች መግለጫና መግቢያ አድርገህ ተጠቀምባቸው።

ዘጸአት 3፡13 አንብብ። ሙሴ አሁንም አልረካም ነበር። ከዚህ ቀደም የእስራኤልን ሕዝብ ሊረዳ በሞከረ ጊዜ ያልተቀበለው ሕዝቡ ራሱ ነበር። አሁንም ወደ እነርሱ ተመልሶ የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔር ከባርነት ነፃ እንዳወጣችሁ ልኮኛል ቢላቸው ያምኑ ወይም አያምኑ እንደሆን እርግጠኛ አልነበረም።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸአት 3፡14 አንብብ። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በተጻፈበት ወቅት ስሞች ሁሉ ትርጉም ነበራቸው። የአንድ ሰው ስም በአንዳንድ ግላዊ ባሕርያት ወይም ብቃቶች ላይ ያተኩር ነበር። ለምሳሌ፦ የሙሴ ስም ትርጉም ‹መውጣት› ማለት ነበር። ምክንያቱም የንጉሡ ልጅ ባገኘችው ጊዜ ከውኃ ውስጥ ወጥቷልና።

ነገር ግን እግዚአብሔር ለራሱ አንድ ወይም ሁለት ስሞች ብቻ እንዴት ሊሰጥ ይችላል? እግዚአብሔር፥ እጅግ ታላቅ ስለሆነ ይህ የማይቻል ነበር። እርሱ ኃያል ፈጣሪ፥ ሁሉን የሚያይ፥ ሁሉን የሚያውቅ፥ ሁሉን ቻይ፥ ታማኝና የማይለወጥ፥ ኃያል ፈራጅና ከፉውን ሁሉ የሚበቀል፥ አፍቃሪ፥ ደግና ጸጋ የተሞላ ፈጣሪ ነው። እርሱ በእነዚህ ሁሉና ደግሞም በሌሎች ተጨማሪ አባባሎች (ስሞች) የሚገለጥ ነው።

እስራኤላውያን፥ ስለ እርሱ ሁሉን ነገር ያውቁ ዘንድ እግዚአብሔር ለራሱ ሊሰጠው የሚችል አንድ ስም ሊኖር ይችላልን? አይኖርም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር፥ ለሙሴ እስራኤላውያንን የላከኝ «እኔ ነኝ» በላቸው አለው።

ይህ «እኔ ነኝ» የሚል ስም ሙሉ ለሙሉ ልንረዳው የማንችለው በርካታ ነገሮች አጠቃሎ ይዟል። እግዚአብሔር በእራሱ ሕልውና የሚኖር ነው ማለት ነው። «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ...» የሚለውን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የመጀመሪያ ቃል ታስታውሳላችሁን? እግዚአብሔር በመጀመሪያ ነበር። እርሱ መጀመሪያ አልነበረውም፥ መጨረሻ ሊኖረው አይችልም። በማንም ላይ ጥገኛ አልነበረም፥ ወደ ፊትም አይሆንም። ሁሉን ነገር ስለ ፈጠረ ለሁሉ ነገርና ለሁሉም ሰው ሕይወትን ሰጥቷል። ሁሉም ለሚያስፈልጋቸው ነገሮች በእርሱ ላይ ጥገኛ ናቸው። በምድር፥ በዝናብ፥ በነፋሳት፥ በወንዞች፥ በጨረቃ፥ በከዋክብትና በፀሐይ ሁሉ ላይ ተቆጣጣሪ ነው። ነገሮች ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ናቸው። እርሱ ታላቁ «እኔ ነኝ» ስለሆነ ከሁሉም የላቀ ነው።

«እኔ ነኝ» የተባለው ጌታ ሕዝቡን ነፃ ሊያወጣ እስከ ወሰነ ድረስ፥ ፈርዖንና፥ ግብፃውያን፥ እንደዚሁም ሰይጣንም እንኳ ጭምር የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይዘው ለማስቀረት አይችሉም ነበር።

ዘጸአት 3፡15-18 አንብብ።

## ሠ. እግዚአብሔር ፈርዖን ምን እንደሚያደርግ ያውቅ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው። ዘጸአት 3፡19-20 አንብብ። እግዚአብሔር የግብፁ ንጉሥ ምን ምላሽ እንደሚሰጥ ጠንቅቆ ያውቅ ነበር።

እግዚአብሔር አስተሳሰባችንን፥ ቃሎቻችንንና ተግባራችንን ከማሰባችን ወይም ከማድረጋችን በፊት ያውቃቸዋል። ከመወለዳችን አንሥቶ እስከ ዕለተ ሞታችን ድረስ የምናደርገውን ነገር ሁሉ ያውቃል። ከሞት በኋላ ያለውን ዕድላችንን እንኳ ያውቃል።

## ረ. እግዚአብሔር ለሙሴ ምልክቶችን ሰጠ።

ዘጸአት 4፡1 አንብብ። ሙሴ በግብፅ በነበረ ጊዜ ሕዝቡን ሊረዳ ሞክሮ እንዴት እንዳልተቀበሉት አስታወስ። አሁንም የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ መሪያቸውና ከባርነት ነፃ የሚያወጣቸው እንዲሆን ወደ እነርሱ እንደላከው ቢነግራቸውም እንደማያምኑት ሰጋ። ስለዚህ በእግዚአብሔር እንደተላከ ሕዝቡ እንዲያውቅ በሕዝቡ ፊት የሚያሳያቸውን ተአምራዊ ምልክቶች እግዚአብሔር ለሙሴ ሰጠው። ዘጸአት 4፡2-9 አንብብ። ነገር ግን ሙሴ ወደ ግብፅ ለመመለስ አሁንም ፈርቶ ነበርና ስለዚህ ሌላ ሰበብ ለማቅረብ ሞከረ። ዘጸአት 4፡10 አንብብ።

እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን መልስ ስሙ፤ ዘጸአት 4፡11፥ 12 አንብብ።

ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ናቸው። እርሱ ታላቁ ፈጣሪ ነው። ስለዚህ በምድር ሁሉ ላይ ንጉሥ ነው። ሰዎች ሁሉ እናንተን ጨምሮ በእርሱ ተፈጥራችኋል።

## ሰ. እግዚአብሔር ለሙሴ ረዳት ይሆን ዘንድ አሮንን ሾመ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሙሴ አንድ ተጨማሪ አሳብ ነበረው። ከእርሱ የተሻለ ሰው እንዲልክ ለእግዚአብሔር ነገረው፤ ዘጸአት 4፡13 አንብብ።

ሙሴ ክርክሩን ባለማቋረጡ እግዚአብሔር ተቆጣ፤ ነገር ግን እንዲረዳው ታላቅ ወንድሙ አሮንን እንደሚሾምለት ቃል ገባለት። ዘጸአት 4፡14-17 አንብብ።

ሸ. ሙሴ ጌታን ታዘዘ።

ዘጸአት 4፡18 አንብብ። እግዚአብሔር፥ ለሙሴ ከዚህ ቀደም ሊገድሉት የሚፈልጉት ንጉሡና ሌሎች ጭምር አሁን እንደሞቱ አረጋገጠለት። ይህን ዜና ሙሴ ወደ ግብፅ ለመሄድ በሚዘጋጅበት በዚህ በመጨረሻ ጊዜ መስማቱ በጣም እንደረዳው የማያጠራጥር ነበር። ዘጸአት 4፡19፥ 20 አንብብ።

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከባርነት ለማዳን የወሰነው ለምን ነበር?

   ሀ. እግዚአብሔር መከራቸውን ስለተመለከተና ጩኸታቸውን ስለሰማ ነበር።

   ለ. እግዚአብሔር ስለወደዳቸውና ፍቅሩንና ምሕረቱን ሊገልጥላቸው ስላቀደ ነበር።

   ሐ. እግዚአብሔር አብርሃምን ዘሩን ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርግና በእርሱ ዘር በኩል ነፃ አውጪው ወደ ዓለም እንደሚመጣ ቃል ስለገባለት ነበር።

2. ሙሴ የተመለከተው ቁጥቋጦ እየነደደ ያልተቃጠለው ለምን ነበር? ሁሉን ቻዩ አምላክ በውስጡ ስለነበር ነው።

3. በሚቃጠለው የእሳት ቁጥቋጦ የተመሰለው ማን ነበር? እስራኤላውያን ነበሩ። መከራን እየተቀበሉ ነበር። ሰይጣንና ንጉሡ ሊያጠፏቸው ፈልገው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለነበርና ይጠብቃቸው ስለነበር አልጠፉም።

4. «እኔ ነኝ» የሚለው የእግዚአብሔር ስም ትርጉም ምንድን ነው? እግዚአብሔር ሕልውናውን በራሱ ያገኘና ራሱን ችሎ የሚኖር ማለት ነው። ለሕልውናው ማንም ወይም ምንም አያስፈልገውም። እርሱ ከነገሮች ሁሉ ጅማሬ በፊት ነበር። የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ስለነበር ነገሮች ሁሉ በእርሱ ኃይል ሥር ናቸው። እርሱ ከሁሉ ነገሮች ተነጥሎ ራሱን ችሎ የሚኖር ነው።

5. እግዚአብሔር፥ ሙሴን ለግብፁ ንጉሥ ሕዝቡን እንዲለቅ እንዲያዘዘው እንዲነግረው ባደረገ ጊዜ፥ ሕዝቡን ወዲያውኑ ይለቃል ብሎ አስቦ ነበርን? አልነበረም። ንጉሡ ሕዝቡን መልቀቅ ግድ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ እንደማይለቅ ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው።

6. እግዚአብሔር፥ ሙሴን እንደላከው ሕዝቡ ያውቅ ዘንድ ምን ምልክቶች ሰጠው?

    ሀ. ሙሴ በትሩን ወደ መሬት በጣለ ጊዜ በትሯ እባብ ሆነች፤ የእባቡን ጭራ በሚይዝበት ጊዜ ደግሞ ተመልሳ በትር ሆነች።

    ለ. እጁን ወደ ብብቱ ከቶ በሚያወጣበት ጊዜ በለምጽ እንዳልተሸፈነ ሁሉ መልሶ ወደ ብብቱ ከቶ ሲያወጣው ደግሞ እንደመጀመሪያው ንጹሕ እጅ ሆነ።

7. ከሙሴ ጋር በመሆን ሙሴን ወክሎ እንዲናገር እግዚአብሔር የላከው ማንን ነበር? የሙሴን ወንድም አሮንን ነበር።

# ትምህርት 28

የትምህርት ክፍል፡- ዘጸአት 4፡27-31፤ 5፡1፥ 2፤ 6፡1-8፤ 7፡4፥ 5፥ 20፥ 21፤ 8፡5፥ 6፥ 16፥ 17፥ 24፤ 9፡6፥ 7፥ 10፥ 23-26፤ 10፡13-15፥ 21-23፥ 28፥ 29

አጠቃላይ ርእስ፡- ሙሴና አሮን ፈርዖንን ገጠሙ። ፈርዖን አልታዘዝም አለ። እግዚአብሔር በግብፅ ላይ መቅሠፍት ላከ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር፥ አሮንን ሙሴን እንዲረዳው ላከው (4፡27፥ 8)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ለ. እስራኤል፥ እግዚአብሔር ሙሴን እንደላከው አመኑ (4፡29-31)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ሐ. ፈርዖን፥ እግዚአብሔር በሙሴና በአሮን በኩል የሰጠውን ትእዛዝ አልቀበልም አለ (5፡1-2)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

መ. በፈርዖን ዓመፅ፥ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን አምላካቸው መሆኑን የማሳየት ዓላማ ነበረው (6፡1-8)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሠ. በፈርዖን ዓመፅ፥ እግዚአብሔር እውነተኛና ሕያው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ለግብፃውያን የማሳየት ዓላማ ነበረው (7፡4-5)።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ረ. እግዚአብሔር በግብፅ ላይ ዘጠኝ መቅሠፍቶችን ላከ። (7፡20፥ 21፤ 8፡5፥ 6፥ 16፥ 17፥ 24፤ 9፡6፥ 7፥ 10፥ 23-26፤ 10፡13-15፥ 21-23፥ 28፥ 29)

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለመርዳት ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

የትምህርት 27 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. እግዚአብሔር፥ አሮንን ሙሴን እንዲረዳው ላከው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር ለሙሴ የገባውን ቃል ኪዳን በመጠበቅ የግብፅ ንጉሥ እስራኤላውያንን እንዲለቅ በመጠየቅ ተግባር ላይ ሙሴን እንዲረዳ አሮንን ላከው። ዘጸአት 4፡27፥ 28 አንብብ።

ሙሴና አሮን ወደ ግብፅ ተመለሱ። ሕዝባቸውን እስራኤላውያንን በመጥራት እግዚአብሔር ለሙሴ የተናገረውን መልእክት ነገሯቸው።

ለ. እስራኤላውያን፥ እግዚአብሔር ሙሴን እንደላከው አመኑ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ዘጸአት 4፡29-31 አንብብ። እስራኤላውያን እግዚአብሔር በሙሴ በኩል የላከውን ቃሉን አመኑ። ለነፃነት ያሰሙትን ጩኸት እግዚአብሔር ስለሰማቸው እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

እስራኤላውያን በሙሴ በኩል የተላከውን የእግዚአብሔርን ቃል በማመናቸው እጅግ መልካም አደረጉ። እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል በማናምንበት ጊዜ እርሱን ውሸተኛ እናደርገዋለን። እግዚአብሔር ቃሉን የማያምኑትን ሰዎች ሊረዳ አይችልም።

ሐ. ፈርዖን፥ እግዚአብሔር በሙሴና በአሮን በኩል የሰጠውን ትእዛዝ አልቀበልም አለ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘጸአት 5፡1፥ 2 አንብብ። እግዚአብሔር ለግብፅ ንጉሥ ለመናገር በሙሴና በአሮን ተጠቀመ፤ ንጉሡ ግን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ሳይፈቅድ ቀረ።

ፈርዖን፥ ብቸኛው እውነተኛና ሕያው አምላክ የሆነውን የምድርን ሁሉ ፈጣሪ አላወቀም። ግብፃውያን እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ነገሮች ያመልኩ ነበር። በአገሪቱ ያለውን ትልቁን ወንዝ ያመልኩ ነበር። ፀሐይን፥ ጨረቃንና በርካታ የተለያዩ እንስሳትን ያመልኩ ነበር። እጅግ ብዙ የጣዖት አማልክት ነበሯቸው። በተጨማሪም ግብፃውያን ንጉሣቸው ፈርዖንን እንደ አምላክ ያመልኩት ነበር።

አብዛኛው የዓለም ሕዝቦች ከእውነተኛው የእግዚአብሔር እምነት እያወቁ ፊታቸውን ስለመለሱ ስለ እግዚአብሔር ባላቸው አመለካከት እጅግ ሞኞች ሆነው ነበር። እግዚአብሔርን ማወቅ ስላልፈለጉ ሐሰተኛ አማልክት የሆኑትን እነዚህን ነገሮች ሁሉ እንዲያመልኩ እግዚአብሔር ተዋቸው።

የእናንተና የእኔ ቀደምት አባቶች ከእውነተኛው የእግዚአብሔር እውቀት ፊታቸውን ከመለሱት መካከል የሚገኙ ናቸው። ሐሰተኛ አማልክትን እንዲያመልኩ ሰይጣን ወደዚያ መራቸው። ሰይጣን የእናንተን ቀደምት አባቶች በፈሪሃ መናፍስት ሥር ተቆጣጠራቸው።

አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ጣዖታትን ስላመለኩና የእውነተኛውን አምላክ እውቀት ስላጡ እግዚአብሔር አብርሃምን ጠራና የእስራኤል ሕዝብ አባት አደረገው። እግዚአብሔር ይህን ያደረገው በእስራኤል አማካይነት እውነተኛውን የእግዚአብሔርን እውቀት ለመጠበቅ ነበር። ስለራሱ ያለው እውነት ለቀረው የዓለም ሕዝብ በአብርሃም በኩል እንዲታወቅ ዐቀደ። ስለ እግዚአብሔር የሆነው እውነት እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በሰጠው በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል። እግዚአብሔር ለፈርዖን የግብፅ ጣዖታት ሐሰተኛ አማልክት እንደሆኑና ብቸኛውና እውነተኛው ሕያው አምላክ የአብርሃም አምላክ እንደሆነ አስተማረው፤ ፈርዖን ግን እግዚአብሔርን አልሰማም።

ከእናንተ መካከል ማንኛችሁም ብትሆኑ፥ ሞኙ የግብፁ ንጉሥ የወሰደውን ብልህነት የጐደለውን እርምጃ ዓይነት እንደማትወስዱ ተስፋ አደርጋለሁ። ፈርዖን የእውነተኛውና የሕያው አምላክ የእግዚአብሔርን ድምፅ አልሰማም አለ። የሐሰት አማልክት በነበሩት በራሱ ጣዖታት ታመነ። እነዚህ ነገሮች ብቸኛውና እውነተኛው ሕያው አምላክ በሆነው በእስራኤል አምላክ የተፈጠሩ ነበሩ።

መ. በፈርዖን ዓመፅ፥ እግዚአብሔር እውነተኛና ሕያው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ለእስራኤላውያን የማሳየት ዓላማ ነበረው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሙሴ ወደ ግብፅ በተመለሰ ጊዜ በግብፅ ይኖሩ የነበሩት የእስራኤል ትውልድ የጌታን ታላቅነትና ኃይል የሚያመለክት አንዳችም ማረጋገጫ አልተመለከቱም ነበር። ስለ ጌታ፥ የሰሙት ቀደም ሲል ለአብርሃምና ለይስሐቅ፥ ለያዕቆብና ለዮሴፍ ምን እንዳደረገ ብቻ ነበር። ስለዚህ አሁን እግዚአብሔር ለዚህ የእስራኤል ትውልድ የእርሱን ኃይልና

ጥበብ በማሳየት አሁንም ቢሆን እርሱ ኃያል እንደሆነና ለአብርሃም፥ ለይስሐቅ፥ ለያዕቆብና ለዮሴፍ ያደረገውን ነገር ለእነርሱም የሚያደርግ የእስራኤል አምላክ እንደሆነ እንዲያውቁ ለማድረግ የዚህን ክፉ ንጉሥ ዓመፃ ተጠቀመበት። ዘጸአት 6፡ 1-8 አንብብ።

ሠ. በፈርዖን ዓመፅ፥ እግዚአብሔር እውነተኛና ሕያው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ለግብፃውያን የማሳየት ዓላማ ነበረው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

የግብፅ ንጉሥ ለመታዘዝ ፈቃደኛ ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ እግዚአብሔር የተደነቀ ይመስላችኋልን? አልተደነቀም። እርሱን የሚያስደንቀው ነገር የለም። ንጉሡ ምን እንደሚናገርና ምን እንደሚያደርግ አስቀድሞ ያውቅ ነበር።

እግዚአብሔር ለሙሴ፥ የግብፅ ንጉሥ ሕዝቡን እንደማይለቅና ይህን ትዕቢተኛ ንጉሥ ለእስራኤልና ለግብፅ ኃይሉን ለመግለጥ ሊጠቀምበት ማሰቡን እንደነገረው ታስታውሳላችሁን?

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር ለግብፃውያን ደግሞ እውነተኛውና ሕያው የሆነው በምድር ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው አምላክ እርሱ እንደሆነ ሊገልጥላቸው ዐቅዶ ነበር። የሚታመኑባቸውና የሚያመልኩአቸው ጣዖታት ከእስራኤል አምላክ ሊታደጓቸው የማይችሉ እንደሆኑ ሊያሳያቸው ዐቅዶ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ፈርዖን ከእግዚአብሔር ጋር ለመዋጋት ስለ ወሰነ፥ እግዚአብሔር ለዚህ ክፉ ንጉሥና በእርሱ ላይ ለሚያምጹ ሁሉ ታላቅ ኃይሉንና የሚያመጣውን አስጨናቂ ፍርድ በማሳየት ሊጠቀምበት ወሰነ፤ ዘጸአት 7፡ 4፥ 5 አንብብ።

ይህ ለሁላችንም ማስጠንቀቂያ ሊሆነን ይገባል። የእግዚአብሔርን ነገር ችላ ብለን ወይም ከእርሱ ጋር ተዋግተን ከቅጣቱ ልናመልጥ አንችልም። ከእግዚአብሔር ጋር ተዋግቶ ከእርሱ ቅጣት ሊያመልጥ ወይም ሊያሸንፈው የሚችል ማንም የለም።

መምህር ሆይ፡- እዚህ ነጥብ ላይ በሙሴና በፈርዖን ጠንቋዮች መካከል የነበረውን ግብግብ ልትጨምር ትችላለህ። (ዘጸ. 7፡11፥ 22፤ 8፡7፥18 ተመልከት)።

ይህ ታሪክ ሰይጣን ኃይል ቢኖረውም እንኳ እግዚአብሔር እርሱ ካለው ኃይል የላቀ ብርታት ያለው መሆኑን ለማሳየት ሊጠቅም ይቻላል። ነገር ግን ከሚገባ በላይ ትኩረት አትስጠው። ከሚገባ በላይ ትኩረት በመስጠት ዋና ጉዳይ የምንለውን የእግዚአብሔርን ኃያልነትና ባሕርይ ደግሞም የሰውን ኃጢአተኝነትና ከእግዚአብሔር የመለየቱን ጉዳይ ከአእምሮአቸው ልናጠፋው እንችላለን። ማንኛቸውም ተፈጥሮአዊ ክስተቶች፥ ዕፀዋትና ግዑዝ ነገሮች ሁሉ ነፍስ አላቸው የሚለውን መሠረተ እምነት የሚከተሉ ሰዎች፥ ለሕልውናቸው ሲሉ ዘወትር ስጦታ ወይም ጉቦ በማቅረብና ደፋ ቀና በማለት መናፍስትን ለማረጋጋትና ላለማስቀየም የሞት ሽረት ትግል ያካሄዳሉ። ሕይወትን፥ ጤንነትን፥ ሰብልንና የየዕለቱ የቤተሰቦቻቸውንና የማኅበረሰባቸውን ሕይወት ከሚፈታተኑ ነገሮች ማምለጫ በመፈለግ የሚኖሩ ናቸው። የተሳሳተ አትኩሮት ካደረግን ከዚህ ቀደም ለጤንነትና ለሃብት ይመኩባቸው ለነበሩት መናፍስት እግዚአብሔርን እንደ አንዱ አማራጭ አድርገን የምናቀርብ ልንመስላቸው እንችላለን። እግዚአብሔር ከሌሎች መናፍስት ሁሉ የላቀ ስለሆነና ለሰው ልጆች መልካም መሆኑ ምንም የማያወላዳ ስለሆነ ስለ እውነተኛዎቹ የኃጢአት፥ የጽድቅና የፍርድ ጉዳዮች ሳይረዱ በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንዳላቸው ብቻ በአፍ ሊናገሩ ይችላሉ። በዚህ ዓይነት መንገድ እውነተኛ እምነት አይገኝም። ምክንያቱም እውነተኛ ንስሐ አልተደረገምና። እውነተኛ ንስሐ ማለት፥ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ኃጢአትና ስለራሳችን ባለን አመለካከት ላይ ትክክለኛ ለውጥ ማምጣት ማለት ነው።

ረ. እግዚአብሔር በግብፅ ላይ ዘጠኝ መቅሠፍቶችን ላከ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

የግብፅ ንጉሥ እስራኤላውያንን አልለቅም ስላለ እግዚአብሔር ታላቅ ኃይሉን ማሳየት ጀመረ።

በመጀመሪያ በወንዝ ያለውን ውኃ በሙሉ ወደ ደም ለወጠ፤ ዘጸአት 7፡20፥ 21 አንብብ።

ቀጥሎ የእንቁራሪት መቅሠፍት ላከ፤ ዘጸአት 8፡5፥ 6 አንብብ።

ቀጥሎ ምድሪቱን በቅማል መታ፤ ዘጸአት 8፡16፥ 17 አንብብ።

ከዚህ በኋላ ደግሞ ምድሪቱ በዝንብ መንጋ ተመታች። ዘጸአት 8፡24 አንብብ።

ከዚያም የግብፃውያን የከብት መንጋ (ፈረሶች፥ ላሞችና በሬዎች፥ በጐች፥ ግመሎችና አህዮች) በሙሉ አለቁ። ዘጸአት 9፡6፥ 7 አንብብ።

ቀጥሎ ግብፃውያን በሙሉ በቁስል ተመቱ። ዘጸአት 9፡10 አንብብ።

የእግዚአብሔር ቀጣይ ፍርድ በግብፅ ምድር ላይ አስጨናቂ የሆነ የበረዶ መዓት ማውረድ ነበር። ዘጸአት 9፡23-26 አንብብ።

ቀጥሎ የአንበጣ ጥፋት በምድሪቱ ላይ ሆነ። ዘጸአት 10፡13-15 አንብብ።

ቀጥሎ ግብፃውያን በነበሩበት ስፍራ ሁሉ እግዚአብሔር ፀሐይ ብርሃኗን እንዳትሰጥ በመከልከል ምድሪቱን በጭለማ ጋረደ። ዘጸአት 10፡21-23 አንብብ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ፈረዖንና የግብፅ ሕዝቦች ከእግዚአብሔር ከተላከው ከዚህ አስጨናቂ መቅሠፍት ራሳቸውን ለማዳን አልቻሉም።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

የእግዚአብሔር ምሕረትና ፍቅር ለእስራኤል ሕዝብ ባይበዛ ኖሮ እነርሱም በእነዚህ መቅሠፍቶች መከራቸውን ባዩ ነበር። ከእነዚህ አስጨናቂ ነገሮች አንዱም እንኳ በማናቸውም ላይ እንዳይደርስባቸው እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ጠበቃቸው። እግዚአብሔር ይህን ያደረገው በአንድ አገር ከግብፃውያን ጋር አብረው እየኖሩ ነበር። ዘጸአት 9፡6፥ 7 አንብብ።

እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን የጠበቀው ያለኃጢአት ስለነበሩ ወይም የእርሱ ጥበቃ የሚገባቸው ስለነበሩ አይደለም። የእርሱን ጥበቃ ያገኙት እርሱ አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ስለሆነ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የጠበቀበት ሌላው ምክንያት ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባውን ቃል ኪዳን ስላልዘነጋ ነበር። እግዚአብሔር አብርሃምን መረጠና ሊባርከው ዘሩንም ታላቅ ሊያደርግ እንዲሁም እርሱ አምላካቸው ሊሆን ቃል ገባላቸው። ይህን ቃል ኪዳን ከገባ በርካታ መቶ ዓመታት ያለፉና እስራኤላውያን አሁን በግብፅ በባርነት የሚኖሩ ቢሆኑም እንኳ፥ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለእርሱ የተለዩ ሕዝቦች እንደሆኑ ይቆጥርና ይናገር ነበር። ምክንያቱም እነርሱ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባለት የአብርሃም ዝርያዎች ስለነበሩ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር እስራኤልን ከመቅሠፍቶቹ የጠበቀበት ሌላው ምክንያት በምድር ሁሉ ላይ የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ የሆነው ብቸኛው እውነተኛና ሕያው አምላክ የእስራኤል አምላክ እንደሆነ የግብፅ ንጉሥ እንዲረዳ ነበር። እርሱ የወደደውንና የመረጠውን ያደርጋል።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር በግብፅ ላይ እያንዳንዱን መቅሠፍት ሲያወርድ ፈርዖን ሙሴን ያስጠራው ነበር። ነገር ግን ፈርዖን እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ለማድረግ ፈቃደኛ አልነበረም። ንጉሡ፥ እስራኤላውያን ያላቸውን ነገሮች ሁሉ ይዘው ምድሪቱን እንዲለቁ

አልፈለገም ነበር። እስራኤላውያን፥ ሚስቶቻቸውን ልጆቻቸውንና እንስሶቻቸውን ትተው ከሄዱ እንደሚመለሱ እርግጠኛ ነበር።

ፈርዖን፥ የእስራኤልን ሕዝብ ለመልቀቅ በተስማማ ቁጥር እግዚአብሔር እያንዳንዱን መቅሠፍት ከእነርሱ ላይ ያነሣ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር መቅሠፍቱን እንዳነሣ ፈርዖን ልቡን ያጠነክርና እስራኤላውያን ምድሪቱን እንዳይለቁ ሙከራ ያደርግ ነበር። ፈርዖን ይህንን ባደረገ ቁጥር ልቡ የበለጠ እየጠነከረና እየታበየ መጣ።

እግዚአብሔር የመጨረሻውን የከባድ ጨለማ መቅሠፍት ካስወገደ በኋላ ፈርዖን ትዕቢቱንና እጅግ ብልሹ ባሕርይውን ያሳይ ጀመር። ለሙሴ ምን እንዳለው አድምጡ፤ ዘጸ. 10፡28 አንብብ።

ሙሴን እግዚአብሔር ጠብቆት ባይሆን ኖሮ ንጉሡ በገደለው ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ንጉሡ ፈርዖን፥ ለሙሴ ሁለተኛ ወደ እርሱ ዘንድ ቢመጣና የእስራኤላውያንን ጉዳይ ቢያነሳበት እንደሚገድለው በመናገር ቢዝትበትም እንኳ እግዚአብሔር ነፃ እንደሚያወጣቸው ሙሴ በእምነቱ ጸና። እምነቱና ድጋፉ በእግዚአብሔር ኃይል ላይ ነበር። ሙሴ ለንጉሡ የሰጠው መልስ የሚከተለው ነበር፤ ዘጸአት 10፡29 አንብብ።

ከዚህ በኋላ ምን የሆነ ይመስላችኋል? እነዚህን መቅሠፍቶች ሁሉ ከየ በኋላ እንኳ ፈርዖን እስራኤላውያንን ለመልቀቅ እምቢ አለ። ፈርዖን በመጨረሻ ያሸነፈ ይመስላችኋልን? ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ ሊያሸንፍ የሚችል ይኖራልን? እግዚአብሔር በዚህ ትዕቢተኛ ሰው ተሸነፈን?

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ሙሴን እንደላከው እስራኤላውያን አመኑን? አዎን።
2. እግዚአብሔር የተናገረውን በማያምኑት ሰዎች ደስ ይሰኛልን? ደግሞስ ይቀበላቸዋልን? ደስ አይሰኝም፥ አይቀበላቸውምም።

እርሱን እንደ ውሸታም የሚቆጥሩትን ሁሉ እግዚአብሔር አይቀበልም፥ ደግሞም ይቀጣቸዋል።

3. ሙሴ ወደ እርሱ ዘንድ በመምጣት እስራኤላውያንን ይለቅ ዘንድ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሲነግረው የፈርዖን ምላሽ ምን ነበር? የፈርዖን መልስ «እግዚአብሔርን አላውቀውም እስራኤልንም አልለቅም» የሚል ነበር።

4. ንጉሡ የሰጠው መልስ እግዚአብሔርን አስደነቀውን? አላስደነቀውም። ፈርዖን እስራኤላውያንን ወዲያውኑ እንደማይለቅ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር።

5. የምትናገሩት፥ የምታስቡትና የምታደርጉት ነገር እግዚአብሔርን ሊያስደንቀው ይችላልን? አይችልም። እርሱ ሁሉን ነገር ከመሆኑ በፊት በሚገባ ያውቀዋል።

6. እግዚአብሔር ይህን ክፉ ንጉሥ ሊጠቀምበት ያሰበው እንዴት ነበር? እግዚአብሔር ይህን ትዕቢተኛ ንጉሥ ሊጠቀምበት ያቀደው ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር እውነተኛና ሕያው የሆነ ሁሉን ቻይ አምላክ እንደሆነ እንዲረዱ ለማድረግ ነበር።

7. እግዚአብሔር ኃይሉን ያሳየው እንዴት ነበር? እግዚአብሔር ኃይሉን ያሳየው ታላቅና አስጨናቂ የሆኑ መቅሠፍቶች ወደ ግብፅ በመላክ ነበር።

8. እነዚህ መቅሠፍቶች ምን ነበሩ? እግዚአብሔር የወንዝ ውኃዎችን ወደ ደም ለወጠ! እንቁራሪቶችን፥ ቅማሎችን፥ ዝንቦችን ወደ ምድሪቱ ላከ። የግብፃውያንን ፈረሶች፥ ላሞችና በሬዎች፥ በጎች፥ ግመሎችና አህዮችን ደመሰሰ። በተጨማሪ ቁስልን፥በረዶን፥ አንበጦችን እና ድቅድቅ ጨለማን ላከ።

9. እነዚህ መቅሠፍቶች በእስራኤላውያን ላይ ያልደረሱት ለምን ነበር?

ሀ. በእግዚአብሔር ፍቅርና ጸጋ ምክንያት፥

ለ. እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ዘሮቻቸውን ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርግና አምላካቸው እንደሚሆን የገባውን ቃል ኪዳን ስላልዘነጋ ነበር፥

ሐ. የግብፅ ንጉሥ፥ የእስራኤል አምላክ በምድር ሁሉ ላይ እውነተኛና ሕያው የሆነ ብቸኛ አምላክ እንደሆነና የሚፈልገውንና የመረጠውን የሚያደርግ መሆኑን እንዲገነዘብ ለማድረግ ነበር፥

10. እስራኤላውያን፥ እንዲህ ዓይነት ጥበቃ ሊደረግላቸው የተገቡ ነበሩን? የተገቡ አልነበሩም። ኃጢአተኞች ስለነበሩ የእግዚአብሔር ፍርድ ይገባቸው ነበር።

11. እግዚአብሔር መቅሠፍትን በላከባቸው በእያንዳንዱ ጊዜያት ፈርዖን ምን አደረገ? አሳቡን እንደቀየረና ሕዝቡን እንደሚለቅ በመናገር መቅሠፍቱ እንዲነሣ ሙሴን ጠየቀ።

12. እግዚአብሔር መቅሠፍቱን ባነሣ ጊዜ ፈርዖን ምን አደረገ? የተናገረውን አሳብ በመለወጥ ልቡን የበለጠ እያጠነከረ እስራኤልን ለመልቀቅ ሳይፈቅድ ቀረ።

13. እግዚአብሔር በዚህ ነገር ተደነቀን? አልተደነቀም። ንጉሡ ምን እንደሚያደርግ አስቀድሞ ያውቅ ነበር።

# ትምህርት 29

**የትምህርት ክፍል፡-** ዘጸአት 11፡1፥ 4-7፥ 12፡1-7፥ 12-14፥ 22፥ 28-36፥ 46፥ 51

**አጠቃላይ ርእስ፡-** የሞት መቅሠፍትን ማለፍ

**የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-**

ሀ. የእግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድ በግብፃውያን ላይ (11፡1፥ 4-7)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ለ. እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጣቸው ትእዛዛት (12፡1-7፥ 22፥ 46)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር ታማኝና፥ የማይለወጥ ነው።

1. ነቀፋ የሌለበት በግ መምረጥ ነበረባቸው።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው።

2. በጉን በማረድ ደሙን በዕቃ መቀበል ነበረባቸው።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

3. ደሙን በበሮቻቸው ጉበንና መቃን ላይ መርጨት ነበረባቸው።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

4. የበሮቻቸው ጉበንና መቃን ደም በቀቧቸው ቤቶች ውስጥ መቆየት ነበረባቸው።

5. ከበጉ የሰውነት ክፍል የትኛውንም አጥንት እንዳይሰብሩ መጠንቀቅ ነበረባቸው።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ሐ. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የገባው ቃል ኪዳን (12፡12-14)።

መ. የእስራኤላውያን እምነትና መታዘዝ (12፡28)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ሠ. የግብፃውያን የበኩር ልጆች በሙሉ ሞቱ (12፡29፥ 30)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ረ. ፈርዖን እስራኤላውያን እንዲሄዱ ፈቀደ (12፡31-36፥ 51)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

የትምህርት 28 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ።

### ሀ. የእግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድ በግብፅ ላይ።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው። እግዚአብሔር ዘጠኝ የተለያዩ መቅሠፍቶችን በዓመፀኞቹ ግብፃውያን ላይ የላከ ቢሆንም የግብፅ ንጉሥ እግዚአብሔርን ለመታዘዝና እስራኤላውያን ለመልቀቅ ሳይፈቅድ ቀረ።

ይህ ክፉ የግብፅ ንጉሥ ያሸነፈ ይመስላችኋልን? እግዚአብሔር ተስፋ በመቁረጥ እስራኤላውያንን በባርነት መኖራቸውን እንዲቀጥሉ ያደረገ ይመስላችኋልን? አላደረገም። እግዚአብሔር፥ የግብፅ ንጉሥ ልቡን እንደሚያጠነክርና እስራኤላውያንን እንደማይለቅ ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ግብፅ ከመላኩ በፊት እንኳ ይህ እንደሚሆን ለሙሴ ነግሮት ነበር።

እግዚአብሔር ሰዎች በሚያደርጉት ወይም በሚፈጽሙት ነገር ተደንቆ አያውቅም። ማንኛውም ነገር ከመሆኑ በፊት ያውቀዋል። ስለዚህ ዕቅዱን ሁሉ የሚያከናውነው እርሱ ሊያሸንፍ በሚችልበት መንገድ ነው። ሰዎች የሚሉትም ሆነ የሚያደርጉት ነገር ይህን አይለውጠውም።

እግዚአብሔር የአብርሃምን ዘሮች ነፃ ከማውጣት ተግባሩ ክፉው ንጉሥ ሊያግደው አልቻለም። ከመጨረሻው መቅሠፍት በኋላ ፈርዖን የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚለቅ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር፤ ዘጸአት 11፡1፥ 4-7 አንብብ።

## ለ. እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጣቸው ትእዛዛት።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር ለሙሴ እስራኤላውያን ለመጨረሻውና ከሁሉ ለከፋው መቅሠፍት እንዴት መዘጋጀት እንዳለባቸው ነገረው።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እስራኤላውያንም ለኃጢአታቸው ሞት የሚገባቸው ኃጢአተኞች ነበሩ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

እንደ እግዚአብሔር ምህረትና ጸጋ ባይሆን ኖሮ እስራኤላውያንም ይህን የመጨረሻ ፍርድ መከራ ከሚቀበሉት መካከል በሆኑ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባውን ቃል ኪዳን አስታወሰ። እግዚአብሔር የአብርሃም ዘሮችን እርሱ ወደ ሰጣቸው ምድር እንደሚያስገባቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር። እግዚአብሔር ይህን ለማድረግ የመረጠበት ጊዜ አሁን ነበር።

እግዚአብሔር፥ በኩሮቻቸውን ከዚህ የሞት መቅሠፍት ለመታደግ እስራኤላውያንን እንዲያደርጉ የጠየቃቸው ነገሮች የሚከተሉት ነበሩ።

1. ነቀፋ የሌለበት በግ መምረጥ ነበረባቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው።

ዘጸአት 12፡1-5 አንብብ። የእያንዳንዱ ቤተሰብ ኃላፊ በግ ወይም ፍየል ይመርጡ ዘንድ ይገባቸው ነበር። የተመረጡት እንስሳት ምንም እንከን የሌለባቸው መሆን ነበረባቸው።

በይስሐቅ ምትክ መሥዋዕት ሆኖ ሊቀርብ በቀንዱ ተጠልፎ በጫካ ውስጥ የተያዘውን በግ ታስታውሳላችሁ? በቀንዱ የተያዘው ለምን ነበር? እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ የሚያደርገውና የሚናገረው ሁሉ ፍጹም ነው። የታመመ ወይም የተጐዳ እንስሳን አይቀበልም ነበር።

2. በጉን ሊያርዱና ደሙን በዕቃ ሊቀበሉ ያስፈልጋቸው ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

ዘጸአት 12፡6 አንብብ። በጉ እግዚአብሔር እስከ ደነገገው ቀን ማለትም እስከ ወሩ አሥራ አራተኛ ቀን ይጠበቅ ዘንድ ያስፈልግ ነበር። በዚያን ቀን ምሽት በጉን ማረድ ነበረባቸው።

በጉ ሊሞትና ሕይወቱ ያለበት ደሙ ደግሞ ሊፈስ ያስፈልግ ነበር። ይህም የኃጢአት ቅጣት ሞት እንደሆነ እስራኤላውያንን የሚያስታውስ ነበር።

አዳምና ሔዋን ኃጢአትን እስኪሠሩ ድረስ በዓለም ላይ ሞት አልነበረም። ነገር ግን አዳምና ሔዋን ባለመታዘዛቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር በተለዩ ጊዜ ግን እግዚአብሔር ሥጋቸው ይሞታል አለ። የአዳምና ሔዋን ዝርያዎች በሙሉ ከእግዚአብሔር ተለይተው ኃጢአተኞች ሆነው ተወለዱ። እኔና እናንተን ጨምሮ ሰዎች ሁሉ የሥጋ ሞት መሞት ያለብን ለዚህ ነው። በዓለም ላይ ኃጢአት ባይኖር ኖሮ ሥጋዊ ሞት አይኖርም ነበር። ኃጢአት ባይኖር ኖሮ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለሰይጣን ወደ ተዘጋጀው የዘላለም እሳት መሄድ አይኖርም ነበር።

እስራኤላውያን ደሙ እንዲፈስ በጉን በሚያርዱበት ጊዜ የኃጢአት ቅጣት ሞት እንደሆነ ያስታውሱ ነበር። በይስሐቅ ፈንታ በጉ እንደ ሞተ፥ አሁንም በበኩር ልጆቻቸው ፈንታ የተመረጠውና የታረደው ነቀፋ የሌለበት በግ ሊሞት ያስፈልግ ነበር።

3. ደሙን በበሮቻቸው ጉበንና መቃን ላይ ሊረጩ ይገባ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

ዘጸአት 12፡7 አንብብ። እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን ደሙን በዕቃ እንዲይዙ ነገራቸው። ከዚያ ትንሽ የተከል ቅርንጫፍ በመውሰድ በዕቃ በተቀበሉት ደም ውስጥ በሚገባ መንከር ነበረባቸው። ቀጥሎ በዚህ የተከል ቅርንጫፍ ደሙን በሁለቱም የበሩ ማዕዘኖችና በጉበኑ ላይ ሊቀቡት ያስፈልግ ነበር። ይህ በሮቹ ደም የሚቀባው ቤት በዚያን ምሽት የበጉ ሥጋ የሚበላበት ቤት ነው። የእስራኤልን በኩር ልጆች ከእግዚአብሔር ፍርድ የሚያድናቸው በበሮቹ ላይ የተቀባው የበጎች ደም ነበር።

4. በበሮቻቸው ጉበንና መቃን ደም ባደረጉባቸው ቤቶች መቆየት ነበረባቸው።

እስከ ጠዋት ድረስ ከዚያ ቤት መውጣት አልነበረባቸውም። ዘጸአት 12፡22 አንብብ።

እስራኤላውያን የደሙ ምልክት በውጭ ሆኖ እነርሱ በቤታቸው ውስጥ ሊቆዩ ያስፈልግ ነበር። እግዚአብሔር በበኩር ልጆቻቸው ምትክ

እንዲያርዱት ባዘዘው የበጉ ደምና ሞት በስተጀርባ የመደበቅ ያህል ነበር።

## 5. ከበጉ የሰውነት ክፍል የትኛውንም አጥንት እንዳይሰብሩ መጠንቀቅ ነበረባቸው።

በጉን በሚያርዱበት ወይም በሚበሉበት ጊዜ አጥንቱን መስበር አልነበረባቸውም። ዘጸ. 12፥46 አንብብ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

እስራኤላውያን፥ ሁሉን ነገር ልክ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መንገድ ሊያደርጉ ይገባቸው ነበር። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ያው ነው። ሰዎች በራሳቸው መንገድ ራሳቸውን እንዲያድኑ አይተዋቸውም። አዳምና ሔዋን በዔድን ገነት ለራሳቸው ያዘጋጁትን ልብስ እንዳልተቀበለ ታስታውሳላችሁን? እግዚአብሔር ቃየን ያመጣውን መሥዋዕት፥ እርሱ ባዘዘው መሠረት ስላልነበረ አልተቀበለም። እግዚአብሔር ለኖኅ፥ ትልቁን መርከብ እርሱ ባዘዘው መሠረት እንዲሠራ ነገረው። አሁንም እስራኤላውያን ሁሉን ነገር እግዚአብሔር ለሙሴ ባዘዘው መሠረት ሊያደርጉ ይገባቸው ነበር።

እግዚአብሔር አሁንም ያው ነው። እርሱ አልተለወጠም። ወደ እግዚአብሔር እንደራሳችን አሳብ ወይም እንደማንኛውም ሌላ ሰው አሳብ ልንመጣ አንችልም። ወደ እግዚአብሔር ልንመጣ የምንችለው በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ ነው። እርሱ በነገረን መሠረት የማንመጣ ከሆነ ሊቀበልን ፈጽሞ አይችልም።

## ሐ. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የገባው ቃል ኪዳን

ዘጸአት 12፥12-14 አንብብ። እግዚአብሔር የበጉን ደም በበሮቻቸው መቃንና ጉበን ላይ በሚያይበት ጊዜ መቅሠፍቱ ወደ ቤታቸው ገብቶ በኩር ልጃቸውን እንዳይገድል እንደሚከለከል ቃል ገባላቸው።

## መ. የእስራኤላውያን እምነትና መታዘዝ

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ሊኖረው ያስፈልጋል።

ይህ ነገር እዚህ እናንተ ባላችሁበት አካባቢ የሚፈጸም ቢሆን ኖሮ እንዴት ይሰማችሁ ነበር? «እሺ የሚሞተው በኩር ልጅ ብቻ ነው፥ እኛ ሌሎችም ልጆች አሉን። ስለዚህ ችግር የለም» ትላላችሁን? በፍጹም ይህን እንደማትሉ አውቃለሁ። እስራኤላውያንም ይህንን አላደረጉም። እግዚአብሔር የተናገረውን በማመን ታዘዙ። ዘጸአት 12፡28 አንብብ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚመጣው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

እስራኤላውያን «ከመልካም በጎቼ አንዱን አላርድም። የታመመ አንድ በግ ስላለኝ እርሱን አርዳለሁ» ቢሉ እግዚአብሔር የታመመ በግ ደም የሚቀበል ይመስላችኋልን?

ወይም አንድ ሌላ ሰው «ይህንን ጥሩ በግ ማረድ አሳፋሪ ነው። ከምገድለው ይልቅ በበሩ አጠገብ አስሬ አስቀምጠዋለሁ። እግዚአብሔር ይህንን ያልሞተውን በግ ያያል፥ በመቅሠፍቱም ልጄን አይገድልም» ቢል እግዚአብሔር የዚያን ቤት የበኩር ልጅ የሚያልፍ ይመስላችኋልን?

አያልፍም! በጉ መሞት ነበረበት። ደሙ መፍሰስ ነበረበት። የኃጢአት ቅጣት ሞት መሆኑን መዘንጋት አልነበረባቸውም። ሁሉ ነገር እግዚአብሔር ለሙሴ በነገረው መንገድ መሆን ነበረበት።

እስራኤላውያን በቤታቸው መቃንና ጉበን ላይ ደሙን በሚያዩበት ጊዜ በኩር ልጆቻቸውንና በኩር እንስሳት አይሞቱም ብሎ በነገራቸው በእግዚአብሔር መታመን ነበረባቸው።

ሠ. የግብፃውያን የበኩር ልጆችና እንስሳቶች ሁሉ ሞቱ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

ዘጸአት 12፡29-30 አንብብ። የእያንዳንዱ ግብፃዊ ቤተሰብ የበኩር ልጅና የእያንዳንዱ እንስሳ በኩር ሞቱ። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው። ነገር ግን የኃጢአት ቅጣት ሥጋዊ ሞት ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ለዘላለም ተለይቶ በዘላለም እሳት መሰቃየት ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር በግብፅ አልፋለሁ ባለው መንገድ አለፈ። እርሱ ሁልጊዜ የተናገረውን ይፈጽማል። አደርጋለሁ በማለት በንግግር የሚዝትና ሳይፈጽመው የሚቀር አይደለም። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ሊቀጣ ሲወስን ማምለጫ መንገድ የለም።

እስራኤላውያን ጌታን በመታዘዝ በቤቶቻቸው መቃንና ጉበኖች ላይ የደም ምልክት በማድረጋቸው ከልጆቻቸውም ሆነ ከእንስሳት በኩራት አንድም የሞተ የለም።

እግዚአብሔር የተናገረውን ሁልጊዜ ይፈጽማል። የግብፃውያንን በኩራት ግን በሙሉ እንደሚገድል ተናገረ፥ አደረገውም። ደም ያየበትን ቤት ሁሉ እንደሚያልፍ ተናገረ፥ ልክ እንዳለው አደረገ። እግዚአብሔር ያለውን ነገር ሁሉ እንደሚያደርግ ልንታመንበት የምንችለው አምላክ ነው።

ረ. ፈርዖን እስራኤላውያን እንዲሄዱ ፈቀደ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸአት 12፡31-36 አንብብ። ፈርዖን ሙሴን በዚያው ምሽት ጠርቶ እስራኤላውያንን ከግብፅ ይዞ እንዲወጣ ነገረው።

ፈርዖን ከእግዚአብሔር ጋር በመዋጋት እግዚአብሔርን ተስፋ ሊያስቆርጥ የሚችል መስሎት ነበር፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ተዋግቶ ሊያሸንፍ የሚችል ማንም የለም።

እግዚአብሔር ሕዝቡን ነፃ ለማውጣት ቃል እንደገባ በሚገባ ፈጸመው።

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በሚዋጉት ሁሉ ላይ ቅጣት ይልካል። ነገር ግን በእርሱ በሚታመኑ ላይ ምሕረቱንና ሰላሙን ያደርጋል። ዘጸአት 12፡51 አንብብ።

## ጥያቄዎች

1. የግብፅ ንጉሥ እግዚአብሔርን ለማሸነፍ ችሎ ነበርን? አልቻለም።

2. ከእግዚአብሔር ጋር በመዋጋት ሊያሸንፍ የሚችል አለን? የለም።

3. እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ የላከው የመጨረሻ ፍርድ ምን ነበር? እግዚአብሔር ከግብፃውያን ልጆች በኩሮችን ከእንስሶቻቸውም ሁሉ በኩሮቻቸውን የሚገድል መቅሠፍት ላከ።

4. እግዚአብሔር፥ ለእስራኤላውያን በኩሮቻቸው እንዳይሞቱ ምን እንዲያደርጉ ነገራቸው?

   ሀ. ነቀፋ የሌለበት በግ እንዲመርጡ፥

   ለ. በጉን በማረድ ደሙን በዕቃ እንዲቀበሉ፥

   ሐ. ደሙን በበሮቻቸው ጉበንና መቃን ላይ እንዲቀቡ፥

   መ. በበሮቻቸው ጉበንና መቃን ላይ ደም በተረጨባቸው ቤቶች ውስጥ እንዲቆዩ፥

   ሠ. ከበጉ የሰውነት ክፍል ምንም አጥንት እንዳይሰብሩ ይጠንቀቁ ዘንድ ነበር የነገራቸው።

5. እስራኤላውያን፥ እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ነገሮች በትክክል ባይፈጽሙ ኖሮ ምን ሊሆኑ ይችሉ ነበር? በኩር ልጆቻቸው በሙሉ ያልቁ ነበር።

6. ወደ እግዚአብሔር በመምጣት ተቀባይነት ልናገኝ የምንችልበትን ሁኔታ ሊነግረን የሚችል ማን ነው? እግዚአብሔር ብቻ ነው።

7. እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ቤተሰብ በኩር እገድላለሁ ባለበት ሌሊት በግብፃውያን ቤት ምን ሆነ? አስቀድሞ እንደተናገረው በኩር ልጆቻቸው በሙሉ አለቁ።

8. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የገባው ቃል ኪዳን ምን ነበር? በበሮቻቸው ጉበንና መቃን ላይ ደሙን ባየ ጊዜ የሞት መቅሠፍቱ እንዳይነካቸው እንደሚያደርግ ነበር።

9. በእስራኤላውያን ላይ ምን ሆነ? ልጆቻቸው በሙሉ ምንም ክፉ ነገር አልደረሰባቸውም። አንዳቸውም አልሞቱም።

10. የእስራኤል ልጆች ለምን አልሞቱም?

ሀ. እግዚአብሔር የነገራቸውን በመስማት በቤቶቻቸው ላይ ደም ስላደርጉ፥

ለ. እግዚአብሔር ታማኝ ቃሉን ጠባቂ ስለሆነ ቃል ኪዳኑን በመጠበቅ አለፋቸው።

11. እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ ያደርገዋልን? አዎን ኃጢአትን እቀጣለሁ ካለ ሁልጊዜ ያደርገዋል። እንደዚሁም እግዚአብሔር ለሚታመኑት ሁሉ የተስፋ ቃል ኪዳን ከሰጠ ሁልጊዜ የገባውን ቃል ኪዳን ይፈጽማል።

12. የግብፃውያን በኩሮች በሙሉ ከሞቱ በኋላ ንጉሥ ፈርዖን ሙሴን ምን አለው? እስራኤላውያንን ይዘህ ከግብፅ ውጣ አለው።

## ትምህርት 30

የትምህርት ክፍል፡- ዘጸአት 13፡21፥ 22፤ 14፡1-31

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር እስራኤልን በቀይ ባሕር ታደጋቸው።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን በደመና መራቸው፤ (13፡21፥ 22)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ለ. እስራኤላውያን ከቀይ ባሕር አጠገብ ሰፈሩ፤ (14፡1-3)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ሐ. ፈርዖን፥ እስራኤላውያንን እንደገና ባሪያ ለማድረግ ወሰነ፤ (14፡4-9)።

. ሰይጣን ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው። ሰውን ይጠላል።

መ. እስራኤላውያን ስለፈሩ ሙሴን ጥፋተኛ አደረጉ፤ (14፡10-14)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለመርዳት ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሠ. እግዚአብሔር ባሕሩን ከፈለ፤ (154፡15-18፥ 21)።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ረ. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በባሕሩ መካከል መራቸው፤ (14፡19-25)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ሰ. እግዚአብሔር የግብፅን ሠራዊት በባሕሩ አሰጠመ፤ (14፡26-31)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

የትምህርት 29 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ።

መምህር ሆይ፡- ታሪኩ የተፈጸመበትን ቦታ በካርታ ላይ አሳይ። ይህ እውነተኛ ታሪክ መሆኑን ለአዳማጮችህ በሚገባ ንገራቸው።

### ሀ. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በደመና መራቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነፃ ካወጣቸው በኋላ ለቀደምት አባታቸው ለአብርሃም ቃል ኪዳን ወደገባው ምድር ይመራቸው ጀመር። ዘጸአት 13፡21፥ 22 ተመልከት።

እግዚአብሔር፥ ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ተስፋ ወደ ሰጠው ወደ ከነዓን ምድር ጉዞአቸውን ጀመሩ። ይህም ያዕቆብና የዮሴፍ ወንድሞች ከዮሴፍ ጋር ለመሆን ወደ ግብፅ ከመምጣታቸው በፊት ይኖሩበት የነበረው አገር ነው።

እስራኤላውያን መጀመሪያ ወደ ግብፅ ሲወርዱ ቁጥራቸው ሰባ ያህል ነበር። አሁን ግን ምናልባት ወደ ሁለት ሚሊዮን ተኩል ደርሰው ይሆናል።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር፥ አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

እግዚአብሔር፥ እርሱ ወደሚፈልግበት ስፍራ እንዲሄዱ በደመና መራቸው። የሚመራቸውን ደመና ሁልጊዜ በፊታቸው ያደርግ ነበር። ይወዳቸው ስለነበር ተገቢውን እንክብካቤ ያደርግላቸው ነበር። እግዚአብሔር ባይመራቸው ኖሮ አቅጣጫቸውን ስተው በበረሃ ያልቁ ነበር።

እስራኤላውያን የአብርሃም ዝርያዎች ናቸው። እግዚአብሔር፥ ለአብርሃም በገባው ቃል ኪዳን ከዝርያዎቹ አንዱ የዓለም አዳኝ እንደሚሆን ነግሮት ነበር። ታላቁ አዳኝ ወደዚህች ዓለም መምጣት እንዲችል እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እየጠበቀ ነበር።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር እስራኤልን የጠበቀበት ሌላው ምክንያት ቃሉን ለዓለም እንዲያካፍሉ ለእነርሱ አደራ ስጥቷቸው ስለነበር ነው። እናንተም ስለ እግዚአብሔር በመማር እርሱን ወደማወቅ እንድትመጡ አሁን እያነበብነው ያለነው የእግዚአብሔር ቃል ለእስራኤላውያን ተሰጠ።

## ለ. እስራኤላውያን ከቀይ ባሕር አጠገብ ሰፈሩ።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸአት 14፡1-3 አንብብ። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እስከ ባሕሩ አጠገብ መራቸውና በዚያ ሰፈሩ። ይህ ባሕር ቀይ ባሕር በመባል ይታወቃል። እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን ወደዚህ ስፍራ ያመጣቸው ለእነርሱና ለግብፃውያን እርሱ ሁሉን ቻይና ሉዓላዊ አምላክ መሆኑን በድጋሚ ሊያሳያቸው ዐቅዶ ነበር። እርሱ የሁሉ የበላይ ነው።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ፈርዖን እያሰበ የነበረውንና ማድረግ ያቀደውን ለእግዚአብሔር ማን ነገረው?

ጠላቶቻችሁ ሊያጠቋችሁ ቢፈልጉ ዕቅዶቻቸውን ለእናንተ ይነግራሉን? ሊያደርጉ ያቀዱትን ነገር እንዴት ለማወቅ ትችላላችሁ?

እግዚአብሔር፥ ሰዎች ሊያደርጉት ያቀዱትን ነገር ለማወቅ ሰላዮች መላክ ያስፈልገዋልን? በጭራሽ አያስፈልገውም። እግዚአብሔር በባሕሩ አጠገብ ከእስራኤላውያን ጋር ነበር፥ ነገር ግን በግብፅም ነበር፥ ፈርዖን ሊያደርግ ያቀደውን ነገር ያውቅ ነበር።

## ሐ. ፈርዖን እስራኤላውያንን እንደገና ባሪያ ለማድረግ ወሰነ።

ዋና አሳብ:- ሰይጣን ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው። ሰዎችን ይጠላል።

ፈርዖን የሚመራው በሰይጣን ነበር። ተስፋ ቆርጦ እስራኤላውያንን ለመልቀቅ አልወሰነም ነበር። ዕቅዱ ከኋላቸው ተከትሎ ሊመልሳቸውና በባርነት ሊያቆያቸው ነበር። ዘጸአት 14:4-9።

## መ. እስራኤላውያን ስለፈሩ ሙሴን ጥፋተኛ አደረጉ።

ዋና አሳብ:- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እስራኤላውያን፥ ግብፃውያን ከኋላቸው እንደሚከተሏቸው በተመለከቱ ጊዜ ምን ያደረጉ ይመስላችኋል? በእግዚአብሔር በመታመን ነፃ እንዲያወጣቸው እግዚአብሔርን ጠሩን?

ዘጸአት 14:10-12 አንብብ። እስራኤላውያን እግዚአብሔር፥ በግብፅ ያደረጋቸውን ትላልቅና አስደናቂ ነገሮች ቢያዩም እንኳ አሁንም በእግዚአብሔር አልታመኑም ነበር።

ዋና አሳብ:- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል። ሙሴ ግን በእግዚአብሔር በመታመን እስራኤላውያን በእግዚአብሔር እንዲያምኑ ነገራቸው። ዘጸአት 14:13፥ 14 አንብብ።

እናንተ ከእስራኤላውያን የተለያችሁ ናችሁን? ሰይጣን፥ መናፍስትና ምናልባት አንዳንድ ሰዎች እንኳ በእግዚአብሔር

እንድታምኑ ባይፈልጉ እንኳ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት በእርሱ ብቻ ልትደገፉ ፈቃደኞች ናችሁን?

መምህር ሆይ፡- ለእንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ከአድማጮችህ መልስ አትፈልግ ወይም አትጠብቅ። ነገር ግን አሳባቸውን ለመግለጽ የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ ፍቀድላቸው።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

እስራኤላውያን ኃጢአትን አድርገው በእግዚአብሔር ሳይታመኑ ቢቀሩም እንኳ እግዚአብሔር ምሕረትን የተሞላ ስለሆነ ነፃ ሊያወጣቸው ዐቀደ። ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት አይችሉም ነበር። ባሕሩ ከፊት ለፊታቸው ነበር። ዙሪያቸውን በተራራ ተከበው ነበር። ጠላቶቻቸው ደግሞ ከኋላቸው እየደረሱባቸው ነበር። «ሊያድናቸው የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነበር»።

እግዚአብሔር፥ አዳምና ሔዋንን ከዔድን ገነት ውጭ ባስቀመጣቸው ጊዜ ወደ ዔድን ገነት የሚመለሱበት ምንም መንገድ አልነበረም። በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን ነገር ሊያስተካክሉ የሚችሉበት አንዳችም መንገድ አልነበራቸውም። እንደገና በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ለማድረግ መንገድን መክፈት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነበር። ለአቤል፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ መንገድ የከፈተለት እግዚአብሔር ነበር። ኖኅንና ቤተሰቡን ከጥፋት ውኃ ሊያድን የቻለ እግዚአብሔር ብቻ ነበር። ይስሐቅ በመሠዊያው ላይ ታስሮ በተጋደመበትና አባቱ ሊያርደው ቢላዋን ባነሣበት ጊዜ ሊያድነው የቻለው እግዚአብሔር ብቻ ነበር። እግዚአብሔር መንገድ ሊሰጣቸው ባይፈቅድ ኖሮ እስራኤላውያን በኩር ልጆቻቸውን በሕይወት ለማዳን ባልቻሉ ነበር። በተመሳሳይ መንገድ እስራኤላውያን እግዚአብሔር መንገድ ባያዘጋጅላቸው ኖሮ ከግብፃውያን እጅ ሊያመልጡ አይችሉም ነበር።

ለእናንተም ቢሆን እንደዚህ ነው። ከእግዚአብሔር ቁጣ ለማምለጥ መንገድ ለማበጀት አትችሉም። በምታደርጉት ነገር በእናንተና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነት ልታስተካክሉ አትችሉም። ከዘላለም ቅጣት ሊያድናችሁ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ስለሚያድንበት መንገድ እንድትማሩ በጥንቃቄ አዳምጡ።

## ሠ. እግዚአብሔር ባሕሩን ከፈለ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ዘጸአት 14፡15፥16 አንብብ። እግዚአብሔር ባሕርን ፈጠረ፤ ስለዚህ ባሕርን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ይችላል። በመጀመሪያ ምድር በሙሉ በውኃ ተሸፍኖ ነበር። ደረቅ መሬት ይገኝ ዘንድ እግዚአብሔር ውኃውን እንዴት እንዳንቀሳቀሰ አስታውሱ። በመጀመሪያ ደረቅ መሬት ለማስገኘት ውኃውን ያንቀሳቀሰው ጌታ አሁንም አልተለወጠም። ባሕሩን በማዘዝና ለሁለት በመክፈል በመካከሉም ደረቅ መሬት እንዲሆን በማድረግ ሕዝቡ እንዲሻገሩ አደረገ። እግዚአብሔር ይህን ሊያደርግ የቻለው በምድር ሁሉ ላይ የበላይ ተቆጣጣሪ ስለሆነ ነው።

እስራኤላውያን ባሕሩን ተሻግረው እንዲሄዱ ባሕሩን ለመክፈል ለእግዚአብሔር አስቸጋሪ ነገር አልነበረም። እርሱ ሁሉን ቻይ ነው። ለእርሱ የሚሳነው ነገር የለም።

ዘጸአት 14፡17፥ 18፥ 21 አንብብ። እግዚአብሔር፥ ግብፃውያን እስራኤላውያንን ተከትለው ወደ ባሕሩ እንደሚመጡ ያውቅ ነበር። ስለዚህ የፈርዖንን ሠራዊት በባሕሩ ውስጥ ለመደምሰስ እግዚአብሔር ዐቅዶ ነበር።

## ረ. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በባሕሩ ደረቅ መሬት ላይ መራቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘጸአት 14፡19-11 አንብብ። እግዚአብሔር ሕዝቡን አልተወም። ለአብርሃም ተስፋ ወደገባው ምድር ከግብፅ በሰላም እንደሚመራቸው

ቃል ገብቶ ነበር። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በባሕር ውስጥ ባበጀው ደረቅ መሬት ላይ መራቸው።

እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን እንዲመራ ይጠቀምበት የነበረውን ደመና በእነርሱና በግብፃውያን መካከል አደረገው። ደመናው ከእስራኤላውያን በስተጀርባ ሆኖ ከፊት ለፊት እጅግ ደማቅና እንደ ፀሐይ አብረቅራቂ ብርሃን ያለው ነበር። ለእስራኤላውያን የሚሄዱበትን ስፍራ እንዲያዩ ያበራላቸው ነበር። በግብፃውያን ፊት ግን ደመናው ጨለማ ነበር። በፊት ለፊታቸው የሚታየው ጨለማ ነበር። ይህም ሆኖ እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው ወስኖ ስለነበር ግብፃውያን እስራኤላውያንን መከታተል አላቆሙም ነበር። ዘጸ. 14፡23-25 አንብብ።

## ሰ. እግዚአብሔር የግብፅን ሠራዊት በባሕሩ አሰጠመ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸአት 14፡26-29 አንብብ። እግዚአብሔር የግብፅን ሠራዊት በባሕሩ ውስጥ አሰጠመው።

ከእግዚአብሔር ጋር ተዋግቶ ስኬታማ ሊሆን የሚችል የለም። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሚዋጉትን ሁሉ ይቀጣል። ነገር ግን ቃሉን የሚያምኑትንና እርሱ በተናገረው መንገድ ወደ እርሱ ለሚመጡት ሁሉ ምሕረት የሞላበት አዳኝ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው። እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘጸአት 14፡30 አንብብ። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሙሉ ጠበቀ። ከመካከላቸው አንድም ሰው አልሰመጠም። ግብፃውያን የያዟቸው ሰዎችም አልነበሩም። እግዚአብሔር ስለሚወዳቸውና ቃል ኪዳን ስለገባላቸው አዳናቸው።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ዘጸአት 14፡31 አንብብ። እስራኤላውያን እግዚአብሔር ያደረጋቸውን ታላላቅ ነገሮች በተመለከቱ ጊዜ በእርሱ አመኑ።

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን የምናምነው እግዚአብሔር አንዳንድ ትላልቅና አስደናቂ ነገሮችን ሲያደርግ ካየን ብቻ ነው ይላሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር እኔን እንድታምኑ ታላላቅ ተአምራትን አደርጋለሁ የሚል ቃል ኪዳን አልሰጠንም። እግዚአብሔር ቃሉን ሰጥቶናል፤ ስለዚህ ቃሉን እንድናምንና በእርሱ እንድንደገፍ ይነግረናል። በቃሉ የተጻፈውን ልናምን ፈቃደኞች ካልሆንን ከእግዚአብሔር ተለይተን በመሞት ወደ ዘላለም ቅጣት እንሄዳለን።

## ጥያቄዎች

1. እስራኤላውያን ወደየት መሄድ እንዳለባቸው እግዚአብሔር የሚመራቸው እንዴት ነበር? እግዚአብሔር ቀን በደመና ማታ ደግሞ በእሳት አምድ ይመራቸው ነበር።

2. እስራኤላውያን የሚሄዱት ወደየት ነበር? እግዚአብሔር፤ ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ተስፋ ወደገባው ወደ ከነዓን ምድር ነበር።

3. እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ባሕሩ ጫፍ የወሰደው ለምን ነበር? እግዚአብሔር ፈርዖን እንደሚከተላቸው ያውቅ ነበርና እንደገና ለእስራኤላውያንና ለግብፃውያን እርሱ ሁሉን ቻይና ሉዓላዊ አምላክ መሆኑን ለማሳየት ስለፈለገ ነበር።

4. እግዚአብሔር እስራኤልን የጠበቀው ለምን ነበር?

   ሀ. እርሱ አፍቃሪና ምሕረትን የተሞላ ስለሆነ ነው፥

   ለ. ከዚህ ዘር ታላቁ የኃጢአተኞች አዳኝ ስለሚወጣ ነበር፥

   ሐ. ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባቸው የተስፋ ቃሎች ስለነበሩ ነው፥

   መ. እግዚአብሔር ለዓለም ሁሉ የሆነውን ቃሉን በእስራኤል በኩል ስለሚሰጥ ነበር።

5. እስራኤላውያን የፈርዖን ሠራዊት ከኋላቸው እየተከተላቸው ሲመጣ ምን አደረጉ? በሙሴ ላይ በማጉረምረም በግብፅ ቢተዋቸው ይሻል እንደነበር ተናገሩት።

6. እስራኤላውያን ራሳቸውን የሚያድኑበት መንገድ ነበራቸውን? አልነበራቸውም።

7. ማድረግ የነበረባቸው ምን ነበር? እግዚአብሔርን መጥራትና እንደሚታደጋቸው በእርሱ መታመን ነበረባቸው።

8. ለእግዚአብሔር ባሕሩን መክፈል እጅግ ቀላል የነበረው ለምንድን ነው?

   ሀ. ምክንያቱም፥ ባሕርን የፈጠረ እርሱ ስለሆነ ነው።

   ለ. ምክንያቱም፥ በመጀመሪያ እግዚአብሔር በውኃና በምድር ላይ ኃይል ነበረው። አሁንም አልተለወጠም። ባሕሩ ወደኋላው እንዲሰበሰብ በማድረግ ሕዝቡ በደረቅ መሬት ላይ እንዲሻገር አደረገ።

   ሐ. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለሆነ ለእርሱ የሚሳነው ነገር የለም።

9. እስራኤላውያን በባሕሩ መካከል በደረቅ መሬት በተሻገሩበት ጊዜ ከግብፃውያን ያመልጡ ዘንድ እግዚአብሔር ምን አደረገ? እግዚአብሔር ደመናውን በመካከላቸው አደረገው። በመካከላቸው የተጋረደው ደመና ይመራቸው ዘንድ በእስራኤላውያን በኩል ደማቅና አብረቅራቂ ነበር፤ በግብፃውያን በኩል ግን ጨለማ ነበር።

10. ግብፃውያን ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያመልጡ ያልቻሉት ለምን ነበር? እግዚአብሔር ከሁሉም የላቀ ስለሆነ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ተዋግቶ ሊያሸንፍ የሚችል የለም። እርሱ ሁሉን ቻይ ነው።

11. በኃጢአታችሁ ከሚመጣው የእግዚአብሔር ቅጣት እራሳችሁን በራሳችሁ በማዳን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ትችላላችሁን? አትችሉም።

## ትምህርት 31

የትምህርት ክፍል፡- ዘጸአት 16፡ 1-3፥ 11-16፥ 35፥ 17፡ 1-6

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን መናና ውኃን ሰጣቸው።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እስራኤላውያን አጉረመረሙ (16፡ 1-3)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ለ. እግዚአብሔር ምግብን እንደሚሰጣቸው ቃል ገባላቸው (16፡ 11፥ 12)።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሐ. እግዚአብሔር ምግብን ሰጣቸው (16፡ 13-16፥ 35)።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

መ. እስራኤላውያን እንደገና በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ (17፡ 1-4)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል

ሠ. እግዚአብሔር ለሙሴ ምን ማድረግ እንዳለበት ነገረው (17፡ 5፥ 6)።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ረ. እግዚአብሔር ውኃን ሰጣቸው (17፡ 6)

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

የትምህርት 30 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

### ሀ. እስራኤላውያን አጉረመረሙ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘጸአት 16፡1-3 አንብብ። እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን ባሕሩን በመክፈል ከግብፃውያን ነፃ ቢያወጣቸውና በደረቅ መሬት በሰላም ቢመራቸውም በእግዚአብሔር ላይ አልተደገፉም። በሙሴና በአሮን ላይ በማጉረምረም ጮኹ። ከማጉረምረም ይልቅ እግዚአብሔር ምግብ እንደሚሰጣቸው በማመን በእርሱ ላይ መታመን ነበረባቸው። የነበሩት በምድረ በዳ እንደመሆኑ ምግብ ከየትም ማግኘት አይችሉም ነበር። ሙሴም ሊሰጣቸው አይችልም ነበር።

መምህር ሆይ፡- ምድረ በዳ ምን እንደሚመስል ለመግለጽ ጥቂት ጊዜ ውሰድ። ካርታህን በመጠቀም ሥዕሎችን አሳይ። እስራኤላውያንም ሆኑ ሙሴም ጭምር ለራሳቸው የሆነ ምግብ ሊያዘጋጁ ያለመቻላቸውን አዳማጮችህ መረዳታቸው በጣም አስፈላጊ ነው። ይህንን ሲገነዘቡ እስራኤላውያንን ሊያድን የሚችል እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ይረዳሉ። ከእነዚህ ታሪኮች ለአዳማጮቻችን ለማስተማር የምንፈልገው ደኅንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ ነው፤ (ዮናስ 2፡9)። ብሉይ ኪዳንን በምናስተምርበት ጊዜ ዓላማችን ሰው ለደኅንነት ራሱን መርዳት የማይቻል መሆኑንና ስለ እግዚአብሔር አዳኝነት መግለጽ ነው። በዚህ ሁኔታ ወንጌልን በምናስተምርበት ጊዜ አድማጮቻችን ፊታቸውን የሚመልሱት ወደ ክርስቶስ ብቻ ይሆናል።

### ለ. እግዚአብሔር ምግብን እንደሚሰጣቸው ቃል ገባላቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ዘጸአት 16፡11፥ 12 አንብብ። ሙሴም ሆነ ሕዝቡ ምግብ ማግኘት ባይችሉም እግዚአብሔር ግን ሊመግባቸው ይችል ነበር። ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው። ከእግዚአብሔር ምንም ማግኘት የሚገባቸው ባይሆኑም እንኳ በምሕረቱ እግዚአብሔር ምግብን እንደሚሰጣቸው ቃል ገባላቸው።

የእግዚአብሔር ምሕረት የሚገባው ማንም የለም። ሁላችንም የዘላለም ቅጣት ይገባናል።

## ሐ. እግዚአብሔር ምግብን ሰጣቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ዘጸአት 16፡13-16 አንብብ። እግዚአብሔር ረዳት የሌላቸውን ይረዳል። ማምለጫ መንገድ የሌላቸውን ነፃ ያወጣል። አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን በሠሩና ከእርሱ በተለዩ ጊዜ እግዚአብሔር ነፃ የሚያወጣቸውን አዳኝ እንደሚልክላቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር። ለራሳቸው የሚያገለድሙት የቅጠል ሽፋን ለመሥራት ቢሞክሩም እግዚአብሔር ግን የእንስሳትን ቆዳዎች አዘጋጀላቸው። እግዚአብሔር በምሕረቱ የአቤልን መሥዋዕት ተቀበለ። እግዚአብሔር ኖኅና ቤተሰቡን ከጥፋት ውኃ አዳናቸው። እግዚአብሔር አብርሃምን ከጣዖት አምልኮ ጠራው፥ በዮሴፍ አማካይነት የያዕቆብን ቤተሰብ ከራብ አደጋ ጠበቃቸው፥ እስራኤላውያንን ከግብፅ ነፃ ለማውጣት ሙሴን ጠራው፥ በደረቅ መሬት ይሻገሩ ዘንድ ባሕሩን ከፈለላቸው። አሁን ደግሞ ለእስራኤላውያን ምግብ እንደሚሰጣቸው ቃል ገባላቸው። ከእነዚህ ሰዎች መካከል እግዚአብሔር ያደረገላቸው ነገር የሚገባቸው ሰዎች ፈጽሞ አልነበሩም። ሁሉንም ያደረገው በምሕረቱ ምክንያት ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘጸአት 16፡35 አንብብ። እስራኤላውያን በምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ በሙሉ የሚያስፈልጋቸውን ምግብ እግዚአብሔር በታማኝነት ሰጣቸው። ይህን ለማድረግ ያቃተው ወቅት ፈጽሞ አልነበረም።

እግዚአብሔር ታማኝ ነው። በቃሉ የተናገረውን ሁሉ ለማድረግ ታማኝ ነው።

## መ. እስራኤላውያን እንደገና በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ሰው ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እስራኤላውያን እግዚአብሔር ምግብን ስለሰጣቸው ቢያመሰግኑትም እንኳ ወዲያውኑ ታላቅ ኃይሉን ዘንግተው ማጉረምረም ጀመሩ። በዚህ ጊዜ ምን እንደተፈጸመ አድምጡ። ዘጸአት 17፡1-4 አንብብ።

ለራሳቸው የሚሆን ውኃ ያላገኙት ለምን ነበር? አዎን! የነበሩበት ስፍራ ምድረ በዳ ነበር። ውኃ የሚገኝበት ምንም ስፍራ አልነበረም። ውኃ ካልተገኘ ደግሞ ሁሉም ያልቁ ነበር።

ሊረዳቸው የሚችል ማን ብቻ ነው? አዎን! ጌታ ብቻ ነበር። እግዚአብሔር በምድረ በዳ እንኳ ውኃ ሊሰጣቸው ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁን? በዚያ ደረቅ በረሃማ ስፍራ እግዚአብሔር ውኃ ከየት ሊያገኝ ይችላል?

እግዚአብሔር የረዳቸው ወይስ እንዲሞቱ የተዋቸው ይመስላችኋል?

መምህር ሆይ፡- ለሰዎቹ መልስ እንዲሰጡ ጊዜ ስጣቸው። መልሳቸው ስለ እግዚአብሔር ኃያልነትና መለኮታዊ ባሕርይ ያላቸውን አመለካከት ወይም መረዳት ይገልጥልሃል።

## ሠ. እግዚአብሔር ለሙሴ ምን ማድረግ እንዳለበት ነገረው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን በውኃ ጥም እንዲሞቱ አልተዋቸውም።

እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን በምድረ በዳ በውኃ ጥም እንዳያልቁ ያልተዋቸው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር ውኃ

ሊሰጣቸው የሚገባቸው ነበሩን? አልነበሩም። እግዚአብሔር ውኃ የሰጣቸው እርሱ አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ስለሆነ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ዘጸአት 17፡5፥ 6 አንብብ። እግዚአብሔር ሙሴን ዓለቱን በበትሩ እንዲመታው አዘዘው። እግዚአብሔር ከዓለቱ ውኃን እንደሚያወጣ ተስፋ ሰጥቶት ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ሙሴም እግዚአብሔር ያዘዘውን ሊያደርገው ይገባ ነበር። ፈታኝ ሁኔታዎች በሚገጥሟቸው ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ምን ማድረግ እናዳለባቸው ይነግራቸው ነበር።

ከኃጢአታችን ከሰይጣን ኃይልና ከዘላለም ቅጣት የምናመልጥበትን መንገድ ራሳችን እንድናበጅ እግዚአብሔር ጉዳዩን ለራሳችን አይተወውም። እግዚአብሔር በራሳቸው መታመንን ትተው በእርሱ ብቻ የሚደገፉ ሰዎችን የሚያድን ነው። ኃጢአተኞች የሚያመልጡበትን መንገድ እርሱ ያዘጋጃል።

ረ. እግዚአብሔር ውኃን ሰጣቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

ዘጸአት 17፡6። ሙሴ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ዓለቱን መታው። በዚያን ጊዜ ከዓለቱ ትልቅ የጅረት ውኃ ወዲያውኑ ፈለቀ። የወጣው ውኃ ለእስራኤላውያን ሁሉና ለእንስሳቱ በቂ ነበር። በምድረ በዳ ከዓለት ውኃ ሊሰጥ የሚችል ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ምግብና ውኃን ሰጣቸው። ይህንንም ሆነ ማናቸውንም ነገሮች ከእግዚአብሔር ለማግኘት የሚገባቸው ግን አልነበሩም። ይህን ምግብና ውኃ ለማግኘት አንዳችም የሠሩት ሥራ አልነበረም። እግዚአብሔርም በምላሹ የጠየቃቸው ነገርም የለም። ምግብና ውኃ የሰጣቸው እርሱ አፍቃሪና ምሕረትን የተሞላ ስለሆነ ነው።

የእግዚአብሔር ፍቅርና ምሕረት የሚገባው ሰው ማንም የለም። በምናደርጋቸው ነገሮች ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት

አንችልም። እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች የሚያደርገው ይቅርታ እንደ ልዩ ስጦታ ነው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በታማኝነት በመጠበቅ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ሰጣቸው። እግዚአብሔር የአብርሃምን ዝርያዎች እንደሚባርክ ተስፋ ሰጥቶ ነበር።

እግዚአብሔር የተናገረውን ማንኛውንም ነገር ሁልጊዜ ይፈጽማል።

## ጥያቄዎች

1. እስራኤላውያን በምድረ በዳ በሚጓዙበት ጊዜ ምን አዲስ ችግር ገጠማቸው? ምንም ምግብ ስላልነበረ የምግብ እጦት ችግር ገጠማቸው።
2. እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ታላላቅ ነገሮች ሁሉ አስታውሰው በእርሱ ታመኑን? በጭራሽ! ይልቁኑ ማጉረምረምና በሙሴና በአሮን ላይ መጮህ ጀመሩ።
3. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ምግብ ሊሰጣቸው ይገባ ነበርን? አይገባም ነበር።
4. የእግዚአብሔርን ፍቅር ማግኘት ወይም ከዘላለም ቅጣት መዳን የሚገባው ሰው አለን? የለም። ሁላችንም የእግዚአብሔር ቅጣት ይገባናል።
5. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣቸው ምግብ ምን ነበር? በመጀመሪያ ድርጭቶች ሰጣቸው፣ ከዚያም በየጠዋቱ መናን ይሰጣቸው ነበር።
6. እስራኤላውያን ውኃን ማግኘት ያልቻሉት ለምን ነበር? በምድረ በዳ ስለነበሩ ነው።
7. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ውኃ ይሰጣቸው ዘንድ ሙሴን ምን አድርግ አለው? ዓለቱን በበትርህ ምታ አለው።
8. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ነፃ ሲያወጣቸው ሊያደርጓቸው የሚፈልጓቸውን ነገሮች እነርሱ በሚፈልጉት መንገድ እንዲያደርጉ ይፈቅድላቸው ነበርን? አልነበረም። እግዚአብሔር ራሱ በሚፈልገው መንገድ እንዲያደርጉ ይፈልግ ነበር።

# ትምህርት 32

የትምህርት ክፍል:- ዘጸአት 19:1-25

አጠቃላይ ርእስ:- ለአሥርቱ ሕግጋት መሰጠት የተደረገ ዝግጅት።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች:-

ሀ. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደ ሲና ተራራ አመጣቸው (19:1-4)።

. እግዚአብሔር የሁሉም በላይና ሉዓላዊ ነው።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ለ. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የገባው ቃል ኪዳን (19:5፥ 6)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ሐ. እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር የገቡት ቃል ኪዳን (19:7፥ 8)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

መ. ለእግዚአብሔር መገለጥ በተራራው ላይ የተደረገ ዝግጅት (19:9-15)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ሠ. እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ሆኖ ለእስራኤላውያን ተናገረ (19:16-19)።

. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

ረ. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደ ተራራው እንዳይሄዱ እንደገና አስጠንቀቃቸው (19፡20-25)።

- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።
- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።
- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።
- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

የትምህርት 31 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ።

መምህር ሆይ፡- በዚህ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል የእግዚአብሔር ጽድቅና ቅድስና አስፈሪ ከሆነው ቁጣውና እርግጠኛ ከሆነው ፍርዱ ጋር በግልጽ ትኩረት ተደርጐበት ቀርቧል። በሲና ተራራ ላይ ሰዎችና እንስሳት እንዳይደርሱበት የተከለለው ስፍራ የእግዚአብሔርን ቅድስናና፥ የሰውን ኃጢአተኛነት ከማመልከቱም፥ ኃጢአተኛ የሆነው ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ ያለመቻሉንና ከነኃጢአታቸው ወደ እግዚአብሔር ሕልውና ለመምጣት በሚያስቡ ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ በእርግጥ እንደሚደርስ የሚያሳይ ነው።

አሥርቱ ትእዛዛት እግዚአብሔር ከእያንዳንዱ ሰው ፍጹም የሆነ መታዘዝን እንደሚፈልግ ያመለክታሉ። በሕግ ውስጥ የተገለጸ አንዳችም ጸጋ የለም። የሕግ ዓላማ ሰዎች በራሳቸው መልካም ተግባራት ሊድኑ እንደማይችሉ ማሳየት ነው። ስለዚህ ሕጉ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን በእነርሱ ፈንታ በሞተው በክርስቶስ በኩል የደኅንነትን ስጦታ እንዲቀበሉ የሚያዘጋጅበት መንገድ ነው (ሮሜ 3፡19፥ 20)።

## ሀ. እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን ወደ ሲና ተራራ አመጣቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸአት 19፡1፥ 2 አንብብ። እስራኤላውያን መቼ እንደሚጓዙና ወደ የት እንደሚጓዙ አልወሰኑም ነበር። እግዚአብሔር ይህንን ውሳኔ አደረገ። እንደገኘ ያቸው፥ እንደጠባቂያቸውና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንደሚሰጣቸው አድርገው እንዲቀበሉት ይፈልግ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ዘጸአት 19፡3፥ 4 አንብብ። ሙሴ ያንን የሚቃጠለውን ቁጥቋጦ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየው በዚህ ተራራ ላይ ነበር። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ለሙሴ እርሱንና እስራኤላውያንን ወደዚህ ተራራ መልሶ እንደሚያመጣቸው ቃል ገብቶለት ነበር፤ ዘጸአት 3፡12 አንብብ።

እግዚአብሔር ሊታመኑበት የሚገባ ነው። ሙሴን ጠበቀው፥ እስራኤልን ነፃ አወጣና ወደ ሲና ተራራ አመጣቸው። እግዚአብሔር የገባቸውን የተስፋ ቃሎች ሁሉ የሚፈጽም አምላክ እንደሆነ ልትታመኑበት ትችላላችሁ።

## ለ. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የገባው ቃል ኪዳን።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ዘጸአት 19፡5፥ 6 አንብብ። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን እንዲተላለፍ የሚፈልገውን መልእክት ለሙሴ ነገረው። እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ስምምነት ለማድረግ ዐቀደ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን በፍጹምነት ከታዘዙት እንደሚባርካቸው ቃል ኪዳን ገባላቸው። የነገራቸውን በሙሉ ከፈጸሙ ይቀበላቸዋል፥ የሚያስፈልጋቸውንም መልካም ነገሮች በሙሉ ይሰጣቸዋል።

መምህር ሆይ:- በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ከመታዘዝ ጋር የተያያዘበት ይህ ሁለተኛው ጊዜ ነው። የመጀመሪያው አዳም በዔድን ገነት በነበረበት ጊዜ ነው። ሁለተኛው ለሕጉ በመታዘዝ ላይ ተመሥርቶ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለመባረክ ቃል የገባበት ወቅት ነው። በእነርሱ በኩል ያለውን የቃል ኪዳኑን ክፍል ከታዘዙና ከጠበቁ (ፍጹም የሆነ መታዘዝ)፥ ለእግዚአብሔር ልዩ ንብረት ይሆኑና ለአገልግሎቱ የካህናት መንግሥት ሆነው ይለያሉ (ዘዳግ. 26:16-19፥ 28:1-68)። ሕግ የበረከትን ተስፋ የሚሰጠው በመታዘዝ ላይ ተመሥርቶ እንደሆነና ዳሩ ግን ሕጉ ከሚጠይቀው የተቀደሰ ዓላማ በልባቸውም ሆነ በተግባራቸው ያፈነገጡትን እርግማን እንደሚያደርስባቸው ልዩ ትኩረት ሰጥተን ልንናገርበት ይገባል (ገላትያ 3:10)። ጸጋና ሕግን አታደባልቅ። ሕግ ምን ማድረግ እንዳለብን ያዛል እንጂ እናደርግ ዘንድ የሚሰጠው እርዳታ የለም። የዚህ ትኩረት ዓላማ አዳማጮችህን ለሕግ በመታዘዝ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኙ ወይም ሊባረኩ ፈጽሞ እንደማይችሉ ወደሚረዱበት ነጥብ በዝግታ ማምጣት ነው።

## ሐ. እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር የገቡት ቃል ኪዳን።

ዋና አሳብ:- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘጸአት 19:7፥ 8 አንብብ። እስራኤላውያን በሁሉ ነገር እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ቃል ገቡ።

የግብፃውያን ሠራዊት በቀይ ባሕር ባሳደዷቸው ጊዜ እግዚአብሔርን እንዴት ተጠራጥረውት እንደ ነበር አሁን ረሱት። እንደዚሁም ምግብና ውኃ ባልነበራቸው ጊዜ እንዴት አጉረምርመው እንደ ነበረ ዘነጉት። በዚያን ጊዜ በራሳቸው ተማምነው ነበር። የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን በሚገባ መታዘዝ ብቻ እንደሚያሻ አሰበው ነበር። ልባቸው በኃጢአት የተሞላ መሆኑንና በራሳቸው ጥረት እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙ እንደማይችሉ አልተገነዘቡም ነበር። እግዚአብሔር የሰጠውን ነገር መልሶ በመስጠት እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኝ እንደሚችል አሰቦ እንደነበረው እንደ ቃየን ሆነው ነበር።

የእስራኤል ሕዝብ ከዚህ አዲስ ስምምነት በኋላ እግዚአብሔር ሊባርካቸውም ሆነ የሚያስፈልጋቸውን መልካም ነገሮች ሁሉ ሊሰጣቸው እንደማይችል አልተገነዘቡም ነበር። ስምምነቱ እግዚአብሔርን በፍጹምነት ከታዘዙ እንደሚቀበላቸውና እንደሚባርካቸው፥ ካልታዘዙ ደግሞ በእግዚአብሔር እንደሚረገሙና እንደሚቀጡ የተደነገገ ነበር። እግዚአብሔር በአጭር ጊዜ ውስጥ የእስራኤል ሕዝብ ትእዛዙን እንደሚጥስና በሕጉ ትእዛዝ መሠረት ስለ ኃጢአታቸው ሊቀጣቸው እንዳለ ያውቅ ነበር።

ጠላቶቻችሁ እንደሚጠሏችሁ፥ ሊገድሏችሁ እንደሚፈልጉና ስምምነታችሁን ሊጠብቁ ዝንባሌ እንደሌላቸው እያወቃችሁ ከእነርሱ ጋር ስምምነት ታደርጋላችሁን?

እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን በእነርሱ በኩል ያለውን ስምምነት ሊጠብቁ እንደማይችሉ እያወቀ ይህን ስምምነት ለምን አደረገ? እግዚአብሔር ይህን ያደረገው እነርሱ ኃጢአተኞች እንደሆኑና እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እንደማይችሉ ሊያረጋግጥላቸው ሲል ነበር። በራሳቸው ጥረት የእርሱ ወዳጅ ሊሆኑ እንደማይችሉና ተቀባይነት እንደማያገኙ ለማሳየት ነበር።

ይህ የሚቀጥለው ታሪክ፥ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ምን ሊያስተምር እንደፈለገ ያስረዳናል። አንድ ሰው አንድ ወንዝ ለማቋረጥ በመዋኘት ላይ ነበር። ነገር ግን እጅግ ስለ ደከመ በፍጥነት የሚወርደውን ውኃ መቋቋም አቃተው። በዚያን ጊዜ የተወሰኑ ሰዎች ከወንዙ አጠገብ ሆነው ይመለከቱ ነበር። ከእነዚህ ሰዎች መካከል ከአንድ ጕበዝ ዋናተኛ በስተቀር ይህ እየሰመጠ የነበረውን ሰው ሊያድን የቻለ ማንም አልነበረም። በወንዙ አጠገብ ቆመው የነበሩት ሰዎች ሊሰጥም የቀረበውን ሰው እንዲረዳ ጕበዙን ዋናተኛ አጥብቀው ጠየቁት። እርሱ ግን እምቢ አለ። ሊሰጥም የቀረበው ሰው እየደከመ በሄደ ቁጥር ይህ ሰው ዝም ብሎ ይመለከተው ነበር። ሊሰጥም የጀመረው ሰው እጅግ በመዳከሙ ጥረቱን ባቋረጠና ተስፋ በቆረጠበት ጊዜ ጕበዙ ዋናተኛ ዘሎ በመግባት አወጣው። ታዲያ በወንዙ አጠገብ የነበሩት ሰዎች እጅግ እስኪደክም ድረስ ለምን ጠበቅከው በማለት ወቀሣ ሰንዝረውበት ነበር። እርሱ ግን እንዲህ በማለት መለሰላቸው።

«እየሰጠመ የነበረው ሰው የራሱን ጥረት እያደረገ በሚፍጨረጨርበት ጊዜ ልረዳው ብሞክርም ፈቃደኛ ስላልሆነ ልረዳው አልችልም ነበር፥ ነገር ግን ልረዳው የቻልኩት የእርሱ ጥረት ተሟጦ ባለቀ ጊዜ ነው።»

እግዚአብሔር፥ ለእስራኤላውያን ሕግን የሰጠው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት የማይችሉ መሆናቸውን ለማሳየት ነበር። ተስፋ ቆርጠው በእርሱ በሚደገፉበት ጊዜ ከዘላለም ቅጣት ሊያድናቸው ፈቃደኛ ነበር። እግዚአብሔር ከሰዎች ሁሉ ጋር የሚሠራበት መንገድ ይህ ነው። እግዚአብሔር ነፃ የሚያወጣቸው በሰይጣን፥ በኃጢአትና በሞት ቁጥጥር ሥር የወደቁ ኃጢአተኞች መሆናቸውን አምነው የሚቀበሉ ሰዎችን ነው።

እግዚአብሔር፥ ስለ ራሳችሁ እንድትማሩ የሚፈልገው ነገር ይህንን ነው። እናንተ ራሳችሁን መርዳት የማትችሉ ኃጢአተኞች ናችሁ። ራሳችሁን ከኃጢአት፥ ከሰይጣንና ከሞት ነፃ ልታወጡ አትችሉም።

## መ. ለእግዚአብሔር መገለጥ በተራራው ላይ የተደረገ ዝግጅት

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

ዘጸአት 19፡9-11 አንብብ። እግዚአብሔር ታላቅ ክብሩን፥ ኃይሉንና ቅድስናውን በእስራኤላውያን ፊት በማሳየት ኃጢአትን የሚጠላና ቃሉን የማይታዘዙትን የማይቀበል መሆኑን እንዲገነዘቡ ለማድረግ ዐቀደ።

ዘጸአት 19፡12፥ 13 አንብብ። እግዚአብሔር በተራራው ዙሪያ ክልል እንዲያበጁ ነገራቸው። ከተራራው እጅግ እንደማይቀርቡ ወይም እንደማይነኩት እርግጠኞች መሆን ነበረባቸው። እግዚአብሔር በተራራው ላይ በሚወርድበት ጊዜ በተራራው አጠገብ እንኳ የተገኘ ሰው ወይም እንስሳት ይገደል ነበር።

የኃጢአት ሁሉ ቅጣት ሞት ነው። ይህ የሆነው እግዚአብሔር ፍጹም ቅዱስ፥ ሰው ደግሞ ኃጢአተኛ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ፍጹም ያልሆነ ማናቸውንም ነገር ወይም ሰው አይቀበልም።

ኃጢአተኞችን በሙሉ ከአጠገቡ ያርቃቸዋል። ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አይችሉም። አዳምና ሔዋን በኃጢአታቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለዩ። አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ስለሠሩ ከዔድን ገነት ውጪ ከእግዚአብሔር ራቅ ያለ ስፍራ እንዲኖሩ ተደረገ። እግዚአብሔር ትእዛዙን ያለመጠበቅን ይጠላልና ከኃጢአተኞች ጋር ኅብረት የለውም።

ዋና አሳብ፡- ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚቻለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ዘጸአት 19፡14፥ 15 አንብብ። ሙሴ፥ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሕዝቡን አዘጋጀ። ዝግጅቱን እግዚአብሔር ባዘዘው መንገድ ሊያደርጉት ይገባ ነበር፥ አለበለዚያ ይሞቱ ነበር።

## ሠ. እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ሆኖ ለእስራኤላውያን ተናገረ

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ዘጸአት 19፡16-19 አንብብ። እግዚአብሔር በተናገረ ጊዜ ሕዝቡ መፍራቱ የሚያስደንቅ አይደለም።

እግዚአብሔር በዚያ ተራራ ላይ ራሱን እንዳሳየው ሁሉ ዛሬም ለእናንተ እራሱን ቢያሳያችሁ እንዴት ይሰማችኋል?

የነጐድጓድ ድምፅ የእሳትና የከባድ ደመና መታየትና የመሬት መንቀጥቀጥ መከሰቱ፥ እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ የሚጠላና የሚቀጣ፥ ሁሉን ቻይና የቁጣ አምላክ መሆኑን ለእስራኤላውያን የሚያሳይ ነበር።

እግዚአብሔር በኖኅ ዘመን ዓለምን ሁሉ ባጠፋ ጊዜ ታላቅ ኃይሉንና ለኃጢአት ያለውን ጥላቻና ቅጣት አሳይቶ ነበር። እጅግ ክፉ በነበሩበት የሰዶምና ገሞራ ከተሞችም ላይ እሳትንና ዲን አዘንበባቸዋል። በግብፃውያን ላይ እጅግ ከባድ የሆኑ መቅሠፍቶችን በላከ ጊዜና የፈርዖንን ሠራዊት በባሕር ባሰጠመ ጊዜ ኃይሉንና

በኃጢአት ላይ ያለውን ጥላቻና ቅጣት ገልጾአል። እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል፥ ኃጢአተኞችን ሁልጊዜ ይቀጣል።

መምህር ሆይ፡- ዕብራውያን 12፡18-21፥ 29 ተመልከት።

## ረ. እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን ወደ ተራራው እንዳይሄዱ እንደገና አስጠነቀቃቸው

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ዘጸአት 19፡20-25 አንብብ። እግዚአብሔር፥ ለሙሴ እስራኤላውያን ኃጢአተኞች ስለሆኑና እግዚአብሔር ደግሞ ቅዱስ ስለሆነ ወደ ተራራው ቢቀርቡ እንደሚሞቱ በመንገር አስጠነቀቃቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሙሴ ኃጢአተኛ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ተቀበለው፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ምሕረት ታምኖ እግዚአብሔር በተናገረው መንገድ ወደ እርሱ ስለቀረበ ነው። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ወደ ተራራው መውጣት አይገባውም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር መልእክቱን ለሙሴ ለመስጠት ፈለገ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሙሴ፥ የእግዚአብሔርን መልእክት ለእስራኤላውያን ለመስጠት የተመረጠ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነበር። ሕዝቡ የሙሴን ቃል ለመስማት ፈቃደኛ ባይሆኑ እግዚአብሔርን ለመስማት ያለመፍቀድ ነውና ይቀጡ ነበር።

እግዚአብሔር ለሙሴ ወደ ሕዝቡ እንዲወርድና ምናልባት እግዚአብሔርን ለማየት ወደ ተራራው እንወጣለን የሚል ፍላጐት እንዳያድርባቸው እንደገና ያስጠነቅቃቸው ዘንድ ነገረው። ይህን ቢያደርጉ ግን እግዚአብሔር ሁሉንም ይገድላቸዋል።

ይህ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሁላችንም የሰጠን መልእክት ነው። ስለዚህ ከዚህ መጽሐፍ ለመስማትና ለመታዘዝ የማይፈልጉ ሁሉ በእግዚአብሔር ለዘላለም ይቀጣሉ።

መምህር ሆይ፡- ዕብራውያን 2፡ 1-3 ተመልከት።

## ጥያቄዎች

1. ሙሴ በሲና ተራራ የሚቃጠለውን ቁጥቋጦ በተመለከተ ጊዜ እግዚአብሔር ለሙሴ ምን ቃል ኪዳን ገባለት? ሙሴን በሰላም ጠብቆ ወደ ሲና ተራራ እንደገና እንደሚያመጣው ቃል ገባለት።

2. እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባውን ነገር አደረገን? አዎን። እግዚአብሔር ሁልጊዜ የተናገረውን ያደርጋል።

3. እግዚአብሔር፥ ለእስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሊሰጥ ያቀደው ለምን ነበር? እስራኤላውያን ኃጢአተኞች እንደሆኑና እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እንደማይችሉ ወይም በእርሱ ዘንድ በራሳቸው ጥረት ተቀባይነት ሊያገኙ እንደማይችሉ ሊያረጋግጥላቸው ሲል ነበር።

4. የእስራኤላውያን ዝንባሌ ምን ነበር? እግዚአብሔርን የተጠራጠሩበትንና በእርሱ ፊት ኃጢአት ያደረጉበትን በርካታ ጊዜያት ዘነጉ። እነርሱ ትዕቢተኞችና በራሳቸው የሚተማመኑ ነበሩ።

5. እግዚአብሔር ለሙሴ በተራራው ዙሪያ ከልል እንዲያበጅ የነገረው ለምን ነበር? እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ ኃጢአትን ይጠላል! ስለዚህ ኃጢአተኞች ወደ እርሱ እንዲቀርቡ ፈጽሞ ስለማይፈቅድ ነበር።

6. ሕዝቡ እጅግ የፈራው ለምን ነበር? ተራራው እጅግ ስለተናጋና እንዲሁም እሳት፥ ከባድ ደመናና፥ መብረቅ ስለነበር ነው።

7. ይህ ሁሉ ነገር ለእስራኤላውያን የሚያሳየው ምን ነበር? እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ፥ ንጹሕ እንደሆነና ኃጢአትን እንደሚጠላና እንደሚቀጣ ያሳያል።

8. እግዚአብሔር ለእስራኤል የላከው መልእክተኛ ማን ነበር? ሙሴ።

9. ዛሬ የእግዚአብሔርን ቃል የምንሰማው እንዴት ነው? የእግዚአብሔርን ቃል የምንሰማው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው።

# ትምህርት 33

የትምህርት ክፍል:- ዘጸአት 20፡ 1-17

አጠቃላይ ርእስ:- አሥርቱ ትእዛዛት።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች:-

ሀ. እግዚአብሔር አሥርቱን ትእዛዛት ለእስራኤል ሕዝብ ሰጠ፤ (20፡ 1፥ 2)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ለ. የመጀመሪያው ትእዛዝ (20፡ 3)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሐ. ሁለተኛው ትእዛዝ (20፡ 4-6)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

መ. ሦስተኛው ትእዛዝ (20፡ 7)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሠ. አራተኛው ትእዛዝ (20፡8-11)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ረ. አምስተኛው ትእዛዝ (20፡12)።

. እግዚአብሐር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሰ. ስድስተኛው ትእዛዝ (20፡8-13)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሸ. ሰባተኛው ትእዛዝ (20፡24)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ቀ. ስምንተኛ ትእዛዝ (20፡15)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

በ. ዘጠነኛው ትእዛዝ (20፡16)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። እራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ተ. አሥረኛው ትእዛዝ (20፡17)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ቸ. ማጠቃለያ

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

የትምህርት 32 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ።

### ሀ. እግዚአብሔር አሥርቱን ትእዛዛት ለእስራኤል ሕዝብ ሰጠ።

ዋና አሳብ፦ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል

ሙሴ፥ ወደ ተራራው ሥር ከተመለሰ በኋላ እግዚአብሔር ከተራራው ላይ ሆኖ ለእስራኤላውያን ተናገረ፤ ዘጸአት 20፡ 1፥ 2 አንብብ።

ተራራው እየተናወጠ ነበር። ነጐድጓድና የመብረቅ ብርሃን እንዲሁም ጢስ አሁንም ነበር። ሕዝቡ ስለፈሩ ከተራራው ርቀው ይገኙ ነበር። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ተናገረ፥ አሥርቱን ትእዛዛትም ሰጣቸው።

ዋና አሳብ፦ እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

ከእነዚህ ትእዛዛት አንዱን እንኳ መጣስ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ወደ ዘላለማዊ ቅጣት መሄድ ነው። ይህ የቅጣት ስፍራ ለሰይጣንና እርሱን ተከትለው በእግዚአብሔር ላይ ላመፁ መላእክት እግዚአብሔር ያዘጋጀው ነበር።

ዋና አሳብ፦ ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር ትእዛዛቱን ለእስራኤል በሚሰጥበት ጊዜ እንኳ ሁልጊዜ ትእዛዛቱን ሁሉ በፍጹምነት ሊታዘዙት እንደማይችሉ ያውቅ

ነበር። ታዲያ እግዚአብሔር ትእዛዛቱን ሊከተሉ እንደማይችሉ እያወቀ ለእስራኤላውያን ለምን ሰጣቸው? ይህን ያደረገው እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በፍጹምነት ሊታዘዙት እንደማይችሉና በራሳቸው ጥረት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኙ እንደማይችሉ ለማስገንዘብ ነበር።

ደግሞም እግዚአብሔር ሕጉን ለእስራኤላውያን የሰጠው እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት እንደማይችሉ ለማሳየት ብቻ አልነበረም። ሰዎች ሁሉ ምን ያህል ኃጢአተኛ እንደሆኑ እንዲረዱና ማንም ሰው በሚያደርገው ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝ እንደማይችል ለማስገንዘብ ነው። እግዚአብሔር ሕግን የሰጠው ሰዎች ሁሉ ከዘላለም ቅጣት ለመዳን በእርሱ ምሕረት ላይ መደገፍ እንደሚገባቸው ለማሳወቅ ነው።

የእግዚአብሔር ትእዛዛት እንደ መስታወት ናቸው። ወደ መስታወት እስካልቀረብን ድረስ ቆሻሻ ፊታችንን ለማየት እንደማንችል ሁሉ ሕግ እስካላሳየን ድረስ ቆሻሻ ልባችንን ለማየት አንችልም።

የእግዚአብሔር ሕግ እንደ ራጅ ማንሻ መሣሪያ ነው። በውስጣችን ምን ዓይነት እንደሆንን ያሳየናል። ይህም ማለት እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያየን ማለት ነው።

*መምህር ሆይ:- ያዕቆብ 1:22-25 ተመልከት።*

ነገር ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ ለመጠበቅ ካልቻልን ምን ይሆናል? የቻልነውን ያህል ካደረግንና የጥረታችንን ያህል ከደከምን እግዚአብሔር ይቀበለናልን? አይቀበለንም። እግዚአብሔር ያለው ትእዛዛቱን በሙሉ በፍጹምነት ሁልጊዜ ልንፈጽማቸው እንደሚገባ ነው። አንዳንዶቹን ትእዛዛት ብቻ በፍጹምነት መፈጸም አይበቃም። እግዚአብሔር፥ ሰው አብዛኛውን ትእዛዛቱን ቢጠብቅና አንዱን እንኳ ቢያፈርስ ሁሉንም እንዳፈረሰ ይቆጥረዋል። ያ ሰው ኃጢአተኛ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ቅጣቱን ይቀበላል።

እግዚአብሔር አንድን ሰው ኃጢአተኛ ብሎ ይቀጣው ዘንድ ከትእዛዛቱ አንዱን ብቻ ለአንድ ቀን እንኳ መተላለፍ በቂው ነው። አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ተለይተው ከዔድን ገነት እንዲወጡ

ከመደረጉ በፊት እግዚአብሔርን ስንት ጊዜ በደሉ? አዳምና ሔዋን አንድ ጊዜ ብቻ ኃጢአትን አድርገው የሞትን ቅጣት ተቀበሉ።

እግዚአብሔር የሚጠብቅብን ትእዛዛቱን ሁሉ ሁልጊዜ እንድንጠብቅ ነው። ከትእዛዛቱ አንዱን አንድ ጊዜ ብቻ እንኳ ብንተላለፍ አይቀበለንም።

መምህር ሆይ፡- የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በሙሉ የመጠበቅ አስፈላጊነትን ለማሳየት ከመካከሉ አንድ ቀለበት በጐደለው ሰንሰለት መግለጫነት መጠቀም ይቻላል።

አንድ ሰንሰለት ከመካከሉ አንድ ቀለበት ቢወጣበት ጠንካራ መሆኑ ሊቀጥል ይችላልን? አንዱ ኃይለኛ እንስሳህን አንዱ ቀለበት በተሰበረበት ሰንሰለትህ ልታስረው ትችላለህን? የተሰበረ ቀለበት ባለው ሰንሰለት ወደታሠረ አደገኛ የዱር አውሬ መቅረብ ይቻላልን? ነገር ግን የምትፈሩት ምንድን ነው? ከሰንሰለቱ ውስጥ የተሰበረው አንድ ቀለበት ብቻ ነው፥ የቀሩት በሙሉ ጥሩ ስለሆኑ አትፍሩ ብላችሁ ወደዚህ አደገኛ አውሬ ትቀርባላችሁን? አታደርጉትም! ሰንሰለቱ ጠንካራ ነው፥ ችግር የለም ልንል የምንችለው አንድም የተሰበረ ቀለበት ከሌለበት ነው። አንድ ቀለበት እንኳ የተሰበረ ቢሆን ሰንሰለቱ የማይረባና ዋጋ የሌለው ይሆናል።

የእግዚአብሔር ሕግ ልክ እንደዚህ ነው። አንዱን ከተላለፍን ሁሉንም እንደተላለፍን ይቆጠራል። እግዚአብሔር፥ ከትእዛዛቱ አንዱን እንኳ ብንተላለፍ ኃጢአትን አድርገናልና ቅጣት እንደሚጠብቀን ተናግሯል።

እግዚአብሔር፥ ሰዎች ሁሉ እርሱን ፍጹም እስከሚያስደስቱ መልካም ሊሆኑና ከቅጣቱ ሊያመልጡ እንደማይችሉ እንዲገነዘቡ ይፈልጋል። ሁላችንም፥ ኃጢአተኞች ሆነን ከእግዚአብሔር ተለይተን ስለተወለድን የእግዚአብሔርን ሕግጋት እርሱ በሚፈልገው መንገድ በፍጹምነት ልንጠብቅ አንችልም። እግዚአብሔር፥ በእኛ ደስ እንዲለውና እንዲቀበለን በሚያስችል ሁኔታ እግዚአብሔርን ልናውቀው፥ ልንወደውና ልንታዘዘው አንችልም።

እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ለእኔና ለሌሎች ወንጌላውያን አስተምሮናል። የእግዚአብሔር ሕግ እንደተላለፍንና ወደ ዘላለም ቅጣት መሄድ እንደሚገባን እግዚአብሔር አስተምሮናል። እኛም ራሳችን ኃጢአተኞች ሆነን ስለተወለድን በራሳችን መልካም ሥራዎች እግዚአብሔርን ለማስደሰት አንችልም። በምናደርጋቸው ነገሮች እግዚአብሔር ሊቀበለን ፈጽሞ አይችልም።

የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በምናነብበት ጊዜ እርሱ የሚጠላቸውን በርካታ ነገሮች እንዳደረጋችሁ፥ ትእዛዛቱን በፍጹምነት መጠበቅ እንዳልቻላችሁ ከእግዚአብሔር ለዘላለም ከመለየት ራሳችሁን ማዳን እንደማትችሉ፥ አምናችሁ እንድትቀበሉ እግዚአብሔር ይፈልጋል።

እግዚአብሔርን በምታደርጉት ነገር ልታስደስቱት አትችሉም። ከእግዚአብሔር ፊት ኃጢአቶቻችሁን ልታስወግዱ አትችሉም። ኃጢአቶቻችሁ በሙሉ መከፈል አለባቸው። የኃጢአት ቅጣት ደግሞ ሞት ማለትም ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለዘላለም ለእሳት መዳረግ ነው።

መምህር ሆይ፡-

ሀ. እያንዳንዱን ትእዛዝ እያነበብክ ቀለል ያለ ማብራሪያ ስጥባቸው። ይህን ትምህርት ፈጥነህ አትለፈው። አስፈላጊ ከሆነ ትምህርቱን ወደ በርካታ ክፍሎች ከፋፍለው። አስታውስ «... ኃጢአት በሕግ ይታወቃል» (ሮሜ 3፡20)።

ለ. የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መታዘዝ የሚያስፈልገው ከልብና ከአእምሮ ጭምር ነው እንጂ እንዲሁ ለእይታ ብቻ አይደለም።

ሐ. በእያንዳንዱ ትእዛዝ ውስጥ ያለው ዋና አሳብ እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ መሆኑ ነው። ለሕዝቡ ትክክለኛ ነገር ትክክል፥ የተሳሳተ ነገር ደግሞ የተሳሳተ የሚሆነው፥ እግዚአብሔር ሉዓላዊና የሁሉ የበላይና ገዥ ስለሆነና የራሱ መመዘኛ ስላስቀመጠለት ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሊጠየቅ አይቻልም ፥ሊጠየቅም አይገባውም።

## ለ. የመጀመሪያው ትእዛዝ።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

ዘጸአት 20:3 አንብብ። በመጀመሪያው ትእዛዝ እግዚአብሔር፥ እርሱ ብቻ አምላክ እንደሆነ ተናገረ። ይህ ማለት ሰዎች ሁሉ ሊከተሉት የሚገባው እርሱ ብቻ ነው ማለት ነው። እርሱ ፍጹምና ብቸኛ የሆነ መሪ ነው። እግዚአብሔር የአምላክነት ስፍራውን ማንም እንዲሻማው አይፈቅድም። ሰዎች በምድራዊ ሕይወታቸውም ሆነ ከዚህ ሕይወት በኋላ ለሚያስፈልጋቸው ነገር መታመን ያለባቸው በእግዚአብሔር ብቻ ነው። ከእርሱ በስተቀር ማንንም ወይም ምንም ነገር ማምለክ የለባቸውም። በአስተሳሰባቸው ከፍተኛውን ስፍራ ሊሰጡት የሚገባው ለእግዚአብሔር ነው። ስለ ሁሉም ነገር ምስጋናና ክብር ሊሰጡት ይገባል።

በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ስፍራ ማንም ደግሞም ምንም ሊይዘው አይገባውም። አንድ ሰው በእግዚአብሔር ቦታ ማንንም ቢያኖር ይህ ዓመፃና ኃጢአት ነው። በንግግራችን እግዚአብሔር ገዢአችን ነው ብንልም እንኳ ሁልጊዜ በሕይወታችን የመጀመሪያውን ስፍራ የምንሰጠው ለእግዚአብሔር ካልሆነ ትእዛዛቱን ተላልፈናል ማለት ነው።

ዋና አሳብ:- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

አዳም፥ እያወቀ ሆን ብሎ በሕይወቱ ለእግዚአብሔር የመጀመሪያውን ስፍራ ከመስጠት ዘወር አለ። አዳም በእግዚአብሔር መንገድ ከመሄድ ይልቅ በራሱ መንገድ ሄደ። የአዳም ዘሮች በሙሉ በራሳቸው መንገድ ሄዱ። በሕይወቱ ክፍል በሙሉ እግዚአብሔር ገዥ እንዲሆን የፈቀደ ማንም የለም።

የእናንተና የእኔ ቀደምት አባቶች ይህንን የመጀመሪያውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፉ። በእግዚአብሔር ስፍራ መናፍስትን አኖሩ። በሕይወታቸው የእግዚአብሔርን ስፍራ ሰይጣን ወሰደ።

ይህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ማናችንም ብንሆን አልፈጸምንም፥ ለዚህ ትእዛዝ መተላለፍ ቅጣቱ ከእግዚአብሔር መለየት ነው።

መምህር ሆይ:- ይህንን አሳብ ለማስፋት በቂ ጊዜ ውሰድ። እግዚአብሔር በእውነት አምላክ እንደሆነ መስማማት ማለት በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እርሱን ብቻ መስማት፥ መታዘዝ ከፍ ማድረግና ማምለክ፥ ኃይሉን ወይም ሥልጣኑን ወይም ክብሩን ለማንም ያለመስጠት ማለት ነው። ሆኖም ይህን ነገር ልናሟላው እንደምንችለው ነገር አድርገህ እንዳታስተምር ተጠንቀቅ። ይልቁኑ ይህ ማናችንም ልናደርገው የማንችለውና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ማንም ሊፈጽመው እንደማይችል አሳያቸው።

ሐ. ሁለተኛው ትእዛዝ።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸአት 20:4-6 አንብብ። እግዚአብሔር ይህን ሁለተኛ ትእዛዝ ለእስራኤላውያን የሰጠው እርሱ መጀመሪያ የሌለው ታላቅ፥ ዘላለማዊ መንፈስ እንደሆነና እንደ ሰውና እንደሌሎችም እንደተፈጠሩ ማናቸውም ነገሮች ሁሉ አካል የሌለው መሆኑን ለማሳየት ነው።

እግዚአብሔር ሰው አይደለም፥ ወይም አዕዋፍ፥ እንስሳና ዓሣም አይደለም። ማንም ሰው እግዚአብሔር የፈጠረውን ነገር በፈጣሪው በእግዚአብሔር ስፍራ ማስቀመጥ የለበትም።

እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል የሚያውቅ ማንም የለም። ስለዚህ እግዚአብሔር ለእርሱ አንዳችም ምስል እንዳይደረግ ተናገረ። እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል የምናውቅበት ብቸኛው መንገድ በዚህ መጽሐፍ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ነገር የተለየ ሁሉ የሰይጣን ውሸት ነው።

ዋና አሳብ:- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሰይጣን በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎችን ሁሉ ከእውነተኛው የእግዚአብሔር እውቀት አርቋቸዋል። እውነተኛውንና ሕያውን አምላክ አያውቁም። ሰይጣን በእግዚአብሔር ቦታ ሌሎች ነገሮችን

እንድናመልክ ይገፋፋናል። ሰዎች እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል የራሳቸውን አሳብና የሌሎች ሰዎችን አሳብ ይከተላሉ። ይህን ያደረጉ ሁሉ ሁለተኛውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለተላለፉ የተኰነኑ ናቸው።

መምህር ሆይ:- ሮሜ 1:18-23 ተመልከት። የምታስተምራቸው ሰዎች ጣዖታትን የሚያመልኩና ወይም ለእግዚአብሔር የተቀረጸ ምስል የሚያደርጉ ከሆነ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንደተላለፉና የተኰነኑ እንደሆኑ አመልክታቸው።

መ. ሦስተኛው ትእዛዝ።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸአት 20:7 አንብብ። በሦስተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር እርሱን ማክበር እንዳለባቸውና እርሱ ፈጣሪያቸውና እውነተኛው ገዢያቸው እንደሆነ በመገንዘብ ስሙን በከንቱ ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ እንዳይጠሩ ነገራቸው።

እግዚአብሔር የሁሉ ሰውና የሁሉ ነገር ሉዓላዊ ፈጣሪና ገዢ ነው። እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔርን ሊፈራና እርሱ ሕይወታችንን ሊወስድና ሁላችንንም ለዘላለማዊ ቅጣት ሊያጠፋን ኃይል እንዳለው ሊገነዘብ ይገባዋል።

ዋና አሳብ:- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ስለ ሰዎች ክፉ ነገሮችን መናገርና የሚገባቸውን ክብር ያለመስጠት ክፉ ነገር ነው። አንድ ልጅ ለቤተሰቡ አክብሮትን ሊያሳይ ይገባል። ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው ሊከባበሩ ይገባል። ወጣቶች ታላላቆቻቸውን ሊያከብሩ ይገባል። ለሰው የሚገባውን ክብር ያለመስጠት መጥፎ ነገር ነው። ነገር ግን እውነተኛና ሕያው የሆነውን አምላክ ያለማክበር ወይም በእግዚአብሔር ስም በማይገባ ሁኔታ መጠቀም እንዴት ክፉ ነገር ነው። ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ያልሰጡ ሁሉ የተኰነኑ ናቸው።

ሠ. አራተኛው ትእዛዝ።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸአት 20፡8-11 አንብብ። በአራተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር፥ ሁሉን ነገር በስድስት ቀናት ውስጥ የፈጠረውን ጌታን በማክበር ለማሳየት ሰባተኛውን ቀን ልዩ የዕረፍት ቀን አድርገው እንዲጠብቁት አዘዛቸው።

እግዚአብሔር፥ ዓለምን ከፈጠረና ከጨረሰ በኋላ በሰባተኛው ቀን ምን እንዳደረገ ታስታውሳላችሁን? አዎን እግዚአብሔር ከሠራው ሥራ ዐረፈ። እግዚአብሔር ለምን ዐረፈ? አዎን እግዚአብሔር ያረፈው ሊሠራ ያቀደውን ሥራ ስላጠናቀቀ ነበር።

ስለዚህ እግዚአብሔር፥ ለእስራኤላውያን ምድርና በውስጧ ያሉትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረ እርሱ ብቻ እንደሆነ እንዲያስቡ በየሰባተኛው ቀን ማረፍ እንዳለባቸው ነገራቸው። የዚህ ዓለም መብት ያለው ባለቤት እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሰይጣንና ክፉ መላእክቱ ይህንን ዓለም ለራሳቸው ቢያደርጉትም ነገር ግን በትክክል የራሳቸው አይደለም።

ለነገሮች ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው። አዝርዕት በተገቢው ሁኔታ እንዲያድጉ ዝናብንና ፀሐይን ይሰጣል። እርሱ ብቻ የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ፥ ባለቤትና ሕይወት ሰጭ ነው። ሰይጣን በዚህ ዓለም የሚኖሩ ሕዝቦችን ይቆጣጠራል፥ ነገር ግን ዓለም የእግዚአብሔር ንብረት ናት።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ከእግዚአብሔር ሌላ እንደፈጣሪና ሕይወት ሰጪ አድርገው በሌላ በማንም የሚታመኑ ወይም ሌላውን ተስፋ የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፈዋል። በእውነተኛው ፈጣሪ ላይ ይህንን አስከፊ ኃጢአት የሠሩ ሁሉ በእግዚአብሔር ይቀጣሉ።

መምህር ሆይ፡- የምታገለግለው የሰባተኛ ቀን አክባሪ የሆኑት የአድቬንቲስት አማኞች የሚገኙበት አካባቢ ከሆነ ለአድማጮችህ፥እግዚአብሔር የበግ ወይም የሌሎች እንስሳት መሥዋዕት እንዲያቀርቡለት እንዳላዘዘ ሁሉ፥ በሰባተኛው ቀን እንዲያርፉ እንዳላዘዛቸው መግለጽ ያስፈልግህ ይሆናል። ሆኖም ግን እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪ እርሱ ብቻ እንደሆነና ሌላ አምላክ እንደሌለ እንዲያውቁ ይፈልጋል። ነገር

ካን የሰንበት ጥያቄ የመከራከሪያ አሳብ ወይም ዋና ርእስ እንዳይሆን ጥንቃቄ አድርግ። ቆይተህ ክርስቲያኖች በሚሆኑበት ጊዜ በዚህ በሰንበት ጉዳይ ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ያስፈልግሃል። በሰንበት ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የመነጋገሪያ ርእስ ለሚያደርጉት ሰንበትን ቢጠብቁና ሌሎቹን ዘጠኝ ትእዛዛት በፍጹምነት ለመጠበቅ ባይችሉ ሰንበትን መጠበቃቸው ከንቱ መሆኑን ግለጽላቸው። (ያዕቆብ 2፡9-11)።

ረ. አምስተኛው ትእዛዝ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸአት 20፡12። በአምስተኛው ትእዛዝ፥ እግዚአብሔር፥ ልጆች ወላጆቻቸውን መታዘዝ እንዳለባቸው ተናገረ። ይህን ካላደረጉ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ያደርጋሉ፥ እግዚአብሔር ልጆች እንዲኖራቸው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። የእግዚአብሔር ዕቅድ ወላጆች ለልጆቻቸው እንክብካቤ እንዲያደርጉ፥ ልጆች ደግሞ ወላጆቻቸውን እንዲወዱ፥ እንዲያከብሩና እንዲታዘዙ ነው።

እግዚአብሔር ይህን ትእዛዝ ሰጣቸው። ይህንን ትእዛዝ በፍጹምነት የማይታዘዝ ማንኛውም ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይተላለፋል።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ማናችንም ብንሆን እግዚአብሔር የሚጠብቅብንን ያህል ወላጆቻችንን አልታዘዝንም። ሁላችንም ይህንንና ሌሎች ትእዛዛትን ተላልፈናል። አስታውሱ! ከትእዛዛቱ ዘጠኙን ብንታዘዝና አንዱን ብንተላለፍ በእግዚአብሔር መኰነናችን አይቀርም። በተጨማሪ እግዚአብሔር እነዚህን ትእዛዛት እንድናከብር የሚጠብቅብን ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ እስከምንሞትበት ቀን ድረስ ነው። አንዱን ያለመታዘዝ እንኳ ከእግዚአብሔር ለዘላለም የመለየትን ቅጣት ያስከትላል።

ሰ. ስድስተኛው ትእዛዝ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸ. 20፡13፡- በስድስተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር ሰው መግደል በእርሱ ላይ ኃጢአት መሥራት እንደሆነ ተናገረ። እግዚአብሔር የሰው ሁሉ ፈጣሪ ነው። እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ሕይወትን ሰጥቷል። እግዚአብሔር በቃሉ ከተናገረው በስተቀር ማንም ሰው የሌላውን ሕይወት የማጥፋት መብት የለውም።

መምህር ሆይ፡- እግዚአብሔር መንግሥታትን ሰው የገደለውን ጥፋተኛ ሰው እንዲገድሉ አዟቸዋል፤ (ዘፍጥረት 9፡6፤ ሮሜ 13፡1-4)።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር በተጨማሪ በቃሉ ውስጥ ሰውን መጥላት በልብ ውስጥ የመግደል ያህል እንደሆነ ግልጽ አድርጎታል። እግዚአብሔር፥ አንድ ሰው ሌላውን የመግደል ፍላጎት ቢያድርበት፥ እንደገደለ ተቆጥሮ እንደሚኰነን ተናግሯል። አንድን ሰው ብንረግም እንኳ እንደ ነፍሰ ገዳይ እንቆጠራለን። እግዚአብሔር የሚፈርድብን ባደረግነው ነገር ብቻ ሳይሆን ልናደርግ በምንፈልገው ነገር ጭምር ነው።

መምህር ሆይ፡- ማቴዎስ 5፡21-28 ተመልከት።

## ሸ. ሰባተኛው ትእዛዝ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸ. 20፡14 አንብብ። እግዚአብሔር፥ በሰባተኛው ትእዛዝ የተናገረው ከትዳር ጓደኛ ውጭ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት መሆኑን ነው። ለፍትወተ ሥጋ ኃጢአት ሁሉ ቅጣቱ ከእግዚአብሔር ለዘላለም መለየት ነው።

እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረ ጊዜ ሔዋንን ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠው። እግዚአብሔር በጋብቻ ስለተጣመራችሁ ከእንግዲህ በፊቴ ሁለት ሰዎች አይደላችሁም አለ። ልክ እንደ አንድ ሰው ነበሩ። ባልና ሚስት አንዱ የሌላው ንብረት ስለሆነ አንዱ ከሌላው ጋር ብቻ እንዲኖሩ ያስፈልጋል። ዝሙት ወይም ሌሎች የፍትወተ ሥጋ ኃጢአቶችም በአሳብ ደረጃ ብቻ እንኳ ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማጤን ይገባል።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር ሰው ከትዳር ጓደኛው ሌላ ሰው ቢመለከትና ማንኛውም ዓይነት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ቢመኝ፥ ይህን ትእዛዝ ተላልፏል ማለት ነው። ይህን ሲያደርግ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት አድርጓል ማለት ነው። እርሱ ሁሉን ያውቃል። ከአስተሳሰባችን አንዱን እንኳ አይዘነጋም።

## ቀ. ስምንተኛው ትእዛዝ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸ. 20፡15 አንብብ። በስምንተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር፥ የሌላውን ሰው ንብረት በፍጹም መውሰድ እንደሌለባቸው ተናገረ።

ለእያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ንብረት ሰጥቶ እንዲጠብቅ ያደረገው እግዚአብሔር ነው። አንድ ሰው የሌላውን ሰው ንብረት ቢወስድ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን አድርጓል።

አንድ ሌባ የሰረቀውን ነገር ለባለቤቱ መመለስ ወይም ካሣ መክፈል አለበት፤ ሆኖም ግን ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ ለስርቆት ኃጢአት በቂ ማካካሻ ሆኖ እግዚአብሔርን አያረካውም። የስርቆት ኃጢአት ቅጣት ከእግዚአብሔር ለዘላለም መለየት ነው። እግዚአብሔር ከሞት በስተቀር ሌላ ክፍያ አይቀበልም። ሙሉው የሞት ቅጣት ለኃጢአት ካልተከፈለ በስተቀር እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር አይልም።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

አንድ ሰው ለመስረቅ ቢፈልግ ወይም ቢያቅድና ነገር ግን እያዝ ይሆናል ብሎ በመፍራት ቢተወው፥ በእግዚአብሔር ፊት በመስረቅ ኃጢአት ተጠያቂ ከመሆን አይድንም።

የሚከተለውን ዓይነት ድርጊት በእናንተ አካባቢ ተፈጽሞ እንደሆነ አላውቅም። ቀጥሎ የተመለከተው ታሪክ ግን አንድ ሰው የእርሱ ያልሆነ ምንም ነገር ባይወስድም እንኳ እንዴት በሌብነት እንደሚመደብ የሚገልጽ ነው።

አንድ ሰው በጣም ጥሩ አውራ ዶሮ በሌላ ሰው ቤት አየ። ሆኖም የአውራ ዶሮው ባለቤት ሊሸጥለት እንደማይፈልግ ቢሸጠውም እንኳ ለመግዛት በቂ ገንዘብ እንደሌለው ተመለከተ። ስለዚህ ሊሰርቀው ወሰነ። ከዚያም ባሌቤቱ አውራ ዶሮውን በምሽት የት እንደሚያስቀምጠው ተመለከተና ባለቤቱ ከባድ እንቅልፍ ላይ እንዳለ ለመመለስ ዐቀደ። ያቀደበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ ከቤቱ ተነሥቶ በቀጥታ አውራ ዶሮው ወዳለበት ቤት መጓዝ ጀመረ። አውራ ዶሮው የሚያድረው ከቤቱ አቅራቢያ በሚገኝ የዶሮ ቤት ውስጥ እንደሆነ አውቆ ነበር። ድንገት ሰው አይቶት ማንነቱን እንዳይለይ ምንም ዓይነት መብራት አልያዘም ነበር። ወደ ቤቱ በደረሰ ጊዜ ወደ አውራ ዶሮው መስፈሪያ ለመድረስ በጨለማው ውስጥ በእጁና በእግሩ ቀስ ብሎ መሳብ ጀመረ። አውራ ዶሮው የነበረበትን ክፍል ለመክፈት እጁን ሰደድ ሲያደርግ አውራ ዶሮው ፈራና ማስካካት ጀመረ። ሰውዬው ዘሎ በመውጣት ዓቅሙ የፈቀደውን ያህል እየሮጠ ጫካውን አቋርጦ ወደ ቤቱ ደረሰ። የአውራ ዶሮው ባለቤት ይህን ተወዳጅ ንብረቱን በዚያች ምሽት ሊሰርቀው የነበረው ማን እንደሆነ አላወቀም፥ እግዚአብሔር ግን አይቶታል። ሊሰርቅ ያቀደው ሰው የእግዚአብሔርን «አትስረቅ» የሚለውን ትእዛዝ ተላልፏል። ኃጢአትን አድርጓል፥ የኃጢአቱም ቅጣት ከእግዚአብሔር ለዘላለም መለየት ነው።

እግዚአብሔር፥ ኃጢአት በሙላት እስካልተከፈለ ድረስ ይቅር አይልም። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን በሙሉ ለሠሩት ብቻ ሳይሆን ሊሠሩት ዐቅደው ካልተሳካላቸው ኃጢአት በሙሉ ቅጣት ይፈጽምባቸዋል።

## በ. ዘጠነኛው ትእዛዝ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸአት 20፡16 አንብብ። በዘጠነኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር ስለሁሉ ነገር እውነትን ብቻ መናገር እንደሚገባ ተናገረ።

ሰይጣን ከሁሉ የላቀው ውሸተኛ ነው። ለአዳምና ሔዋን በዔድን ገነት ዋሻቸው። ለእኛና ለእናንተ ቀደምት አባቶች ውሸትን ተናገረ።

ሰይጣን በዓለም ሁሉ ለሚገኙ ሰዎች ውሸተን እየተናገረ ነው። ሰይጣን ያለማቋረጥ ውሸትን የሚናገሩ ሰዎች ሁሉ አባት ነው።

ዋና ሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

አንዳንድ ሰዎች ስለ ሌሎች ሰዎች እውነት ያልሆነ ነገር ይናገራሉ። ውሸት የሚናገሩባቸውን ሰዎች ስለሚጠሏቸው ወይም ስለሚቀኑባቸው ወይም ሊጐዱአቸው ስለሚፈልጉ ባላደረጉት ነገር ወይም ባልተናገሩት ነገር ይከሷቸዋል።

አንዳንድ ጊዜ ባሎች ስለ ሚስቶቻቸው፥ ሚስቶችም ስለ ባሎቻቸው ውሸት ይናገራሉ። ይህ እንዳትዋሹ ብሎ በተናገረው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን መሥራት ነው።

አንዳንድ ሰዎች የሐሰት ወሬ እየፈጠሩ የሚያስፈሩ ታሪኮችን ያሰራጫሉ። ሌሎች ያንን ይሰሙና በዚያ ላይ ይጨምሩበታል። እነዚህ ሁሉ ውሸት ስለሆኑ በእግዚአብሔር ላይ የተሠሩ ኃጢአቶች ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች መናፍስትን እንዳዩ ወይም መናፍስት ሲናገሩ እንደሰሙና መልእክት እንደሰጧቸው አድርገው ውሸት ይናገራሉ። ይህን ውሸት የሚናገሩት ሌሎች ሰዎችን በማስፈራራት ከእነርሱ ክፍያን ለማግኘት ነው።

አንዳንድ ሰዎች ጥፋት ነገር ያደርጉና ያደረጉትን ለመሸፈን ይዋሻሉ። ወደ ፍርድ ፊት በሚቀርቡበት ጊዜ እንኳ ይዋሻሉ።

ብዙ ሰዎች ስለሚዋሹና መዋሸታቸውን ሌሎች ስላላወቁባቸው ከፍርድ አምልጠዋል። ከእግዚአብሔር ግን ውሸትን ልንደብቅ አንችልም። እግዚአብሔር ሁልጊዜ እውነትን ይናገራል። እርሱ ስለማንኛውም ሰው ሆነ ነገር እውነቱን ያውቃል። እግዚአብሔር ውሸትን ስለሚጠላ ውሸተኞችን ሁሉ ይቀጣል።

## ተ. አሥረኛው ትእዛዝ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ዘጸአት 20፡ 17 አንብብ። የእግዚአብሔር አሥረኛ ትእዛዝ የሌሎች የሆነውን ማንኛውንም ነገር መመኘት የለባችሁም የሚል ነበር።

ይህ ኃጢአት የሰይጣን ኃጢአት ነበር። በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ የቀናና የታበየ ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ብዙ ሰዎች በሌሎች ሰዎች ንብረት የሚቀኑ ስስታሞች ናቸው። ከእነርሱ በላይ ያላቸውን ሰዎች ይጠላሉ፥ ደግሞም የሌሎችን ንብረት ይመኛሉ። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ባላቸው ነገር የሚረኩ አይደሉም። በአእምሮአቸው ሌሎች ያላቸው ነገር ስለሌላቸው ይናደዳሉ።

ይህም በእግዚአብሔር ላይ የተሠራ ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር ይህን ኃጢአት ይጠላል፤ ስለዚህ ምቀኛ የሆኑ ሰዎችን ሙሉ ይቀጣል።

ቸ. ማጠቃለያ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣቸው አሥር ትእዛዛት እነዚህ ናቸው። በየትኛውም ስፍራ ለሚኖሩ ሰዎች የእግዚአብሔር ትእዛዝ አንድ ዓይነት ነው። ስለዚህ እነዚህም ትእዛዛት ለእናንተም የተሰጡ ናቸው።

ለስርቆታችን፥ ለዝሙታችንና ለቁጣችን ምላሽ ብንሰጥም እንኳ የኃጢአት ዕዳችን ለእግዚአብሔር ተከፍሏል ማለት አይደለም። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው። ማለትም ለሰይጣንና ለመናፍስቱ እግዚአብሔር በአዘጋጀው ቦታ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለዘላለም መኖር ነው። ኃጢአት ሁሉ በእግዚአብሔር ይቀጣል። ከእርሱ የማምለጫ ስፍራ የለም።

## ጥያቄዎች

1. አንዱን ትእዛዝ እንኳ ቢተላለፉ የእግዚአብሔር ቅጣት ምንድን ነው? ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለዘላለም ለሰይጣንና ለመናፍስቱ በተዘጋጀው የቅጣት ስፍራ መኖር ነው።

2. እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን፥ አሥርቱን ትእዛዛት ሊጠብቁ ይችላሉ ብሎ አስቧልን? አላሰበም። እግዚአብሔር፥ ማንም ሰው ሙሉ በሙሉ ሊታዘዘው እንደማይችል ያውቅ ነበር።

3. ማንም ሰው እግዚአብሔርን በፍጹምነት ለመታዘዝ የማይችለው ለምንድን ነው? ሁላችንም ከእግዚአብሔር ተለይተን ኃጢአተኞች ሆነን ስለተወለድንና እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ስለማንችል ነው።

4. ታዲያ እግዚአብሔር ትእዛዛትን የሰጠው ለምንድን ነው?

   ሀ. ሰዎች ሁሉ በራሳቸው ጥረት በሚያደርጉት ነገር እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እንደማይችሉ ለሰዎች ሁሉ ለማረጋገጥ ነበር። የእግዚአብሔር ሕግጋት ምን ያህል ኃጢአተኛ እንደሆንን ያሳዩናል።

   ለ. እግዚአብሔር ሕጉን የሰጠው ሰዎች ከዘላለም ቅጣት ለመዳን በራሳቸው ሳይሆን በምሕረቱ እንዲታመኑ ለማድረግ ነበር።

5. እግዚአብሔር፥ ሰዎች ከእርሱ ሌላ የሚያመልኩት ወይም የሚያገለግሉት ነገር ቢኖራቸው ግድ አለውን? አዎን። ይህ በእግዚአብሔር ላይ የተሠራ ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር አምላክነቱንና የሁሉ የበላይ ገዥነቱን ከማንም ሆነ ከምንም ጋር አይካፈለውም።

6. የተቀረፀ ምስልን ለእግዚአብሔር ማድረግ ወይም ዛፎችን፥ ድንጋዮችን ወይም እግዚአብሔር የሠራቸውን ማናቸውንም ነገሮች ማምለክ ትክክል ነውን? አደለም! ይህም ቢሆን በቀጥታ በእግዚአብሔር ላይ የተሠራ ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ስለማናውቅ በምንም ነገር ልንመስለው መሞከር የለብንም።

7. እግዚአብሔር ስለ እርሱ በምናስበውና በምንለው ነገር ይገደዋልን? አዎን! እግዚአብሔር በአስተሳሰብና በንግግር ሁልጊዜ የማያከብሩትን ሁሉ ይቀጣል።

8. እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን በሰባተኛው ቀን ዕረፍ ያላቸው ለምን ነበር?

ሀ. እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ በስድስት ቀን ፈጥሮ ስለጨረሰና በሰባተኛው ቀን ስላረፈ፥

ለ. እግዚአብሔር ፈጣሪ እንደሆነና ያሉን ነገሮች ሁሉ ከእርሱ ዘንድ የተሰጡ መሆኑን ሁልጊዜ እንድናስታውስ ስለሚፈልግ ነው። በዓለም ላይ ስላሉ ነገሮች ሁሉ ምስጋናን ለሰይጣን፥ ለመናፍስቱ ወይም ለመሳሰሉት መስጠት የለብንም።

9. ልጆች ወላጆቻቸውን ያለመታዘዛቸው ወይም ያለማክበራቸው እግዚአብሔርን ግድ ይለዋልን? አዎን እግዚአብሔር፥ ወላጆቻቸውን ያልታዘዙትን ወይም ያላከበሩትን ይቀጣቸዋል።

10. እግዚአብሔር ነፍሰ ገዳዮችን በሙሉ የሚቀጣው ለምንድን ነው? ለሰዎች ሁሉ ሕይወትን የሰጠው እርሱ ስለሆነና የሰዎችን ሕይወት ለመውሰድ ሥልጣን ያለው እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው።

11. እግዚአብሔር ሌላውን ሰው ስለሚጠላ ሰው ምን ይላል? ያ ሰው ነፍሰ ገዳይ ነው ይላል።

12. እግዚአብሔር ስለዝሙት ያለው አመለካከት ምንድን ነው? እግዚአብሔር በትዳር ጓደኛሞች መካከል ከሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ውጭ ያሉትን ግንኙነቶች ሁሉ ይቃወማል፥ ይኰንናልም።

13. እግዚአብሔር የሚሰርቁትን ሁሉ የሚቀጣው ለምንድን ነው? ምክንያቱም ለሰዎች ንብረትን የማፍራት መብት የሰጠ እርሱ ስለሆነ ነው።

14. ሰዎች ሊሰርቁ አስበው እንያዛለን ብለው ፈርተው ቢተውት በመስረቅ ወንጀል ተጠያቂ ናቸውን? አዎን! ምክንያቱም እግዚአብሔር፥ በልባቸው የነበረውን የመስረቅ ዕቅድ ተመልክቷልና።

15. እግዚአብሔር ውሸትን ስለመናገር የሰጠው ትእዛዝ ምንድን ነው? ለማንም ሰው መዋሸት በእግዚአብሔር ላይ የሚሠራ ኃጢአት ነው። ምክንያቱም እርሱ ሁልጊዜ እውነትን ስለሚናገርና ሐሰትንም ስለሚጠላ ነው።

16. በሌሎች ሰዎች ብንመቀኝና ያላቸውን ብንመኝ እግዚአብሔር ይሰማዋልን? አዎን! ይህም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን መሥራት ነው። ያ ኃጢአት የሰይጣን ኃጢአት ነበር። በእግዚአብሔር ላይ በቅንዓት በመነሣት የእርሱን የሥልጣን ስፍራ ለመውሰድ ፈለገ።

# ትምህርት 34

የትምህርት ክፍል:- ዘጸአት 24፡12-18፤ 25፡1-11፤ 17-22፤ 26፡31-33፤ 27፡1፥ 2፤ 28፡1፤ ዘሌዋውያን 1፡1-5፤ 16፡2፥ 3

አጠቃላይ ርእስ:- የማደሪያው ድንኳን።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች:-

ሀ. ሙሴ እንደገና ወደ ተራራው በእግዚአብሔር ተጠራ (ዘጸአት 24፡12)።

. ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ለ. ኢያሱ ከሙሴ ጋር ወደ ተራራው ወጣ (ዘጸአት 24፡13-18)።

ሐ. እግዚአብሔር ሙሴን የማደሪያውን ድንኳን እንዲሠራ አዘዘው (ዘጸአት 25፡1-8)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

መ. የማደሪያው ድንኳን እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መንገድ መሥራት ነበረበት (ዘጸአት 25፡9)።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ሠ. ቅድስተ ቅዱሳን።

ረ. ታቦቱና የምሕረት መቀመጫው (ዘጸአት 25፡10፥ 11፥ 17-22)።

ሰ. መጋረጃው (ዘጸአት 26፡31-33)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ሸ. የናስ መሠዊያ (ዘጸአት 27፡1፥ 2፥ ዘሌዋውያን 1፡1-4)።

- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ቀ. አሮንና ልጆቹ ካህናት ተደረጉ (ዘጸአት 28፡1፤ ዘሌዋውያን 16፡2፥ 3)።

- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

- ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

የትምህርት 33 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

መምህር ሆይ፡- ለዚህ ትምህርት ቀለል ያለ የመገናኛውን ድንኳን ዓይነት ንድፍ ብትሠራ በጣም ጥሩ ነው። በተለይም ልታስተምራቸው ያሉትን የመገናኛው ድንኳን ቁሳቁሶች ሊገልጹልህ የሚችሉ ምስሎች ማዘጋጀቱ ይጠቅምሃል። እነርሱም የውጪኛው አጥር፥ የናስ መሠዊያው፥ ቅድስቱ፥ ቅድስተ ቅዱሳኑ፥ መጋረጃው፥ ታቦቱና የምሕረት መቀመጫው ናቸው። ቀላል አምሳያ ልትሠራ ካልቻልክ የመገናኛውን ድንኳን ገጽታ በሚያሳይ ሥዕል ወይም ፎቶ ተጠቀም። ስለ ዕቃዎቹ በምትገልጥበት ጊዜ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የት እንደሚቀመጡ መናገሩን አትርሳ።

ሀ. ሙሴ አንድ ጊዜ እንደገና ወደ ተራራው በእግዚአብሔር ተጠራ።

ዋና አሳብ: - እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር ሲና በመባል ከሚታወቀው ተራራ ላይ ለእስራኤላውያን ተናገረ። አሥርቱ ትእዛዛቱንም ነገራቸው።

እግዚአብሔር፥ ለእስራኤላውያን የሰጣቸውን ትእዛዝ እንዲረሱ ስላልፈለገ አንድ ጊዜ እንደገና ሙሴን ወደ ተራራው ጠራው። ሙሴ ለእስራኤላውያን ሊያስተምራቸው ይችል ዘንድ እግዚአብሔር ትእዛዛቱን በሁለት የድንጋይ ጽላቶች ሊጽፋቸው ዐቀደ። የእግዚአብሔርን ሕግ መርሳት አልነበረባቸውም። ዘጸአት 24፡12 አንብብ።

## ለ. ኢያሱ ከሙሴ ጋር ወደ ተራራው ወጣ።

ሙሴ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ወደ ተራራው ወጣ።

ዘጸአት 24፡13-18 አንብብ። ኢያሱ የሚባል ወጣት ሰው ከሙሴ ጋር አብሮ ተጓዘ። ኢያሱ የሙሴ ረዳት ነበር።

## ሐ. እግዚአብሔር ሙሴን የማደሪያውን ድንኳን እንዲሠራ አዘዘው።

ዋና አሳብ: - እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሙሴ በተራራው ላይ በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር ለሙሴ አሥርቱ ትእዛዛትን በሁለት የድንጋይ ጽላቶች ላይ ጽፎ ሰጠው።

በተጨማሪ እግዚአብሔር እስራኤላውያን ይተዳደሩባቸው ዘንድ የሰጠውን ሌሎች ትእዛዛትና ሥርዓቶች ለሙሴ አብራራለት። እግዚአብሔር ንጉሣቸው ነበር። ስለዚህ ሊያደርጉት የሚፈልገውን ነገር በሙሉ ነገራቸው።

እግዚአብሔር፥ ሙሴና ሕዝቡ እንዲያደርጉት የሚፈልገው አንድ ተጨማሪ ነገር ነበር። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ይህን እንዲያደርጉ ያዘዘበትን ምክንያት መረዳት አስፈላጊ ስለሆነ አብራራዋለሁ።

እግዚአብሔር፥ ለእስራኤላውያን አሥርቱ ትእዛዛትን ሰጥቷል። እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን ሕግጋቱን ከጠበቁ ከእነርሱ ጋር

እንደሚሆን፥ እንደሚጠብቃቸውና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንደሚሰጣቸው ተስማምቷል። ሕግጋቱን ካልታዘዙ ግን ቅጣቱ ሞት ነበር። አሁን እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን ኃጢአተኞች እንደሆኑ ሁልጊዜ ትእዛዛቱን ሊጠብቁ እንደማይችሉ ተገነዘበ። እግዚአብሔር፥ እንደማይታዘዙትና አንድ የማምለጫ መንገድ እስከሌላቸው ድረስ ሁሉንም ሊቀጣቸው እንደሚገባ ተረዳ።

ዋና አሳብ፦ እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ሆኖም ግን እግዚአብሔር ስለወደዳቸው ሊያጠፋቸው አልፈለገም። ስለዚህ ከእነርሱ ጋር የሚኖርበት ልዩ ስፍራ እንዲያዘጋጁ ነገራቸው። ወደዚያ እንዲመጡና ሕግጋትን በመተላለፋቸው ከሚገባቸው ቅጣት እንዲድኑ ይፈልግ ነበር።

ስለዚህ እግዚአብሔር፥ ለሙሴ እስራኤላውያን ለዚህ ልዩ ስፍራ ማዘጋጃ መዋጮ እንዲያዋጡና እርሱ ከእነርሱ ጋር የሚኖርበት እነርሱም ለእርሱ የሚሆን መሥዋዕት የሚያቀርቡበትንና እርሱን የሚያመልኩበትን መገናኛ እንዲሠሩ እንዲነግራቸው አዘዘው፤ ዘጸአት 25፡1-8 አንብብ።

እግዚአብሔር ይህን ልዩ ስፍራ እንዲያዘጋጁ ያዘዘው ለራሱ ስለሚያስፈልገው አልነበረም። እግዚአብሔር እንደ እኛ የሆነ አካል የለውም። ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ አይረጥብም፥ አይደክምም፤ ስለዚህ የሚተኛበት ቤት አያስፈልገውም። እርሱ መንፈስ ነው።

በተጨማሪ ይህ ማለት እግዚአብሔር ከዚህ በኋላ በሁሉም ስፍራ አይገኝም ማለት አይደለም። ለሙሴ እንዲሠራ ባዘዘው ልዩ ቦታ ቢገኝ እንኳ በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ መገኘቱን ይቀጥላል።

## መ. የማደሪያው ድንኳ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መንገድ መሠራት ነበረበት።

ዋና አሳብ፦ ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ዕቅድና ፈቃድ ብቻ ነው።

ዘጸአት 25፡9 አንብብ። በዚያ ቦታ እያንዳንዱ ነገር እግዚአብሔር ለሙሴ በተራራው ላይ በነበረበት ጊዜ በነገረው መሠረት በትክክል መሠራት ነበረበት። ሁሉ ነገር በእግዚአብሔር መንገድ መሠራት

ነበረበት። ነገሮችን በእግዚአብሔር መንገድ ለመሥራት ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ስም ታስታውሳላችሁን? አዎን ቃየን! ወደ እግዚአብሔር በትክክለኛ መንገድ ማምጣት ስላልፈቀደ እግዚአብሔር አልተቀበለውም። ኖኅ የሠራው ትልቁ መርከብ እግዚአብሔር በነገረው በትክክለኛ መንገድ መሠራት እንደነበረበት ታስታውሳለህን?

ወደ እርሱ እንዴት መምጣት እንደምንችል ለእግዚአብሔር ልንነግረው አንችልም። ወደ እግዚአብሔር እርሱ ባስተማረን መንገድ መምጣት አለብን። ይህን መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያስተምረናል።

ቤቶቻችሁን ለመሥራት የምትጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች ምን ዓይነት ናቸው?

መምህር ሆይ፡- ይህ ጥያቄ የመገናኛው ድንኳን የተሠራበትን ቁሳቁስ ለመግለጽ የሕዝቡን አእምሮ ለማግኘት የሚያዘጋጅ ነው። እንደዚህ ዓይነት ጥያቄ ከጠየቅካቸው በኋላ ትምህርቱን ከመቀጠልህ በፊት መልስ ለመስጠት እንዲችሉ ጊዜ ስጣቸው።

እስራኤላውያን ቀደምት አባቶቻቸው ወደመጡበት ምድር እየተመለሱ ስለነበር የእናንተ ቤቶች የተሠሩባቸውን ዓይነት ትላልቅ ቁሳቁስ ተጠቅመው ቢሠሩ ቤቱን ይዘውት ሊንቀሳቀሱ አይችሉም ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ያዘዛቸው የመገናኛውን ድንኳን አብዛኛውን ክፍል ከእንስሳት ቆዳና ከፍየሎች ጸጉር እንዲሠሩ ነበር። በጉዞ ላይ እያሉ ይኖሩባቸው የነበሩት ድንኳኖች የተሠሩት ከዚሁ ዓይነት ቁሳቁስ ነበር።

## ሠ. ቅድስተ ቅዱሳን።

እግዚአብሔር፥ ለሙሴ የሚሠሩት ቤት ሁለት ክፍሎች ያሉት እንዲሆን ነገረው። ከውጭ ሲገባ የሚገኘው የመጀመሪያው ክፍል ቅድስት ወይም ልዩ ክፍል በመባል ይታወቅ ነበር። እግዚአብሔር፥ ለተለየ አገልግሎት የለየው ክፍል ነበር። በእግዚአብሔር የተመረጡ ካህናት እግዚአብሔርን በሚያገለግሉበት ጊዜ ብቻ ይጠቀሙበት ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ስለ ካህናት ትማራላችሁ።

ቀጥሎ ያለው ሁለተኛው ክፍል ከመጀመሪያው የበለጠ የላቀ አስፈላጊ ነበር። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ካለው አስፈላጊነት የተነሣ ቅድስተ ቅዱሳን ወይም ፈጽሞ የተለየ ክፍል በመባል ይታወቅ ነበር። ይህ ክፍል ለእግዚአብሔር ብቻ የተለየ ሲሆን ጥቂት ቆይተን እንደምንመለከተው ሊቀካህኑ ብቻ በዓመት አንድ ጊዜ ይገባበት ነበር። የእግዚአብሔር ሕልውና የሚገለጠው በዚህ ክፍል ውስጥ ነበር። በእስራኤላውያን ሠፈር መካከል እግዚአብሔር ሊኖርበት ቃል ኪዳን የገባበት የመገናኛው ድንኳን ልዩ ክፍል ይህ ነበር።

መምህር ሆይ:- በሥዕል ወይም በአምሳያ ንድፍ በመጠቀም የቅድስቱንና የቅድስተ ቅዱሳኑን ክፍል አሳያቸው።

## ረ. ታቦቱና የምሕረት መቀመጫው።

ዘጸአት 25፡10-11 አንብብ። እግዚአብሔር ሕልውናው በሚገለጥበት በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የሚቀመጥ አንድ ሣጥን እንዲሠራ ሙሴን አዘዘው። እግዚአብሔር ለሙሴ ይህ ሣጥን መሠራት ያለበት በእግዚአብሔር በተመረጠ ልዩ ዓይነት እንጨት መሆን እንዳለበት ነገረው። ሣጥኑን ከሠሩ በኋላ በወርቅ መለበጥ ነበረባቸው።

መምህር ሆይ:- አዳማጮችህ ወርቅ ምን እንደሆነ ምናልባት አያውቁም ይሆናል። ከወርቅ የተሠራ ነገር ለማሳየት የጋብቻ ቀለበትህን ተጠቀም።

ዘጸአት 25፡17 አንብብ። ሙሴ የወርቅ መከደኛ እንዲሠራና በውስጠኛው ክፍል ባለው ሣጥን ላይ እንዲያደርገው ታዘዘ። በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ከሚገኙ ነገሮች ሁሉ የላቀ ስፍራ የሚሰጠው ይህ የምሕረት መቀመጫ በመባል የሚጠራው መከደኛ ነበር። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከኃጢአተኛው የእስራኤል ሕዝብ ጋር በመኖር ምሕረቱን የሚያሳይበት ዋና ስፍራ ይህ ነበር።

በምሕረት መቀመጫው ግራና ቀኝ ሁለት ኪሩቤል በወርቅ እንዲሠራ ሙሴ በእግዚአብሔር ታዝዞ ነበር። ዘጸአት 25፡18 አንብብ።

ስለ ኪሩብ (መልአክ) ለመጨረሻ ጊዜ የሰማኸው መቼ እንደነበር ታስታውሳለህን? አዎን እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ከዔድን ገነት ከተባረሩ በኋላ ወደ ዔድን ገነት ተመልሰው እንዳይገቡ በበሩ ላይ

ኪሩብ አቁሞ በነበረ ጊዜ ነው። ከዔድን ገነት ውጭ ይጠብቅ የነበረው ኪሩብ እውነተኛና ሕያው ነበር። ነገር ግን ሙሴ እንዲሠራ የታዘዘው የወርቅ ምስል ነበር።

ዘጸአት 25፡19፥ 20 አንብብ። የሁለቱ ኪሩብ ምስሎች በሣጥኑ ላይ ባለው የምሕረት መቀመጫ ባለበት የሥርየት መክደኛ እርስ በርስ የሚታዩ ተደርጉ መቀመጥ ነበረባቸው። ክንፎቻቸው ወደ እያንዳንዳቸው የተዘረጉ ሆነው የምሕረት መቀመጫ የተባለውን ስፍራ ሊሸፍኑ ይገባ ነበር። ፊታቸው ወደታች ተዘቅዝቆ የሣጥኑን ክዳን የሚመለከት መምሰል ነበረበት።

ዘጸአት 25፡21፥ 22 አንብብ። ይህ ሣጥን በውስጠኛው ክፍል ከመጋረጃው ቀጥሎ የሚቀመጥ ነበር። ሙሴ በሣጥኑ ውስጥ ከምሕረት መቀመጫው በታች አሥርቱ ትእዛዛት የተጻፈባቸውን ሁለቱን ጽላቶች እንዲያስቀምጥ ታዝዞ ነበር። እነዚህም እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ሊሰጣቸው ቃል የገባው ነበር። ኋላ በሌላ ትምህርት እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ስለ ሰጠው ስለ እነዚህ ሁለት ጽላቶች እንማራለን።

እግዚአብሔር፥ ሁሉ ነገር እርሱ ባዘዘው መሠረት በተጠናቀቀ ጊዜ ወደ ውስጠኛው ክፍል እንደሚመጣ ተናገረ። ሕልውናውም በኪሩቦች መካከል በሚያበራው ደማቅ ብርሃን ይረጋገጣል።

ሰ. መጋረጃው።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል። እግዚአብሔር ለሙሴ በሁለቱ ክፍሎች መካከል ይለይ ዘንድ እጅግ የሚያምር ወፍራም መጋረጃ እንዲያደርግ አዘዘው። ይህ መጋረጃ እስራኤላውያን በኃጢአታቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይተው እንዳሉ የሚያሳስብ ነበር ዘጸአት 26፡31-33 አንብብ።

ረ. የናስ መሠዊያ

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማችይል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

እግዚአብሔር፥ የጨርቅ መጋረጃዎችን በሁለቱ ክፍሎች ዙሪያ እንደ አጥር እንዲያቆም ሙሴን አዞት ነበር።

እንደዚሁም በመጋረጃው አጥር መግቢያ ላይ በእንጨት ተሠርቶ በናስ የተለበጠ የናስ መሠዊያ እንዲያኖር ታዞ ነበር፤ ዘጸአት 27፡1፥ 2 አንብብ።

አንድ ሰው የሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ለማቅረብ በሚፈልግበት ጊዜ ወደ ናስ መሠዊያው ሊያመጣው ያስፈልግ ነበር። እጆቹን በእንስሳው ራስ ላይ በማድረግ እንስሳውን ማረድ ነበረበት። ይህን በማድረግ እርሱ ኃጢአተኛ እንደሆነና የእግዚአብሔር ቅጣት የሆነው ሞት እንደሚገባው አምኖ መቀበሉን እና የእንስሳውን ሞት በእርሱ ፈንታ እንዲቀበል እግዚአብሔርን መጠየቁን ያሳያል፤ ዘሌዋውያን 1፡1-5 አንብብ።

እግዚአብሔር በጐችን፥ ፍየሎችን፥ ወይፈኖችን ርግቦችን በመሥዋዕትነት ሊቀበል ይፈቅድ ነበር። ነገር ግን የእንስሳት ደም የኃጢአትን ዋጋ ሊከፍል ይችላልን? አይችልም። የእንስሳት ደም ለኃጢአት መከፈል ያለበትን ቅጣት መግለጫ ብቻ ነበር። ትክክለኛው የኃጢአት ዋጋ የኃጢአተኛው ከእግዚአብሔር መለየት ነው።

## ቀ. አሮንና ልጆቹ ካህናት ተደረጉ።

ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል። እግዚአብሔር፥ ለሙሴ አሮን ሊቀ ካህን ልጆቹ ደግሞ ካህናት እንዲሆኑ አዘዘው፤ ዘጸአት 28፡1 አንብብ።

እግዚአብሔር ወዳለበት እንዲገባ የሚፈቀድለት አሮንን ብቻ ነበር። ከእርሱ ሌላ ማንኛውም ሰው መጋረጃውን አልፎ ወደ ውስጠኛው ክፍል ቢገባ ይሞት ነበር።

አሮን እግዚአብሔር ወዳለበት ወደዚህ ክፍል መግባት የሚችለው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር። አሮን ወደዚህ ስፍራ ሊገባ

የሚችልበት አንዱና ብቸኛው ዓመታዊ ቀን የስርየት ቀን በመባል ይታወቅ ነበር፤ ዘሌዋውያን 16፡2፥ 3።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

አሮን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ከመግባቱ በፊት እንስሳ አርዶ ደሙን በስሃን መያዝ ነበረበት። ሁለቱን ክፍሎች ከለየው ከወፍራሙ መጋረጃ ካለፈ በኋላ የስርየት መቀመጫ በሚባለው በወርቅ መክደኛው ላይ ደሙን ይረጭ ነበር።

ዋና አሳብ፡- ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ለሙሴ በነገረው መሠረት ሁሉ ነገር ከተከናወነ፥ እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን ያለፈ ዓመት ኃጢአት ይቅር ይል ነበር።

የእንስሳት ደም ለኃጢአት ይቅርታ ሊያስገኝ ይችላልን? አይችልም። የእንስሳት ደም የኃጢአትን ዋጋ ሊከፍል አይችልም። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ሲሆን ይህም ኃጢአተኛው ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው የዘላለም የእሳት ፍርድ መሄድን ያጠቃልላል። ኃጢአት ሙሉ በሙሉ መከፈል አለበት። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ይህን የሚገባቸውን ፍርድ ሊያነሣና ያለፈውን ዓመት ኃጢአታቸውን ይቅር ሊል ቃል ገብቶ ነበር። ይህ የሚሆነው ግን እርሱ በተናገረው መንገድ ወደ እግዚአብሔር ከቀረቡ ነበር።

እግዚአብሔር ወደ እርሱ የሚመጡትን የሚቀበለው እርሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በገለጠው መንገድ ሲመጡ ብቻ ነው።

መምህር ሆይ፡- እዚህ ነጥብ ላይ አዳማጮችህ ግልጽ ወደሆነ ውዝግብ ውስጥ የመግባት ሁኔታ ያገጥማቸው ይሆናል። በአንድ በኩል እግዚአብሔር የኃጢአት ዋጋ በሙሉ እንዲከፈል ይፈልጋል ብለን፥ በሌላ በኩል ደግሞ እርሱ ባዘጋጀው መንገድ ወደ እርሱ የሚቀርቡትን የአማኝ እስራኤላውያንን ኃጢአት እግዚአብሔር ይቅር ይላል ማለታችን ተቃራኒ አሳብ ሊመስላቸው ይችላል።

እዚህ ላይ የምናስተምረው የሥርየትን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን በእግዚአብሔር መንገድ ወደ እርሱ የሚመጣ ኃጢአተኛ ሙሉ ይቅርታ አግኝቶ በኃጢአቱ ምክንያት ከነበረበት ፍርድ ነፃ ይሆናል። ነገር ግን እግዚአብሔር ይህን የሚያደርገው ያንን ኃጢአት በጽድቅና በመስቀል ላይ በሚሞተው በኢየሱስ ክርስቶስ የመሥዋዕትነት ደም ጉዳዩን ወደ ፍጻሜ ለማምጣት ስለ ዐቀደ ነው። ጌታ ኢየሱስ በሞተበት ጊዜ እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳን አማኞችን ኃጢአት በሙሉ በእርሱ ላይ አኖረ። እነዚህ ኃጢአቶች በእግዚአብሔር ዘንድ ሳይቀጡ ወይም ዋጋቸው ሳይከፈል ቆይቶ ነበር። (ሮሜ 3፡25፥ ዕብራውያን 9፡15 አንብብ)።

ይህ አወዛጋቢ የሚመስል ነገር በኢየሱስ መስቀል ላይ እንዴት እንደተወገደ ለመግለጽ ተሽቀዳድመህ አትሞክር። በብሉይ ኪዳን የተሠሩና ይቅር የተባሉ ኃጢአቶች እንዴት ዋጋቸው እንደተከፈለ ወደ ፊት እንደሚረዱ ብቻ አረጋግጥላቸው።

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር አሥርቱን ትእዛዛት የጻፈው በምን ላይ ነበር? በሁለት የድንጋይ ጽላቶች ላይ ነበር።

2. እግዚአብሔር፥ ለሙሴ ሕዝቡና እርሱ እንዲሠሩ ያዘዘው ምን ነበር? እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚሆንበትን የማደሪያውን ድንኳን ነበር።

3. እግዚአብሔር የሚኖርበት ቤት ያስፈልገዋልን? እግዚአብሔር መንፈስ ነው ስለዚህ፤ የሚኖርበት ቤት አያስፈልገውም።

4. እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን ይህንን ማደሪያውን እንዲሠሩ ያዘዘው ለምን ነበር? እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን የሰጣቸውን አሥርቱን ትእዛዛትን እንደሚተላለፉ ያውቅ ነበር። የእግዚአብሔርን ይቅርታና ምሕረት የሚቀበሉበትና ወደ እርሱ የሚመጡበት አንድ ስፍራ እስከሌላቸው ድረስ ሁላቸውም በሞት ይቀጡ ነበር።

5. ሁሉን ነገር መሥራት ያለባቸው እንዴት ነበር? እግዚአብሔር ለሙሴ በተራራው ላይ ባዘዘው መሠረት ብቻ መሥራት ነበረባቸው።

6. እግዚአብሔር በዚያ እንዳለ የሚያሳየው ደማቅ ብርሃን የሚታየው በየትኛው ክፍል ነበር? በውስጠኛው ክፍል (በቅድስተ ቅዱሳን) ነበር።

7. በዓመት አንድ ጊዜ ትልቁንና ከባዱን መጋረጃ አልፎ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሊገባ የሚችለው ማን ብቻ ነበር? ሊቀ ካህኑ ነበር።

8. ሊቀ ካህኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሲገባ ከእርሱ ጋር ምን መያዝ ነበረበት? የታረደውን እንስሳ ደም መያዝ ነበረበት።

9. ሊቀ ካህኑ ደሙን ምን ያደርገው ነበር? ከኪሩቡ ሥር በሚገኘው የወርቅ መክደኛና ደማቅ ብርሃን ላይ ሊረጨው ይገባ ነበር።

10. ሊቀ ካህኑ ይህን ካደረገ እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግ ቃል ገብቶለት ነበር? እግዚአብሔር ፍርዱን በማንሳት ለአንድ ተጨማሪ ዓመት ይቅር ይላቸው ነበር።

11. የኃጢአት ደመወዝ በእንስሳት ደም መክፈል እግዚአብሔርን የሚያረካ ነበርን? አልነበረም። የእንስሳት ደም የኃጢአትን ዋጋ ሊከፍል አይችልም።

12. የኃጢአት ብቸኛ ዋጋ ምንድን ነው? የኃጢአተኛው ብቸኛው ዋጋ ሞት ነው። ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለዘላለም መቀጣት ነበረበት።

# ትምህርት 35

የትምህርት ክፍል፡- ዘጸአት 32፡1-20፤ 34፡1፥ 2፤ 39፡42፥ 43፤ 40፡17፥ 34፥ 35

የትምህርቱ ርእስ፡- እግዚአብሔር የጥጃ ምስል በመሥራታቸው በእስራኤላውያን ላይ ፈረደባቸው።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው የመገናኛው ድንኳን ተሠራ

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እስራኤላውያን ያመልኩት ዘንድ የወርቅ ጥጃ ምስል ሠሩ (32፡1-6)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ለ. እግዚአብሔር ለሙሴ እስራኤላውያን የጥጃ ምስል ሠርተው እንዳመለኩ ነገረው (32፡7፥ 8)።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ሐ. ሙሴ፥ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሙሉ እንዳያጠፋ አጥብቆ ለመነ (32፡9-14)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

መ. ሙሴ ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶች ሰበረ (32፡15-19)።

ሠ. ሙሴ የጥጃውን ምስል ሰባብሮ አጠፋው (32፡20)።

ረ. እግዚአብሔር አሥርቱ ትእዛዛትን እንደገና ጻፈ (34፡1፥ 2)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል

ሰ. የመገናኛው ድንኳን ሥራ ተጠናቀቀ፤ እግዚአብሔርም ከሕዝቡ ጋር ይገኝ ዘንድ ወደ መገናኛው ድንኳን መጣ (39፡42፥ 43፤ 40፡17፥ 34፥ 35)።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

የትምህርት 34 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

### ሀ. እስራኤላውያን ያመለኩት ዘንድ የወርቅ ጥጃ ምስል ሠሩ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። እራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሙሴ አሥርቱ ሕግጋት የተጻፈባቸውን ሁለት ጽላቶችና የመገናኛውን ድንኳን አሠራር መመሪያዎች በተራራው ላይ ሆኖ በሚቀበልበት ጊዜ እስራኤላውያን በድንኳኖቻቸው ሆነው ሙሴ ወደ ተራራው ሥር የሚመለስበትን ጊዜ ይጠብቁ ነበር።

ዘጸአት 32፡1-16 አንብብ። እስራኤላውያን፥ እግዚአብሔር የማይቻሉ የሚመስሉ አያሌ አስደናቂ ነገሮችን ሲሠራ ተመልክተዋል። በግብፃውያን ላይ እግዚአብሔር ያወረደውን በርካታ መቅሠፍቶች ተመልክተዋል። እግዚአብሔር የግብፃውያንን በኩራት በሙሉ ሲገደል፥ እነርሱ ግን በበራቸው ጉበንና መቃን ላይ ያደረጉትን ደም ተመልክቶ ልጆቻቸውን እንዳላጠፋባቸው አይተዋል። ከሚያሳድዷቸው የግብፅ ሠራዊት ነፃ ይወጡና ያመልጡ ዘንድ ባሕሩን ከፍሎ ሲያሻግራቸው ተመልክተዋል። የግብፃውያንን ሠራዊት በሙሉ በባሕሩ ሲያሰጥም አይተዋል። ምግብ ከሰማይ ውኃ ደግሞ ከዓለት አውጥቶ ሲሰጣቸው ተመልክተዋል። ከሲና ተራራ ላይ በተናገራቸው ጊዜ ሁሉን ቻይ የሆነውን ኃይሉንና ቅድስናውን ለማሳየት የተጠቀመበትን የመብረቅ ብርሃን፥ ነጐድጓድና ከባድ ደመና ተመልክተዋል። እግዚአብሔር ሲያደርግ የተመለከቷቸው እነኚህ ሁሉ ታላላቅ ነገሮች እያሉ አሁንም እንደገና ፊታቸውን እግዚአብሔርን ከማመን መለሱ። ከወርቅ የጥጃ ምስል ሠሩና ከግብፅ ያወጣን አምላክ ይህ ነው አሉ።

የእግዚአብሔርን ትእዛዙ ጣሱ። እግዚአብሔር፥ ምንም ዓይነት ምስል ለእርሱ ሠርተው እንዳያመልኩ ነግሯቸው ነበር።

ለ. እግዚአብሔር፥ ለሙሴ ሕዝቡ የጥጃ ምስል ሠርቶ እንዳመለከ ነገረው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ዘጸአት 32፡7፥ 8 አንብብ። እስራኤላውያን ምን እያደረጉ እንደነበር ሙሴ ለማየት ችሎ ነበርን? አልነበረም። እግዚአብሔርስ ሊያየው ችሎ ነበርን? ምን እያደረጉ እንደነበር እግዚአብሔር አወቀን? አዎን! እስራኤላውያን የሚያደሩግትን ሁሉ እግዚአብሔር አውቆ ነበር።

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያያል ያውቃል። ከሰዎች ለመደበቅ ብንችልም እንኳ እግዚአብሔር የምናደርገውን ሁሉን ነገር ያውቃል። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ትእዛዙን ጥሰው የተከለከለውን ፍሬ በበሉ ጊዜ አይቶአቸው ነበር። እግዚአብሔር ቃየን አቤልን ሲገድል ተመልክቶ ነበር። እግዚአብሔር በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎች ያድርጉ የነበረውን ክፉ ነገሮች ተመለከተ። እግዚአብሔር የሰዶምና ገሞራ ሰዎችን ክፉ ሥራዎች ተመልክቶ ነበር። እግዚአብሔር፥ ዮሴፍ ወደ ግብፅ በወረደና አባቱ ያዕቆብ እንኳ ሞቷል ብሎ ባሰበ ጊዜ ከእርሱ አልተለየም ነበር። እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን በግብፅ በነበሩበት ጊዜ እነርሱንና ባሪያ አድርጕ የገዛቸውን ክፉ ንጉሥ ተመለከተ። ከእግዚአብሔር የተሰወረ አንዳችም ነገር የለም። ስለእያንዳንዳችን ሁሉን ነገር ያውቃል።

እግዚአብሔር፥ ሙሴ ሊያያቸው ባይችልም እንኳ እስራኤላውያንን ተመለከተ። እስራኤላውያን የወርቅ ጥጃ ምስል ሠርተው እንዳመለኩ ለሙሴ የነገረው እግዚአብሔር ነበር።

ሐ. ሙሴ፥ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሙሉ እንዳያጠፋ አጥብቆ ለመነ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ዘጸአት 32፡9-14 አንብብ። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሙሉ ለምን አላጠፋም?

መምህር ሆይ፡- አዳማጮችህ መልስ ለመስጠት ካልቻሉ ከቁጥር 11-14 ያለውን እንደገና አንብብ። ከዚህ በኋላ ከቻሉ መልስ ለመስጠት ጊዜ ስጣቸው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሙሉ ያልገደለው ለምን እንደሆነ አሁንም መልስ ለመስጠት ካልቻሉ ግን እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን በሙሉ ያላጠፋው ሙሴ እግዚአብሔር ይቅርታ እንዲያደርግላቸው አጥብቆ ስለለመነ መሆኑን ግለጽላቸው። ሙሴ፥ «ጌታ ሆይ፥ ሁላችንንም ካጠፋኸን ግብፃውያን ይህንን ሲሰሙ ምን ይሉናል? ሕዝብህን እስራኤልን ከግብፅ ምድር ያወጣኸውና ወደ እነዚህ ተራራማ ስፍራዎች ያመጣኸው ልታጠፋቸው እንደሆነ አያስቡምን?» በማለት ጸልዮ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ሙሴ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለእስራኤል የገባቸውን የተስፋ ቃሎች እንዲያስብ አሳሰበው። (እስራኤል የሚለው መጠሪያ እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሰጠው አዲስ ስም እንደነበረ ታስታውሳለህን?) ሙሴ እግዚአብሔርን የሚያሳስበው ነገር ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ዘራቸውን በሰማይ እንዳሉ ከዋክብት እንደሚያበዛቸው የገባውን የተስፋ ቃል ነው። ሙሴ፥ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ፈጽሞ እንደማያፈርስ ያውቅ ነበር።

መምህር ሆይ፡- እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን ዘንግቶ ሙሴ እያስታወሰው ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ከተነሣ፥ ጉዳዩ እንደዚያ እንዳይደለ አረጋግጥላቸው። እግዚአብሔር ለሙሴ ይህን ዓይነት ጸሎት እንዲጸልይ አሳሰበው ወይም አሳብን ሰጠው። ነገር ግን እነርሱ ካልጠየቁህ በስተቀር ይህን ጥያቄ አታንሣው።

መ. ሙሴ፥ ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶች ሰበራቸው።

ዘጸአት 32፡15-19 አንብብ። ሙሴ እጅግ ተቆጣ። እስራኤላውያን፥ የጌታን ትእዛዛት በሙሉ ለመፈጸም ቃል ኪዳን የገቡ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጀመሪያዎቹን ሁለት የእግዚአብሔር ትእዛዛት ተላለፉ፤ ዘጸአት 20፡3፥ 4 አንብብ።

ሠ. ሙሴ የጥጃውን ምስል ሰባብሮ አጠፋው።

ሙሴ፥ እስራኤላውያን በወርቅ የሠሩትን የጥጃ ምስል ሰባብሮ አጠፋው፤ ዘጸአት 32፡20 አንብብ።

ረ. ጌታ፥ አሥርቱን ትእዛዛት እንደገና ጻፋቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር፥ ሙሴ የሰባበራቸውን አሥርቱ ትእዛዛት የተጻፉባቸውን ሁለት ጽላቶች ለመተካት አዲስ ጽላት እንዲያዘጋጅ ሙሴን አዘዘው። ዘጸአት 34፡ 1፥ 2 አንብብ።

እግዚአብሔር አሥርቱን ትእዛዛት በአዲሶቹ ጽላቶች ላይ እንደገና ጻፋቸው።

ሰ. የመገናኛው ድንኳ ተሠርቶ አለቀና እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ይኖር ዘንድ ወደዚያ መጣ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር፥ ለሙሴ ከእነርሱ ጋር ይኖር ዘንድ ማደሪያ ስፍራ እንዲሠሩለት እንደነገረው ታስታውሳላችሁን? እስራኤላውያን፥ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ማደሪያ ድንኳኑን ሠሩ። ዘጸአት 39፡42፥ 43፤ 40፡17 አንብብ።

እግዚአብሔር ባዘዛቸው መንገድ ባይሠሩት ኖሮ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ለመኖር ባልመጣ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ሕዝቡና እርሱ ስለሠሩ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ሰፈር መካከል ላይ በነበረው የመገናኛው ድንኳን ለእርሱ ብቻ በተዘጋጀው ልዩ ክፍል ወረደ፤ ዘጸ. 40፡34፥ 35 አንብብ።

እስራኤላውያን እግዚአብሔር ባስተማራቸው መንገድ ወደ እርሱ መምጣት ይችሉ ነበር። በየዓመቱ፥ ሊቀ ካህኑ አሮን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በመግባት በኪሩብ ሥር ባለው የምሕረት መቀመጫ በተባለው ስፍራ ደሙን ይረጭ ነበር።

ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንደምንመጣ ለመወሰን አንችልም። እርሱ ፍጹም ስለሆነ የሚቀበለን እርሱ በቃሉ በተናገረው መንገድ ወደ እርሱ በምንመጣበት ጊዜ ብቻ ነው። የእግዚአብሔርን መልእክት በጥንቃቄ አዳምጡ። እንደ እናንተና እንደ እኛ ያለ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኝበትን ብቸኛ መንገድ ያስተምራችኋል።

## ጥያቄዎች

1. ሙሴ፥ በተራራው ላይ በነበረ ጊዜ እስራኤላውያን ምን ያደርጉ ነበር? የጥጃ ምስል በወርቅ ሠርተው ከግብፅ ያወጣን አምላክ ይህ ነው በማለት ያመልኩ ነበር።

2. ሙሴ፥ እስራኤላውያን ያደረጉትን ነገር ያወቀው እንዴት ነበር? እግዚአብሔር ስለነገረው ነው።

3. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ያላጠፋው ለምን ነበር?

    ሀ. ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ስለ ጸለየ ነበር።

    ለ. ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ለገባቸው ቃል ኪዳናች ታማኝ ስለሆነ ነበር።

4. እግዚአብሔር አሥርቱ ትእዛዛትን የጻፈበትን ሁለት ጽላት ሙሴ በሰበረ ጊዜ እግዚአብሔር ምን እንዲያደርግ አዘዘው? እግዚአብሔር ለሙሴ ሁለት ሌሎች ጽላቶችን እንዲያዘጋጅና ወደ ተራራው እንዲያመጣ አዘዘው። ይህን ያደረገው እንደገና ሊጽፍበት ነበር።

5. እስራኤላውያን እግዚአብሔር ባዘዛቸው መንገድ የማደሪያውን ድንኳን ባይሠሩት ኖሮ እግዚአብሔር ይኖርበት ዘንድ ወደዚያ ይመጣ ነበርን? አይመጣም ነበር።

6. ኃጢአተኞች ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችሉት ባሻቸው መንገድ ነውን? አይደለም። ወደ እግዚአብሔር ዘንድ እርሱ በተናገረው መንገድ ካልመጣን ተቀባይነት አናገኝም።

7. ወደ እግዚአብሔር የሚወስደንን መንገድ እንዴት ለማወቅ እንችላለን? የእግዚአብሔር ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ለማወቅ እንችላለን።

# ትምህርት 36

የትምህርት ክፍል፡- ዘጸአት 40፡36-38፤ ዘኍልቁ 13፡1-3፥ 17-21፥ 25-33፤ 14፡1-10፥ 26-32

አጠቃላይ ርእስ፡- እስራኤላውያን ባለማመናቸው ምክንያት እግዚአብሔር ወደ ከነዓን እንዳይገቡ አደረገ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. ሙሴ የእግዚአብሔር ነቢይ ነበር።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ለ. እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን በደመና ዐምድ መራቸው (ዘጸአት 40፡36-38)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ሐ. የተስፋዪቱን ምድር መሰለል (ዘኍልቁ 13፡1-3፥ 17-21፥ 25)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

መ. ከሰላዮቹ አሥሩ እግዚአብሔርን አላመኑም (ዘኍልቁ 13፡26-29)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሠ. ካሌብና ኢያሱ በእግዚአብሔር አመኑ (ዘኍ. 13፡30)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ረ. እስራኤላውያን በእግዚአብሔር አላመኑም ነበር (ዘኍ. 14፡1-10)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ሰ. እግዚአብሔር ሕዝቡ ሁሉ በምድረ በዳ እንደሚያልቅ ተናገረ (ዘጸአት 14፡26-32)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

የትምህርት 35 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

### ሀ. ሙሴ የእግዚአብሔር ነቢይ ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል

ሙሴ እስራኤላውያንን በሚመራበት ጊዜ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነበር። በእግዚአብሔር ስለ ተመራ፥ እግዚአብሔር እንዲናገር የሚፈልገውን ነገር በትክክል ተናገረ። ሙሴ እግዚአብሔር እንዲጽፍ የሚፈልገውን ነገር ደግሞ ለመጻፍ በእግዚአብሔር ተመራ። እያስተማርናችሁ ያለውን እነዚህን አምስት መጻሕፍት የጻፈው እርሱ ነው።

መምህር ሆይ፡- መጽሐፍ ቅዱስህን በመክፈት ሙሴ የጻፋቸውን አምስት መጻሕፍት አሳያቸው።

### ለ. እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን በደመና ዐምድ መራቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እስራኤላውያን፥ እግዚአብሔር ለአባታቸው ለአብርሃም ቃል ኪዳን ወደ ገባው ምድር ከግብፅ ተነሥተው እየተጓዙ ነበር።

በዚህ መንገድ ከዚህ ቀደም ተጉዘው አያውቁም። የመሄጃውን መንገድ አያውቁትም ነበር። የሚከተሉአቸው መንገዶችም አልነበሩም። ታዲያ ትክክለኛውን መንገድ የሚያውቁት እንዴት ነበር?

ዘጸአት 40፡36-38 አንብብ። እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን ቀን በደመና ማታ ደግሞ በእሳት ዐምድ ይመራቸው ነበር።

እግዚአብሔር፥ እንዲቆሙና እንዲያርፉ በሚፈልግበት ጊዜ ደመናው ይቆም ነበር። እንደገና ጉዞ እንዲጀምሩ ሲፈልግ ከፊት ለፊታቸው ይጓዝ ነበር።

እስራኤላውያን ብዙ ጊዜ ባያምኑትና ባይታዘዙትም እንኳ እግዚአብሔር አልተዋቸውም ነበር።

ሐ. የተስፋዪቱን ምድር መሰለል።

እግዚአብሔር፥ ለእስራኤላውያን አሥርቱን ትእዛዛትና የመገናኛውን ድንኳን መሥሪያ ትእዛዝ ከሰጠበት ከሲና ተራራ ደመናውን አነሣ። ደመናው በሚንቀሳቀስበት ጊዜ እስራኤላውያን እየተከተሉት እግዚአብሔር ሊሰጣቸው ቃል ወደገባላቸው ምድር ድንበር ድረስ መራቸው።

በከነዓን ይኖሩ የነበሩት ሰዎች በጣም መጥፎና ጣዖት አምላኪዎች ስለነበሩ እግዚአብሔር ሊደመስሳቸውና ምድራቸውን ለእስራኤላውያን ሊሰጥ ዐቅዶ ነበር።

መምህር ሆይ፡- እስራኤላውያን በዚህ ጊዜ የት እንደነበሩ ለማመልከት ካርታህን ተጠቀም።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እስራኤላውያን እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሮቹ ሊሰጥ ቃል ወደገባው ምድር ወሰን በደረሱ ጊዜ ከእያንዳንዱ ነገድ አንዳንድ ሰው በአጠቃላይ አሥራ ሁለት ሰዎች እንዲመርጥ እግዚአብሔር ሙሴን አዘዘው። እነዚህ አሥራ ሁለት ሰዎች እስራኤላውያን ወደ ምድሪቱ ከመግባታቸው በፊት ቀድመው ሄደው ምድሪቱን የሚሰልሉ ነበሩ፤ ዘኁልቁ 13፡1፥ 2 አንብብ።

ሙሴ፥ እግዚአብሔርን ታዝዞ ምድሪቱንና በውስጧ የሚኖሩ ሰዎችን እንዲመለከቱ አሥራ ሁለት ሰላዮችን ላከ፤ ዘኁልቁ 13፡3፥ 17-21፥ 25 አንብብ።

መ. ከሰላዮቹ አሥሩ እግዚአብሔርን አላመኑም ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እነዚህ አሥራ ሁለት ሰዎች ሲመለሱ ወደ ሙሴ መጡ። ለእስራኤላውያንም የሚከተለውን ዘገባ አቀረቡ። ዘኍልቁ 13፡26-33 አንብብ።

እነዚህ ሰዎች የሚናገሩት እውነት ነበር። እርግጥ ምድሪቱ በጠንካራ ሰዎች ተይዛ ነበር። አንዳንዶቹም እጅግ ግዙፍ ነበሩ። ሆኖም ግን ከአሥራ ሁለቱ ሰላዮች አሥሩ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገውን ታላላቅና ኃይለኛ ነገር ረስተውት ነበር። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለ ዘነጉ። በግብፅ ያደረገውን ተአምራትና ከባርነት እንዴት ነፃ እንዳወጣቸው ዘነጉ። እግዚአብሔር የከነዓንን ሕዝብ አሸንፎ ምድሪቱን ሊሰጣቸው እንደሚችል አላመኑም ነበር።

## ሠ. ካሌብና ኢያሱ በእግዚአብሔር አምነው ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ሁለቱ ሰላዮች ግን እግዚአብሕር ምድሪቱን ሊሰጣቸው እንደሚችል አምነው ነበር። እነዚህ ሁለት ሰዎች ካሌብና ኢያሱ ነበሩ።

ካሌብና ኢያሱ የከነዓንን ከተሞች የከበቡትን ትላልቅና ጠንካራ የቅጥር ግንቦች ተመልክተው ነበር። ግዙፍ የሆኑትንም ሰዎች ተመልክተው ነበር። ነገር ግን አምላካቸው ሁሉን ቻይና የሚፈልገውን ሁሉ ማድረግ የሚችል እንደሆነ አልዘነጉም ነበር። እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ያደረጋቸውን ታላላቅና ኃያል ነገሮች አስታወሱ። በገባው ቃል መሠረት የከነዓንን ሕዝብ ከዚያች ምድር እንደሚያስወጣና ምድሪቱን ለእስራኤላውያን አሳልፎ እንደሚሰጥ አመኑ። ዘኍልቁ 13፡30 አንብብ።

## ረ. እስራኤላውያን እግዚአብሔርን አላመኑም ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እስራኤላውያን ይከተሉት የነበረው ማንን ይመስላችኋል? እግዚአብሔርን ያላመኑትን አሥሩን ሰላዮች ተከተሉ? ወይስ እግዚአብሔር ምድሪቱን እንደሚሰጣቸው ያመኑትን ካሌብንና ኢያሱን ተከተሉ?

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ዘኍልቁ 14፡1-10 አንብብ። እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን ያደረጉትን ነገር በሙሉ ተመለከተ። እንዳላመኑትም ያውቅ ነበር። ሁኔታቸው እግዚአብሔር ውሸታም እንደሆነ የሚቆጥሩ የሚያስመስል ነበር። እግዚአብሔር ምድሪቱን እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር። ነገር ግን አላመኑትም ነበር።

አንድ ሰው አንድ ነገር ቢነግራችሁና ባታምኑት ሰውዬውን ውሸታም አድርጋችሁ መቁጠራችሁ አይደለምን? አዎን እንደዚያ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ብንሰማና ሳናምነው ብንቀር እግዚአብሔር ውሸታም እንደሆነ አድርገን መቁጠራችን ነው።

ሰ. እግዚአብሔር፥ ሕዝቡ ሁሉ በምድረ በዳ እንደሚያልቅ ተናገረ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ እጅግ ተቆጣ።

ዘኍልቁ 14፡26-32 አንብብ። እስራኤላውያን፥ እግዚአብሔርን ስላላመኑ፥ እግዚአብሔርን ካመኑት ከኢያሱና ከካሌብ በስተቀር ሕዝቡ ሁሉ በምድረ በዳ እንደሚያልቅ እግዚአብሔር ተናገረ። ይህ ትውልድ በሙሉ ካለቀ በኋላ፥ ማለትም ከ40 ዓመታት በኋላ ለልጆቻቸውና እንደዚሁም ለኢያሱና ለካሌብ ምድሪቱን ያወርሳቸው ዘንድ ተናገር።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔርን ያለማመን እጅግ አስከፊ ነገር ነው። ሰይጣን፥ ለሔዋን የነገራት መልካሙንና ክፉውን ከሚያሳውቀው ዛፍ ብትበላ እንደማትሞት ነበር። ሰይጣን፥ እግዚአብሔር ውሸታም ነው አለ!

ሒዋንም አመነችው። ቃየንም እግዚአብሔርን ስላላመነ በራሱ መንገድ ወደ እግዚአብሔር መጣ። እግዚአብሔርም እርሱንና መሥዋዕቱን ሳይቀበል ቀረ። ኖኅ፥ እግዚአብሔር ታላቅ የጥፋት ውኃን ሊልክ እንደሆነ ለሕዝቡ በተናገረ ጊዜ ሕዝቡ ሳይምነው ቀረ። ስለዚህ ወደ ትልቁ መርከብ ሳይገቡ ስለቀሩ በሙሉ ጠፉ። ግብፃውያን የእስራኤል አምላክ እውነተኛና ሁሉን ቻይ እንደሆነ አያምኑም ነበር። ከእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚከላከሉላቸው የሚተማመኑባቸው ጣዖታት ነበሩአቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር ምድራቸውን አጠፋ፥ በኩራቸውን ገደለባቸው፥ ሠራዊታቸውን በባሕር አሰጠመ።

እግዚአብሔር፥ እርሱን ለማመን ያልፈቀዱትን ሁሉ ይቀጣቸዋል። እርሱ ሁልጊዜ እውነትን ስለሚናገር ውሸታም አድርገው የሚያስቡትን ሁሉ ይቀጣቸዋል። የእግዚአብሔርን ቃል ለማመን የማይፈቅዱ ሁሉ እግዚአብሔር ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ አዘጋጀው የዘላለም ቅጣት ስፍራ ይሄዳሉ።

## ጥያቄዎች

1. ሙሴ የጻፋቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መጻሕፍት ስንት ናቸው? ሙሴ የመጀመሪያዎቹን አምስት መጻሕፍት ጽፏል።

2. ሙሴ ምን መጻፍ እንዳለበት ያውቀው እንዴት ነው? እግዚአብሔር የነገረውን ነገር በትክክል እንዲጽፍ እርሱ ራሱ በሚገባ ስለመራው ነው።

3. እስራኤላውያን ወደ የት መሄድ እንዳለባቸው የሚያውቁት እንዴት ነበር? እግዚአብሔር በደመና ይመራቸው ነበር።

4. አሥሩ ሰላዮች እስራኤላውያን ወደ ከነዓን መግባት እንደማይችሉ ያሰቡት ለምን ነበር?

   ሀ. ግዙፍ ሰዎችንና በኃይለኛ ግንብ የተቀጠሩ ከተሞችን አይተው ስለነበር ነው።

   ለ. እግዚአብሔር ምድሪቱን እንደሚሰጣቸው የገባላቸውን የተስፋ ቃል ስላላመኑ ነበር።

5. ካሌብና ኢያሱ፥ እስራኤል ወደ ከነዓን እንደሚገቡ ያመኑት ለምን ነበር? እግዚአብሔር ምድሪቱን እንደሚሰጣቸው በገባው የተስፋ ቃል አምነው ስለነበር ነው።

6. የእግዚአብሔርን ቃል ባናምንና በእርሱ ባንደገፍ እርሱን ምን ማለታችን ነው? እግዚአብሔር ውሸተኛ ነው ማለታችን ነው።

7. እግዚአብሔር፥ እርሱ የተናገረውን ነገር የማያምኑትን ሰዎች ይቀበላልን? አይቀበልም። በእግዚአብሔር የማያምኑ ሰዎች ወደ ዘላለም ቅጣት ይሄዳሉ።

8. እስራኤላውያን፥ እግዚአብሔር ምድሪቱን እንደሚሰጣቸው የሰጣቸውን የተስፋ ቃል ባለማመናቸው ምክንያት የመጣባቸው ቅጣት ምን ነበር? እግዚአብሔር፥ እርሱን የማያምኑ ሁሉ በምድረ በዳ እንደሚቀሩ ተናገረ። ወደ ከነዓን ለመግባት አይችሉም ነበር።

9. እግዚአብሔር ወደ ተስፋዪቱ ምድር ወደ ከነዓን እንደሚገቡ የተናገረው እነማንን ነው?

   ሀ. ካሌብንና ኢያሱን ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን ስላመኑ ነበር።

   ለ. የሚቀጥለውን የእስራኤላውያን ትውልድ ነው።

# ትምህርት 37

የትምህርት ክፍል:- ዘኍልቁ 20፡1-12፥ 23-25፥ 28፥ 21፡4-9።

አጠቃላይ ርእስ:- እግዚአብሔር፥ ለእስራኤላውያን ከዓለት ውኃ አፈለቀላቸው።

እግዚአብሔር፥ ለሙሴ የነሐስ እባብ እንዲሠራ አዘዘው።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች:-

ሀ. እስራኤላውያን ውኃን በማጣታቸው በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ (20፡1-5)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ለ. ሙሴና አሮን የእግዚአብሔርን እርዳታ ጠየቁ (20፡6)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ሐ. እግዚአብሔር ለሙሴ ዓለቱን እንዲናገረው አዘዘው (20፡7፥ 8)።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

መ. ሙሴ እግዚአብሔርን አልታዘዘም (20፡9-11)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሠ. የእግዚአብሔር ቅጣት በሙሴና በአሮን ላይ (20፡12)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ረ. አሮን ሞተ (20፡23-25፥ 28)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ለ. እስራኤላውያን እንደገና አጉረመረሙ (21፡4፥ 5)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሸ. እግዚአብሔር ተናዳፊ እባቦችን ላከ 21፡6፥7)።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ቀ. የናስ እባብ (21፡8፥ 9)።

. እግዚአብሔር፥ አፍቃሪ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

የትምህርት 36 ጥያቄዎችን ከልስ።

የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

ሀ. እስራኤላውያን ውኃ በማጣታቸው በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ዘኍልቁ 20፡1-5 አንብብ። እስራኤላውያን ውኃ በማጣታቸው በሙሴና በወንድሙ በአሮን ላይ አጉረመረሙ።

እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ውኃ ያልጠየቁት ለምን ነበር? ከዚህ ቀደም ውኃ በፈለጉበት ጊዜ እግዚአብሔር ከዓለት ውኃን አፍልቆላቸው ነበር። እግዚአብሔርን ያልጠየቁበት ምክንያት ግን ከዚህ ቀደም ለእነርሱ እጅግ ብዙ ነገር ያደረገላቸው ቢሆንም በእርሱ አልታመኑም ነበርና ነው።

በአሁኑም ዘመን ቢሆን እንደ እስራኤላውያን ያሉ እጅግ ብዙ ተለዋዋጭ ሰዎች አሉ። በየዕለቱ ቀንና ማታ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ እንደሆነ ያሳየናል። በፈጠራቸው ነገሮች እርሱ ማን እንደሆነ ያሳየናል። ፀሐይን፥ ጨረቃንና ከዋክብትን ፈጥሯል። ዝናብንና ነፋስን ይልካል። አዝርዕት ሁሉ እንዲያድጉ የሚያደርግ እርሱ ነው። ነገሮችን ሁሉ የሚቆጣጠረው እርሱ ነው። ይህን ሁሉ ነገር የሰጠን በእርሱ እንድናምን ነው። እግዚአብሔር እውነትን እናውቅ ዘንድ ቃሉን ደግሞ ሰጥቶናል። እግዚአብሔር በየዕለቱ የሚያደርጋቸው እነዚህ ሁሉ ነገሮች እያሉ አብዛኞዎቹ ሕዝቦች እንደ እስራኤላውያን ናቸው። በእግዚአብሔር አያምኑም።

## ለ. ሙሴና አሮን የእግዚአብሔርን እርዳታ ጠየቁ።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ሙሴና አሮን በእግዚአብሔር ስለታመኑ እርዳታ ጠየቁት። ዘኍልቁ 20፡6 አንብብ።

ሙሴና አሮን በምድረ በዳ ውኃ ሊያገኙ እንደማይችሉ ያውቁ ነበር። እግዚአብሔር ባይረዳቸው ኖሮ እስራኤላውያን በሙሉ በውኃ ጥም ያልቁ ነበር።

## ሐ. እግዚአብሔር ለሙሴ ዓለቱን እንዲናገረው አዘዘው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሰው ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

ዘኁልቁ 20፡7፥ 8 አንብብ። እግዚአብሔር፥ ሙሴን ዓለቱን እንዲናገረው አዘዘው። ከዚህ ቀደም ውኃ ባስፈለጋቸው ወቅት እግዚአብሔር፥ ሙሴን ዓለቱን እንዲመታ አዞት ነበር። አሁን ግን ዓለቱን እንዲናገረው ብቻ አዘዘው። ሁልጊዜ፥ እግዚአብሔር እንዳለው መፈጸም ነበረበት።

መ. ሙሴ፥ እግዚአብሔርን አልታዘዘም።

ዋና አሳብ:- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ምን እንደሆነ አድምጡ። ዘኁልቁ 20፡9-11 አንብብ።

ሙሴና አሮን በእስራኤላውያን ላይ ተቆጡ። ሙሴና አሮን ከዚህ ቀደም ችግር በሚያጋጥማቸው ጊዜ እንደሚያደርጉት አላደረጉም። በዚህ ጊዜ በእግዚአብሔር ሳይታመኑ ቀሩ።

ሙሴ እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ዓለቱን መታው።

ሠ. የእግዚአብሔር ቅጣት በሙሴና በአሮን ላይ።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ሙሴና አሮን ተቆጥተው እግዚአብሔርን ሳይታዘዙ ስለቀሩ ወደ ከነዓን ምድር እንደማይገቡ እግዚአብሔር ነገራቸው። ዘኁልቁ 20፡12 አንብብ።

ረ. አሮን ሞተ።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር፥ አሮንን ወደ ከነዓን ምድር እንዲገባ እንደማይፈቅድ ተናገረ። እግዚአብሔር፥ ለሙሴ አሮንን ወደ ተራራው ጫፍ አጠገብ ወዳለው ስፍራ እንዲወስደው ነገረው። ዘኁልቁ 20፡23-25፥ 28 አንብብ። አሮን በተራራው ላይ ሞተ፥ በምድረ በዳም ተቀበረ። እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ ወደ ሰጠው ምድር ሳይገባ ቀረ።

. እግዚአብሔር ሁልጊዜ የተናገረውን ይፈጽማል።

. የአሮን ልጅ የሊቀ ካህንነቱን ስፍራ ተረከበ።

ሰ. እስራኤላውያን እንደገና አጉረመረሙ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር፥ ለእስራኤላውያን የሚያስፈልጋቸውን ውኃ ሰጥቶአቸው ነበር። ነገር ግን ያደረገላቸውን ነገር ወዲያውኑ ዘንግተው እንደገና ማጉረምረም ጀመሩ። ዘኁልቁ 21፡4፥ 5 አንብብ።

## ሸ. እግዚአብሔር የሚናደፉ እባቦችን ላከባቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ይሆን ዘንድ ደንግጓል።

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ስለቀጣቸው ብዙዎቹ ሞቱ። ዘኁልቁ 21፡6 አንብብ። እስራኤላውያን በእባቦቹ እየተነደፉ አለቁ። ይህ የሆነው እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ስለሠሩት ኃጢአት እየቀጣቸው ስለነበር ነው።

እንደዚሁም ሰዎች ሁሉ በሰይጣንና በኃጢአት ስለተነደፉ ለእግዚአብሔር የሞቱ ናቸው። ሰይጣን እባብ ነው ማለቴ አይደለም፥ አይደለምም። ሰይጣንና ኃጢአት ነድፈውናል ስል በዘይቤያዊ አነጋገር መጠቀሜ ብቻ ነው። በሰይጣንና በኃጢአት ምክንያት፥ አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ዘንድ የሞቱ ሆኑ። ከእግዚአብሔር ተለዩ፤ እኛም ደግሞ ኃጢአተኞች ሆነን የተወለድነውና ለእግዚአብሔር የሞትንና ከእርሱ የተለየን የሆነው በሰይጣንና በኃጢአት ምክንያት ነው።

መምህር ሆይ፡- ዕብራውያን 2፡14፥ 15 ተመልከት።

እስራኤላውያን እግዚአብሔር ከላከባቸው ተናዳፊ እባቦች ማምለጥ አልቻሉም ነበር። እባቦቹ በሁሉም ስፍራ ነበሩ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ለመቅጣት ሲወስን ከእርሱ ሊደበቁ የሚችሉበት አንዳችም ስፍራ የለም። በኖኅ ዘመን እግዚአብሔር የመርከቡን በር በዘጋና የጥፋት ውኃን በላከ ጊዜ ሰዎች ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያመልጡ የሚችሉበት ስፍራ ነበርን? እግዚአብሔር፥ በሰዶምና ገሞራ ላይ እሳትና ዲን በላከ ጊዜ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያመልጥ ችሎ ነበረን? የሎጥ ሚስት እግዚአብሔርን መታዘዝ አቅቶአት ወደ ኋላ በተመለከተች ጊዜ ከእግዚአብሔር ፍርድ

ለማምለጥ ቻለችን? እግዚአብሔር ሰዎችን ሊቀጣ በሚወስንበት ጊዜ ቅጣቱ የተወሰነባቸው ሰዎች ከእግዚአብሔር ለማምለጥ ሊሰወሩ የሚችሉበት ስፍራ የለም።

ዋና አሳብ፡- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

እስቲ! እስራኤላውያን፥ እግዚአብሔር ተናዳፊ እባቦችን ለኃጢአት ፍርድ በላከባቸው ጊዜ ምን ያደረጉ ይመስልሃል? በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን ዝንባሌ ፈጥነው በመለወጥ ኃጢአት ማድረጋቸውን አመኑ። ዘኁልቁ 21፡7 አንብብ።

ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያድናቸው የሚችል እርሱ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ወዲያውኑ ስለተገነዘቡ ሙሴ ከእግዚአብሔር እርዳታን እንዲለምን ጠየቁት።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እስራኤላውያን ራሳቸውን መርዳት አይችሉም ነበር። ሙሴም ራሱ ከእባቦች ሊያድናቸው አይችልም ነበር። ሊያድናቸው የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነበር።

ቀ. የናስ እባብ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

እግዚአብሔር ምሕረትን የተሞላ ስለሆነ ይቅር ሊላቸውና ሊያድናቸው ወሰነ። የእግዚአብሔር እርዳታ የማይገባቸው ነበሩ። ነገር ግን በእርሱ የታመኑበትን ሁሉ አዳናቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን ከሞት ይድኑ ዘንድ እነርሱም ሆኑ ራሱም ሙሴ ጭምር ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው ነገረው። ዘኁልቁ 21፡8 አንብብ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ይድኑ ዘንድ የራሳቸውን መንገድ እንዲፈልጉ አልነገራቸውም። እግዚአብሔር፥ ለሙሴ ምን ማድረግ እንዳለበት

ነገረው። ሙሴ እግዚአብሔር የነገረውን ሊያደርግና ሕዝቡ ደግሞ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ወደ ናሱ እባብ መመልከት ነበረበት። ጉዳዩ መፈጸም ያለበት በእግዚአብሔር መንገድ ነበር። ዘኁልቁ 21፡9 አንብብ።

ዋና አሳብ፡- ሰው፥ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር፥ ሕዝቡ ከተነደፈበት እባባ መርዝ ይድን ዘንድ ምን ያድርግ አለ? አዎን! ወደ ናሱ እባብ መመልከት ብቻ ነበረባቸው። የተሰቀለው የናስ እባብ እነርሱን የሚያድን ኃይል ነበረውን? በጭራሽ! እባቡ ምንም ኃይል አልነበረውም። በእግዚአብሔር በመታመን የተሰቀለውን እባብ የተመለከቱትን እስራኤላውያን ሁሉ የፈወሰው የእግዚአብሔር ኃይል ነበር።

እግዚአብሔር የፈወሳቸው ደግሞ በእርሱ ስላመኑ ብቻ ነበር።

ሕዝቡ ወደተሰቀለው የናስ እባብ ሳይመለከቱ ቢጸልዩ ይድኑ የነበሩ ይመስልሃልን? አይድኑም ነበር። ወደተሰቀለው እባብ ሳይመለከቱ ለእግዚአብሔር ስጦታን ቢሰጡ ኖሮ ይድኑ ነበርን? በጭራሽ! እግዚአብሔር እንደተናገረ ወደ ናሱ እባብ መመልከት ነበረባቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ወደ ናሱ እባብ ተመልከተው ያልዳኑ ሰዎች የነበሩ ይመስልሃልን? አልነበሩም። እግዚአብሔር ሁልጊዜ የተስፋ ቃሎቹን ይጠብቃል። ወደ ናሱ እባብ የተመለከቱት ሰዎች ሁሉ ወዲያውኑ ተፈወሱ። እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ እንደሚፈጽም ልንታመንበት ይገባል።

መምህር ሆይ፡- ሕዝቡ ወደ ናሱ እባብ እየተመለከተ ሳለ የሚያሳይ ሥዕል አሳያቸው። የናሱ እባብ ምንም ኃይል እንደሌለው በሚገባ መረዳታቸውን እርግጠኛ ሁን። በእግዚአብሔር ታምነው ወደ ናሱ እባብ የተመለከቱትን ሁሉ እግዚአብሔር እንዳዳናቸው ለመናገር ትኩረት አድርግ።

## ጥያቄዎች

1. እስራኤላውያን ውኃ ሲያስፈልጋቸው ምን ማድረግ ይችሉ ነበር? በጌታ ሊታመኑ ይችሉ ነበር።

2. እግዚአብሔር፥ ሙሴና አሮን ወደ ተስፋዪቱ ምድር አይገቡም ያለው ለምን ነበር?

   ሀ. በእግዚአብሔር ስላልታመኑ ነበር።

   ለ. ስለተቆጡ ነበር።

   ሐ. ሙሴ እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ዓለቱን ስለመታ ነበር።

3. እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን ባለማመናቸው ምክንያት ምን አደረጋቸው? እግዚአብሔር ተናዳፊ እባቦችን ልኮ ብዙ ሰዎች እንዲያልቁ አደረገ።

4. እንደ እባብ ሰዎችን ሁሉ በመናደፉ ወደ ዓለም ሞትን ያመጣው ማን ነበር? ሰይጣን ነበር።

5. ሰይጣን፥ ወደ ሰዎች ሁሉ ሞትን ያመጣው እንዴት ነበር? ሰይጣን፥ አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን እንዲሠሩና እነርሱም ሆኑ እኛ ሁላችን እንድንሞት አደረገ።

6. እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን ከሞት ይድኑ ዘንድ ለሙሴ ምን ነገረው? የናስ እባብ ሠርቶ እንዲሰቅል ነገረው።

7. በእባብ የተነደፉት ሰዎች ይድኑ ዘንድ ምን ማድረግ ነበረባቸው? የተሰቀለውን እባብ መመልከት ነበረባቸው።

8. የናሱ እባብ ወደ እርሱ የሚመለከቱትን ለማዳን ልዩ ተአምራዊ ኃይል ነበረውን? አልነበረውም።

9. ወደ ናሱ እባብ የተመለከቱትን ማን ፈወሳቸው? እግዚአብሔር ፈወሳቸው።

10. ሆኖም ግን ሊፈወሱ ይገባቸው ነበርን? አይገባቸውም ነበር። ኃጢአተኞች ስለሆኑ መሞት ነበረባቸው።

11. እግዚአብሔር፥ ወደ ናሱ እባብ የተመለከቱትን ሁሉ የፈወሰው ለምን ነበር?

ሀ. እርሱ አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ስለነበር።

ለ. የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል አምነው በቃሉ መሠረት ስለታዘዙ ነበር።

12. ወደተሰቀለው የናስ እባብ ተመልክቶ የሞተ ሰው ነበርን? በፍጹም አልነበረም። እግዚአብሔር ሁልጊዜ የተናገረውን ያደርጋል።

# ትምህርት 38

የትምህርት ክፍል፡- ዘኁልቁ 27፡18-23፤ ዘዳግም 34፡1-5፥ 9፤ ኢያሱ 1፡1፥ 2፤ 11፡23፤ መሳፍንት 2፡7-19፤ 1ኛ ሳሙኤል 8፡1-7፤ 11፡14-15

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደ ተስፋዪቱ ምድር ወሰዳቸው።

## የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት አሳቦች፡-

ሀ. ኢያሱ፥ ሙሴን እንዲተካ ተሾመ (ዘኁልቁ 27፡18-23)።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ለ. የእግዚአብሔር ቃል ተፈጸመ።

1. ሙሴ ሞተ (ዘዳግም 34፡1-5)

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

2. ያላመኑ እስራኤላውያን በምድረ በዳ አለቁ።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ሐ. ኢያሱ እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን መራ (ዘዳግም 34፡9፤ ኢያሱ 1፡1-2፤ 11፡23)

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

መ. እስራኤላውያን ከኢያሱ ሞት በኋላ ወደ ጣዖት አምልኮ ዘወር አሉ (መሳፍንት 2፡7-15)።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. ሰይጣን ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው። ሰውን ይጠላል።

- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።
- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ሠ. የመሳፍንት ዘመን (መሳፍንት 2፡ 16-19)።

- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።
- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።
- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ረ. ሳሙኤል (1ኛ ሳሙኤል 8፡ 1-7)

- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።
- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሰ. የመጀመሪያው ንጉሥ ሳኦል (1ኛ ሳሙኤል 11፡ 14፥ 15)።

የትምህርት 37 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

### ሀ. ኢያሱ፥ ሙሴን እንዲተካ ተሾመ

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር፥ ለእስራኤላውያን ባለማመናቸው ምክንያት ወደ ተስፋዪቱ ምድር እንደማይገቡ ከተናገራቸው አርባ ዓመታት አለፉ። እግዚአብሔር እንደገና ሊሰጣቸው ቃል ኪዳን ወደ ገባላቸው ምድር ድንበር አመጣቸው። እስካሁን ድረስ በመሪነት የሚያገለግላቸው ሰው ሙሴ ነበር። እግዚአብሔር፥ ሙሴ ወደ ተስፋዪቱ ምድር እንዲገባ ፈቀደለትን? አልፈቀደም። እግዚአብሔር፥ ለሙሴ ወደ ተስፋዪቱ ምድር እንደማይገባ ነግሮት ነበር። ይህን ለምን እንዳደረገ ታስታውሳላችሁን?

እስራኤላውያን ወደ ተስፋዪቱ ምድር የሚገቡበት ጊዜ ቢደርስም እግዚአብሔር ሙሴ እንዳይገባ ወስኖ ስለነበር፥ እስራኤላውያን አዲስ

መሪ ያስፈልጋቸው ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ለሙሴ ረዳቱ የነበረውን ኢያሱን አዲሱ የእስራኤል ሕዝብ መሪ አድርጎ እንዲሾመው ነገረው። ዘኍልቁ 27፡ 18-23 አንብብ።

ለ. የእግዚአብሔር ቃል ተፈጸመ።

1. ሙሴ ሞተ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር፥ ሙሴን ከከነዓን አጠገብ ወደሚገኝ የተራራ ጫፍ ላይ እንዲሄድ ነገረው። በዚህ የተራራ ጫፍ ላይ እግዚአብሔር፥ ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ተስፋ የገባውን ምድር ለሙሴ አሳየው። ዘዳግም 34፡ 1-5 አንብብ።

ሙሴ፥ በዚህ ተራራ ጫፍ ላይ ሞተ። እግዚአብሔር፥ ለእስራኤል ተስፋ ወደገባው ምድር ሙሴ እንዲገባ አልፈቀደለትም። እግዚአብሔር የተናገረውን አደረገ።

እግዚአብሔር ከሁሉም የላቀ ነው። የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ያደርጋል።

2. ያላመኑ እስራኤላውያን በምድረ በዳ አለቁ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

እስራኤላውያን በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት ተንከራተቱ። እግዚአብሔር የተስፋዪቱን ምድር እንደሚሰጣቸው ያላመኑ እስራኤላውያን በሙሉ በምድረ በዳ አለቁ። ይህ ቃሉን ስላላመኑ እግዚአብሔር የፈጸመባቸው ቅጣት ነበር።

ለእስራኤላውያን የእግዚአብሔር ቃል በሙሴ በኩል እንደተሰጣቸው ሁሉ፥ ለእናንተም አሁን የእግዚአብሔር ቃል በእኛ በኩል እየተሰጣችሁ ነው። በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የእግዚአብሔር ቃል እያስተማርናችሁ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ለማመን የማይፈቅዱ ሰዎች ሁሉ ይቀጣሉ፥ ይሞታሉ። ከዚያም በኋላ

እግዚአብሔር ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወዳዘጋጀው ስፍራ ይሄዳሉ። የማያምኑ ሰዎች ከእግዚአብሔር ለዘላለም ይለያሉ።

መምህር ሆይ:- ዕብራይውን 4 ተመልከት።

## ሐ. ኢያሱ፥ እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን መራ።

ኢያሱ አዲሱ የእስራኤል ሕዝብ መሪ ሆነ። ዘዳግም 34:9 አንብብ።

እግዚአብሔርን ያላመኑት ሰዎች ልጆች አሁን ጐልማሳ ሆነዋል። ስለዚህ አሁን እነርሱን ወደ ከነዓን ይወስድ ዘንድ የእግዚአብሔር ጊዜ ነበር። ኢያሱ 1:1፥ 2 አንብብ።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ኢያሱ፥ እስራኤላውያንን ወደ ከነዓን መራ። እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ ቃል ኪዳን የገባውን ምድር ሰጣቸው። ሰይጣንና የግብፅ ንጉሥ እስራኤላውያን ግብፅን እንዳይለቁ ለማድረግ ቢሞክሩም፥እንደዚሁም እስራኤላውያን ደግሞ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን የተጠራጠሩት ቢሆንም እግዚአብሔር ተስፋ የገባውን ቃል ፈጸመ። በቀይ ባሕር የሚያልፉበትን መንገድ በማመቻቸት መራቸው፥ ጠበቃቸው። ደግሞም በምድረ በዳ በተንከራተቱባቸው 40 ዓመታት ምግብና ውኃን ሰጣቸው። እግዚአብሔር ያደርግላቸው ዘንድ ተስፋ ከሰጣቸው ነገሮች ያላደረገው ነገር ፈጽሞ የለም። ኢያሱ 11:23 አንብብ።

## መ. እስራኤላውያን፥ ኢያሱ ከሞተ በኋላ ወደ ጣዖት አምልኮ ተመለሱ።

ዋና አሳብ:- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሰይጣን እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው። ሰውንም ይጠላል።

ኢያሱ በሕይወት እያለ፥ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን አልረሱም። ነገር ግን ኢያሱና እግዚአብሔር በምድረ በዳ ያደረጋቸውን ተአምራት አይተው የነበሩት በሙሉ ከሞቱ በኋላ

የተነሣው ትውልድ እግዚአብሔርን ረሳ። ይህም ትውልድ እውነተኛና ሕያው የሆነውን አምላክ የማያውቁትንና ቃሉ የሌላቸውን የሌሎች ጐረቤት ሕዝቦች መንገዶች ተከተለ። ጣዖታትን በመሥራት በእግዚአብሔር ፈንታ አመለካቸው። መሳፍንት 2፥7-13 አንብብ።

ከእስራኤላውያን አጠገብ ይኖሩ የነበሩ ክፉና ኃጢአተኛ ሰዎች በአልና አስታሮት የተባሉ ጣዖታትን ያመልኩ ነበር። የሚያመልኳቸው ጣዖታት እውነተኛ ወይም ሕያው አልነበሩም። ሕዝቡ እውነተኛና ሕያው እንደነበሩ ቢያስቡም እንኳ ተታለው ነበር። ሰይጣን አታሎአቸው እነዚህን ሐሰተኛ አማልክት እንዲያመልኩ አድርጐ ነበር። ሕዝቡ ግን ሰይጣንና መላእክቱን እያመለኩ እንደነበር አያውቁም ነበር።

ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ከተነገረለት ከእውነተኛውና ሕያው አምላክ ሌላ ሌሎች አማልክትን፥ መናፍስትን፥ የቀደምት አባቶቻቸውን መናፍስት ወይም ማናቸውንም ሌሎች ነገሮች ሲያመልኩ ሰይጣንን እያመለኩ ነው ማለት ነው። ሰይጣን ራሱን ለውጦ በተለያየ መልክ ደብቆ ያቀርባል። በጣዖታት፥ በመናፍስት፥ በቀደምት አባቶች መናፍስትና ሰዎች በሚያመልኩአቸው ሌሎች ነገሮች በስተጀርባ ይደበቃል። ሔዋንን በፈተናት ጊዜ ከእባብ በስተጀርባ ተደብቆ የቀረበው በዚህ ዓይነት ነበር። ሰይጣን፥ እግዚአብሔርን ይጠላል። ስለዚህ ማንም ሰው እግዚአብሔርን እንዲያመልክ አይፈልግም። ሰይጣን ሰዎችን ሁሉ ይጠላል። ማንኛውም ሰው እግዚአብሔርን አምኖ ከሞት ነፃ እንዲወጣ አይፈልግም።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን እርሱን ረስተው ጣዖታትን ስላመለኩ ቀጣቸው። እግዚአብሔር፥ በእስራኤላውያኑ ዙሪያ ያሉትንና ይጠሏቸው የነበሩትን አሕዛብ በማስነሣት እንዲያሸንፏቸውና ባሪያዎች እንዲያደርጓቸው ፈቀደላቸው። መሳፍንት 2፥14፥ 15 አንብብ።

እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን እርሱን ካልታዘዙና እርሱን ብቻ ካላመለኩ ይህ እንደሚፈጸምባቸው አስጠንቅቆአቸው ነበር።

እግዚአብሔር አይለወጥም። የቱንም ያህል ዓመታት ቢያልፉም እርሱ ግን የሰጠውን የተስፋ ቃልና ማስጠንቀቂያ አይረሳም።

ሠ. የመሳፍንት ዘመን።

በቅደም ተከተል ማሳያ ሠንጠረዥ ላይ «መሳፍንት» የሚለውን ቃል አሳይ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

እስራኤላውያን ንስሐ በገቡ ጊዜ ሁሉ፥ ማለትም ስለ ኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር ጋር ተስማምተው ይረዳቸው ዘንድ ወደ እርሱ በጮኹ ቁጥር፥ እርሱም የሚመራቸውና ከጠላቶቻቸው ነፃ የሚያደርጋቸው ወንድ ወይም ሴት መሪ ያስነሣላቸው ነበር። እስራኤልን ለመምራት በእግዚአብሔር የተመረጡት እነኚህ ሰዎች መሳፍንት በመባል ይጠሩ ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ነገር ግን እስራኤላውያን ደግመው ደጋግመው እግዚአብሔርን ረሱ። ስለዚህ በጠላቶቻቸው በተደጋጋሚ እንዲሸነፉ እግዚአብሔር ፈቀደ። መሳፍንት 2፡16-19 አንብብ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው ቅጣት የሚገባቸው ሆነው እግዚአብሔር የቀጣቸው ቢሆንም፥ ዳሩ ግን እርሱ ለእነርሱ ያለው ፍቅርና እንክብካቤ አልተለወጠም ነበር።

እግዚአብሔር በዔድን ገነት ሰይጣንን የሚደመስስና ዓለምን ከሰይጣን ኃይል ነፃ የሚያደርግ አዳኝ እንደሚልክ የተስፋ ቃል ሰጥቶ ነበር። ይህን የነፃ አውጪ ተስፋ ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብም በድጋሚ ሰጥቷል። ይህ አዳኝ ከእነርሱ ዘር የሚመጣ እንደሆነም ነግሯቸውል። አዳኙ የሚመጣው ከእነርሱ ዘር እንደሆነ በመናገሩም፥እግዚአብሔር የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ ዘር የሆኑትን እስራኤላውያንን ጠበቀ።

በተጨማሪም እግዚአብሔር ዓለም ስለ እርሱ እንድታውቅ ይፈልግ ነበር። እግዚአብሔርን ማወቅ የምንችለው በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት ብቻ ነው። እግዚአብሔር አብዛኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሰጠው በእስራኤል በኩል ነበር። እግዚአብሔር የተመረጡ እስራኤላውያንን መልእክቱን ለመጻፍ ተጠቀመባቸው።

እግዚአብሔር፥ እስራኤልን የጠበቀው ቃሉንና የነፃ አውጪውን ታሪክ ለእናንተ ለማስተማር እንዲችል ነው። እግዚአብሔር ቃሉን እንድትሰሙ የፈለገው ወደ እርሱ እንድትመጡና የእርሱ ሕዝብ እንድትሆኑ ነው።

ረ. ሳሙኤል።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

በዚህ ወቅት ለእስራኤላውያን የእግዚአብሔር መልእክተኛ ከነበሩት ሰዎች አንዱ ሳሙኤል ነበር። ሳሙኤል፥ የመጨረሻው የእስራኤል መስፍን ነበር።

ሳሙኤል፥ ዕድሜው በገፋ ጊዜ ስፍራውን የሚወስድ ሰው አልነበረም። ልጆቹ እግዚአብሔርን የሚታዘዙ አልነበሩም። 1ኛ ሳሙኤል 8፡ 1-3 አንብብ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን ከግብፅ ነፃ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ ንጉሣቸውና ሉዓላዊ ገዢያቸው ነበር። እስራኤላውያን ከሌላው አሕዛብ የሚለዩበት ነገር ምድራዊ ንጉሥ ስላልነበራቸው ነበር። ነገር ግን በዙሪያቸው የነበሩ አሕዛብ ንጉሥ ስለነበራቸው እነርሱም በላያቸው ላይ የሚነግሥ ሰው ፈለጉ። 1ኛ ሳሙኤል 8፡4-7 አንብብ። እስራኤላውያን በላያቸው ገዥ የሚሆን ንጉሥ መፈለጋቸው እግዚአብሔር ንጉሣችን እንዲሆን አንፈልግም ማለታቸው ነበር።

ሰ. የመጀመሪያው ንጉሥ ሳኦል።

እግዚአብሔር ንጉሥን ሰጣቸው። ስሙም ሳኦል ይባል ነበር። በእስራኤል ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የተሾመ የመጀመሪያው ሰው ሳኦል ነበር። 1ኛ ሳሙኤል 11፡ 14፥ 15 አንብብ።

በቅደም ተከተል ማግያ ሰንጠረዥ ላይ «ሳኦል፥ ዳዊት፥ ሰሎሞን» የሚሉትን ስሞች ጻፍ።

## ጥያቄዎች

1. ከሙሴ ሞት በኋላ የእስራኤል መሪ ማን ሆነ? ኢያሱ።

2. እግዚአብሔር፥ ከሙሴ ሞት በኋላ እስራኤላውያንን በፍጥነት ወደ ከነዓን ምድር የመራቸው ለምን ነበር? ምክንያቱም እግዚአብሔርን ያላመኑት ጐልማሶች በሙሉ በምድረ በዳ አልቀው ስለነበር ነው።

3. እግዚአብሔር፥ ለአብርሃም ዘሮች ተስፋ የገባላቸውን ምድር ሰጣቸውን? አዎን! እግዚአብሔር የገባውን የተስፋ ቃል በመጠበቅ ምድራቸውን ሰጣቸው።

4. እስራኤላውያን፥ ከኢያሱ ሞት በኋላ ምን አደረጉ? ከእግዚአብሔር ዘወር በማለት በአካባቢያቸው እንዳሉትና እውነተኛውንና ሕያው የሆነውን አምላክ እንደማያውቁት ቃሉም እንደሌላቸው ሰዎች ጣዖታትን አመለኩ።

5. ሰዎች፥ ጣዖታትን፥ መናፍስትን፥ የቀደምት አባቶች መናፍስትንና ሌሎች የተፈጠሩ ነገሮችን እንዲያመልኩ የሚያታልላቸው ማን ነው? ሰይጣን ነው።

6. እውነተኛና ሕያው ከሆነው አምላክ ሌላ ማናቸውንም ነገር ወይም ማንኛውንም ሰው ብናመልክ በእርግጥ እያመለክን ያለነው ማንን ነው? ሰይጣንንና መናፍስቱን ነው።

7. ሰይጣን፥ ሰዎችን ጣዖታትን፥ መናፍስትን የቀደምት አባቶቻቸውን መናፍስትና ሌሎች ነገሮችን እንዲያመልኩ የሚያደርገው ለምንድን ነው?

   ሀ. ምክንያቱም ሰይጣን እግዚአብሔርን ስለሚጠላ ማንም እግዚአብሔርን እንዲያመልክ ስለማይፈልግ ነው።

   ለ. ምክንያቱም፥ ሰይጣን ሰዎችን ሁሉ ስለሚጠላ በእግዚአብሔር ታምነው ከሞት ነፃ እንዲወጡ ስለማይፈልግ ነው።

ሐ. ምክንያቱም፥ ሰይጣን ራሱን ሸፍኖ በማቅረብ ሰዎችን ለማጭበርበር በበርካታ ዘዴዎች ስለሚጠቀም ነው።

8. እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያንን ጣዖታትን በማምለካቸው የቀጣቸው እንዴት ነበር? እግዚአብሔር ጠላቶቻቸው እንዲያሸንፏቸው በማድረግ ቀጣቸው።

9. እስራኤላውያን ስሕተታቸውን አምነው እግዚአብሔር ነፃ እንዲያወጣቸው በጠየቁ ጊዜ እግዚአብሔር ምን አደረገ? እግዚአብሔር፥ መሳፍንት በመባል የሚታወቁትን ወንዶችና ሴቶች ከመካከላቸው በመሪነት በማስነሣት፥ ከጠላቶቻቸው ጋር እንዲዋጉና ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ በማድረግ ይረዳቸው ነበር።

10. ከእስራኤላውያን መሳፍንት መካከል በዋናነት የሚጠቀስ አንድ መስፍን ማን ነበር? ሳሙኤል።

11. እስራኤላውያን፥ ሳሙኤል ከመሞቱ በፊት ምን እንዲያደርግላቸው ጠየቁት? በዙሪያቸው እንዳሉት እንደቀሩት አሕዛብ ንጉሥ ይኖራቸው ዘንድ ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው ጠየቁት።

12. ይህ የእስራኤላውያን ጥያቄ ሳሙኤልን ደስ ያላሰኘው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን ሰው እንዲያነግሥላቸው በመጠየቃቸው ነበር። ይህን ጥያቄ በማቅረብ ትክክለኛውን ንጉሣቸውን እግዚአብሔርን መተዋቸው ነበር።

# ትምህርት 39

የትምህርት ክፍል፡- 1ኛ ሳሙኤል 13፡13፥ 14፤ 16፡1-5፥ 11-13፤ 2ኛ ሳሙኤል 5፡1-4፤ 7፡1-3፥ 12-17፤ 1ኛ ዜና 22፡5፥ 6፤ 29፡26-28፤ 2ኛ ዜና 2፡1፤ 5፡1

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር፥ በሳኦል ምትክ ዳዊትን መረጠ። እግዚአብሔር የቤተ መቅደሱን ሕንፃ ሥራ እንዲሠራ ሰሎሞንን መረጠ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. ሳኦል፥ እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ ቀረ (1ኛ ሳሙኤል 13፡13፥ 14)።

- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።
- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ለ. ዳዊት በእግዚአብሔር የተቀባ ንጉሥ ነበር (1ኛ ሳሙኤል 16፡1-5፥ 11-13፤ 2ኛ ሳሙኤል 5፡1-4)።

- ሰው፥ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ሐ. ዳዊት ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ዐቀደ። (2ኛ ሳሙኤል 7፡1-3)።

- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

መ. እግዚአብሔር ለዳዊት ቃል ኪዳን ገባ (2ኛ ሳሙኤል 7፡12-17)።

- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ሠ. ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠራ። (2ኛ ዜና 22፡5፥ 6፤ 29፡26-28፤ 2ኛ ዜና 2፡1፤ 5፡1)።

- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚመጣው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ረ. ከሰሎሞን ሞት በኋላ በእስራኤል ላይ ብዙ ነገሥታት ነግሠዋል።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

የትምህርት 38 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱ አስተዋጽኦና ትምህርቱን ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

### ሀ. ሳኦል እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ ቀረ።

ዋና አሳብ:- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው

እግዚአብሔር፥ በእስራኤል ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ ሳኦልን መርጦ ስለሾመው ይታዘዘው ዘንድ ይጠብቅ ነበር። ሳኦል ግን እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ ቀረ። ስለዚህ እግዚአብሔር በሳኦል እግር የሚተካ ሌላ ሰው መረጠ። 1ኛ ሳሙኤል 3፡13፥ 14 አንብብ።

### ለ. ዳዊት በእግዚአብሔር የተቀባ ንጉሥ ነበር

ዋና አሳብ:- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ከሳኦል ሞት በኋላ ሁለተኛው የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት ሆነ። 1ኛ ሳሙኤል 16፡1-5፥ 11-13 2ኛ ሳሙኤል 5፡1-4 አንብብ።

ዳዊት ከሳኦል የተለየ ዓይነት ሰው ነበር። በእውነት እግዚአብሔርን የሚያምንና በሁሉም ነገር ሊታዘዘው የሚፈልግ ሰው ነበር።

ዳዊት ልክ እንደ እኛ ኃጢአተኛ ሆኖ ከእግዚአብሔር ተለይቶ የተወለደ ሰው ነበር። ነገር ግን ዳዊት ኃጢአተኛ እንደሆነና የኃጢአት

ደመወዝ ሞት እንደሆነ ያውቅ ነበር።ብቸኛ ተስፋው የእግዚአብሔር ምሕረትና ይቅርታ እንደሆነ ያውቅ ነበር። ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ለኃጢአቱ ይቅርታ የደም መሥዋዕት አቀረበ። ዳዊት በእግዚአብሔር ስለ ታመነ፥ እንደ አቤል፥ ሄኖክ፥ ኖኅ፥ አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ፥ ሙሴና ኢያሱ፥ እንዲሁም እንደሌሎቹ አማንያን ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትንና ይቅርታን አገኘ።

ዳዊት፥ ከእግዚአብሔር ነቢያት አንዱ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ነገሮችን ጽፏል። ዳዊት፥ እግዚአብሔርን ስለፍቅሩና ምሕረቱ የሚያወድሱ በርካታ መዝሙሮችን ጽፏል።

መምህር ሆይ፡- ለአድማጮችህ የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍን በማሳየት ከዳዊት ጽሑፎች አንዳንዶቹን አመልክታቸው።

## ሐ. ዳዊት ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ዐቀደ

ዳዊት ንጉሥ ስለነበር እጅግ ሃብታም ሰው ነበር። እጅግ ውብ በሆነ በዝግባ፥ በከበረ ድንጋይ፥ በወርቅ እና በብር በተሠራ ቤት ውስጥ ይኖር ነበር። አንድ ቀን ዳዊት ስለሚኖርበት እጅግ ውብ የሆነ መኖሪያው በማሰብ ላይ እንዳለ የእግዚአብሔር ማደሪያ ግን በምድረ በዳ የነበረው ከእንስሳት ቆዳዎችና ከመጋረጃ ጨርቅ የተሠራ ድንኳን መሆኑ ታወሰው። የእግዚአብሔር ቤት አሁንም ያው እስራኤላውያን በሲና ተራራ በነበሩበት ወቅት የሠሩት የማደሪያ ድንኳን ነበር።

ስለዚህ፥ ዳዊት ለእግዚአብሔር ቋሚ የሆነ ውብ ቤት ለመሥራት ዐቀደ። የሚሠራው ቤተ መቅደስ በዝግባ፥ በከበረ ድንጋይ፥ በብርና በወርቅ የታነፀ እንዲሆን አሰበ።

ለመሆኑ እግዚአብሔር የሚኖርበት ቤት ያስፈልገው ነበርን? አያስፈልገውም ነበር! ነገር ግን የዳዊት ፍላጐት ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክና መሥዋዕታቸውን ለማቅረብ ሊመጡ የሚችሉበት ቋሚ ቤት መሥራት ነበር።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ዳዊት ይህን ለማድረግ በማቀዱ እግዚአብሔር እጅግ በጣም ደስ ተሰኘ። ስለዚህ ጌታ ከነቢያቱ አንዱን ወደ ዳዊት በመላክ ለእግዚአብሔር ከዝግባና ከከበረ ድንጋይ የሚታነፅ ቋሚ ቤት

ለመሥራት በማቀዱ እንደሚስማማ ነገረው። 2ኛ ሳሙኤል 7፡1-3 አንብብ።

## መ. እግዚአብሔር ለዳዊት የገባው ቃል ኪዳን

እግዚአብሔር፥ ለዳዊት የእግዚአብሔርን ቤት እንዲሠራ ለእርሱ ባይፈቅድለትም እንኳ እስራኤላውያን መሥዋዕታቸውን የሚያቀርቡበትንና እግዚአብሔርን የሚያመልኩበትን ይህን አዲስ ቤት ልጁ እንደሚሠራ ነገረው። 2ኛ ሳሙኤል 7፡ 12-17 አንብብ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የሰጠውን ተስፋ ለዳዊትም ሰጠው። እግዚአብሔር ለዳዊት በገባው ቃል ኪዳን ታላቁ የሰው ነፃ አውጪና ሰይጣንን ድል የሚነሳው አዳኝ ከእርሱ ቤተሰብ እንደሚወጣ ነገረው። ይህ ታላቅ የዳዊት ዘር ለዘላለም እንደ ንጉሥ እንደሚገዛ ነገረው። እግዚአብሔር ነፃ አውጪ እንደሚልክ የገባውን ቃል ፈጽሞ ዘንግቶ አያውቅም።

## ሠ. ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠራ።

የእግዚአብሔር ቤት በኢየሩሳሌም ይገነባ ዘንድ የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች በሙሉ ዳዊት አዘጋጀ።

ኢየሩሳሌም በእስራኤል ተራራማ ስፍራዎች የምትገኝ እጅግ ታላቅ ከተማ ነበረች። ኢየሩሳሌምና በዘመኑ የሚገኙ ከተሞች በሙሉ ከጠላቶቻቸው ይጠበቁ ዘንድ በትላልቅ ግንቦች የተቀጠሩ ነበሩ።

መምህር ሆይ፡- ኢየሩሳሌም በየት እንደምትገኝ ከካርታ ላይ አሳያቸው። የኢየሩሳሌምን ከተማና ቅጥሮችዋን የሚያሳይ ሥዕል አሳያቸው።

ዳዊት ከመሞቱ በፊት የእግዚአብሔርን ቤት የመገንባት ኃላፊነቱን ለልጁ ለሰሎሞን ሰጠው። 1ኛ ዜና 22፡5፥ 6 አንብብ።

ሰሎሞን፥ አባቱ ዳዊት ከሞተ በኋላ በእስራኤል ሁሉ ላይ ንጉሥ ሆነ። 1ኛ ዜና 29፡26-28 አንብብ።

ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤት በኢየሩሳሌም ሠራ። 2ኛ ዜና 2፡1፤ 5፡1 አንብብ።

አሁን የእግዚአብሔር ቤት ስለተሠራ እስራኤላውያን በምድረ በዳ ከቆዳና ከጨርቅ የሠሩት ድንኳን አያስፈልግም ነበር።

ይህ አዲሱ የእግዚአብሔር ቤት ቤተ መቅደስ በመባል ይታወቅ ነበር። የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በምድረ በዳ እንደነበረው የመገናኛ ድንኳን ሁሉ ሁለት ውስጠኛ ክፍሎች ነበሩት። ወፍራሙ የጨርቅ መጋረጃ የእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ በነበረው በውስጠኛው ክፍል ፊት ለፊት ተሰቅሎ ነበር። ይህ መጋረጃ ከሊቀ ካህኑ በስተቀር ማንም ሰው ወደ ውስጥ እንዳያልፍ የሚያደርግ ነበር። ደማቁ ብርሃን በውስጠኛው ክፍል ነበር። ምክንያቱም በምድር ላይ ያለ የእግዚአብሔር ልዩ ስፍራ ያ ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

ሊቀ ካህኑ ሕዝቡን ሁሉ ወክሎ በዓመት አንድ ጊዜ ወደዚህ ውስጠኛ ክፍል ማለትም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንዲገባ ይፈቀድለት ነበር። እስራኤላውያን በራሳቸው ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት አይችሉም ነበር። ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉበት ብቸኛ መንገድ በሊቀ ካህኑና በመሥዋዕትነት በሚያቀርበው የእንስሳ ደም አማካይነት ብቻ ነበር። ሊቀ ካህኑ በየዓመቱ የእንስሳ ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ በመግባት በሁለቱ ኪሩቤል መካከል ባለው የምሕረት መቀመጫ በሚባለው የወርቅ መክደኛ ላይ ይረጨው ነበር።

እስራኤላውያን ኃጢአተኞች መሆናቸውን፥ እግዚአብሔር ፍጹም እንደሆነና የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንደሆነ ፈጽሞ መዘንጋት አልነበረባቸውም። የእንስሳት ደም የኃጢአት ዋጋ መሆን ስለማይችል በየዓመቱ ደሙን በመሠዊያ ላይ ማድረግ ነበረባቸው። በየዓመቱ እግዚአብሔር ይቅር ሊላቸውና ፍርዱን ለማዘግየት ተስፋ ሰጥቶ ነበር።

ይህ የሚቀጠለው ለኃጢአት ፍጹምና ሙሉ ዋጋ እስከሚከፈለበት ጊዜ ነበር።

ረ. ከሰሎሞን ሞት በኋላ በርካታ ነገሥታት በእስራኤል ላይ ነግሠው ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ከሰሎሞን ሞት በኋላ የእስራኤል ሕዝብ ማን ንጉሥ ይሁን በሚለው አሳብ ላይ ስለተለያዩ እስራኤል ለሁለት መንግሥታት ተከፈለች።

አሥሩ የሰሜን ነገዶች እስራኤል ሲባሉ፥ ሁለቱ የደቡብ ነገዶች ይሁዳ ተባሉ።

በርካታ ነገሥታት በይሁዳ ላይ የነገሡ ሲሆን፥ እንደዚሁም ደግሞ በእስራኤልም ላይ ብዙዎቹ ነግሠዋል። ከእነዚህ ነገሥታት መካከል እጅግ ጥቂቶቹ የእግዚአብሔርን ቃል በማመን በቃሉ የተደገፉ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ግን የእግዚአብሔርን ቃል አላመኑም ነበር። ጣዖታትን በማምለክ የይሁዳና የእስራኤል ሕዝቦች በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ ኃጢአትን እንዲያደርጉ መሯቸው።

በቅደም ተከተል ማሳያ ሠንጠረዥ ላይ :- ነገሥታት፥ ዮናስ፥ ነቢያት የሚሉትን ቃላት አሳይ።

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር፥ የመጀመሪያው ንጉሥ ሳኦል እንዳልታዘዘ ባየ ጊዜ በእስራኤል ላይ እንዲነግሥ ማንን ሾመ? ዳዊትን።
2. ዳዊት ከሳኦል የሚለየው እንዴት ነበር?

   ሀ. ዳዊት፥ እግዚአብሔርን አመነ ታዘዘም።

   ለ. ዳዊት፥ ኃጢአተኛ ስለመሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር በመስማማትና የመሥዋዕትን ደም በማቅረብ እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር እንደሚለውና እንደሚቀበለው ተማመነ።

3. እግዚአብሔር ለዳዊት የገባው እጅግ ጠቃሚ ቃል ኪዳን ምን ነበር? ከዘሩ አንዱ ነፃ አውጪው እንደሚሆን እግዚአብሔር ለዳዊት ቃል ኪዳን ገባለት።

4. ዳዊት የራሱን ቤት ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ ምን ወሰነ? ዳዊት በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስን ለመሥራት ወሰነ።

5. ዳዊት የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሠራን? አልሠራም። ልጁ ሰሎሞን ሠራው።

6. ይህ አዲሱ ቤተ መቅደስ እስራኤላውያን በምድረ በዳ በሲና ተራራ ሠርተውት ከነበረው የመገናኛ ድንኳን ጋር የሚመሳሰልበት ምን ነገር ነበር?

   ሀ. ሁለት ውስጠኛ ክፍሎች ነበሩት?

   ለ. ከሊቀ ካህኑ በስተቀር ማንም ወደ ውስጥ እንዳያልፍ የሚከለክል እጅግ ትልቅ ወፍራም መጋረጃ ነበረው።

7. ሊቀ ካህኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንዲገባ የሚፈቀድለት መቼ ነበር? በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር።

8. ሊቀ ካህኑ በቅድስተ ቅዱሳን ምን ያደርግ ነበር? ሊቀ ካህኑ የእንስሳት ደም በሁለቱ ኪሩቤል መካከል ባለው የምሕረት መቀመጫ በተባለው የወርቅ መከደኛ ላይ ይረጭ ነበር።

9. የእንስሳት ደም የእስራኤልን የኃጢአትን ዋጋ ሊከፍል ይችል ነበርን?

   ሀ. አይችልም ነበር። ኃጢአት በኃጢአተኛው ሞት ሊከፈል ይገባል።

   ለ. የእንስሳት ደም ለኃጢአት ሙሉ ዋጋ እስከሚከፈል ድረስ የሚቀርብ ጊዜያዊ መሥዋዕት ነበር።

10. ሊቀ ካህኑ በስርየት መከደኛው ላይ ደም በሚረጭበት ጊዜ እግዚአብሔር ምን ያደርግ ነበር?

ሀ. እግዚአብሔር ባለፈው ዓመት እስራኤላውያን የሠሩትን ኃጢአት ይቅር ይል ነበር።

ለ. የኃጢአት ዋጋ በሙላት እስኪከፈል ድረስ እግዚአብሔር ፍርዱን ያቆይ ነበር።

11. ንጉሥ ሰሎሞን ከሞተ በኋላ ምን ሆነ? የሰሜኑ አሥር ነገዶች ከደቡቡ ሁለት ነገዶች ተለይተው የራሳቸውን መንግሥት መሠረቱ።

## ትምህርት 40

የትምህርት ክፍል፡- ዮናስ 1፤ 2፡1፥ 10፤ 3፡1፡1-5፥ 10፤ ኢሳይያስ 10፡5፥ 6፤ ኤርምያስ 20፡5

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር ዮናስንና ሌሎች ሰዎችን መልእክተኞቹ ይሆኑ ዘንድ መረጣቸው።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች፡-

ሀ. እግዚአብሔር፥ ከመጀመሪያው ጀምሮ ለሰዎች ተናግሯል።

- እግዚአብሔር፥ አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።
- እግዚአብሔር፥ ከሰዎች ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ለ. እግዚአብሔር ለዮናስ እንዲያደርግለት የሚፈልገውን ነገረው (ዮናስ 1፡1፥ 2)።

- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ሐ. ዮናስ፥ እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ ቀረ (ዮናስ 1፡3-10)።

- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።
- እግዚአብሔር፥ በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

መ. ዮናስ፥ በትልቅ ዓሣ ተዋጠ (ዮናስ 1፡11-17)።

- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።
- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ሠ. እግዚአብሔር፥ ዮናስን ታደገው (ዮናስ 2፡1፥ 10)።

- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።
- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ረ. እግዚአብሔር ትእዛዙን ለዮናስ ደገመለት (ዮናስ 3፡1፥ 2)።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ሰ. ዮናስ ታዘዘ፥ የነነዌ ሰዎችም ንስሐ ገቡ (ዮናስ 3፡3-5፥ 10)።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

ሸ. የነቢያት መልእክት (ኢሳያይስ 10፡5፥ 6፤ ኤርምያስ 20፡5)

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

. ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

የትምህርት 39 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

### ሀ. እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ጀምሮ ለሰዎች ተናግሯል።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው። እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

በዓለም ላይ የሚገኙ ሰዎችን በሙሉ የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ስለሚወድ በሁሉም ስፍራ የሚገኙ ሰዎች ከሰይጣን፥ ከኃጢአትና ከሞት ነፃ እንዲወጡ ይፈልጋል። ስለዚህ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እግዚአብሔር ሰዎች ፈቃዱን ያውቁ ዘንድ ለሰዎች ተናገረ። እግዚአብሔር ለአዳም፥ ለሔዋን፥ ለቃየንና ለኖኅ ተናገረ። እግዚአብሔር ለኖኅ፥ ሰዎች ሁሉ ንስሐ እንዲገቡና በእርሱ እንዲያምኑ እንደሚፈልግ እንዲነግር መልእክቱን ሰጠው።

እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ለይስሐቅ፥ ለያዕቆብና ለዮሴፍ ተናገረ። እግዚአብሔር መልእክቱን ለሙሴ በመስጠት ለፈርዖንና ለእስራኤላውያን እንዲነግር አደረገ። እግዚአብሔር፥ ሙሴ እስራኤላውያንን ወደ ተስፋዪቱ ምድር በሚመራበት ጊዜ ሁሉ ለእርሱ መናገሩን አላቋረጠም ነበር። እግዚአብሔር፥ ከሲና ተራራ ጫፍ ላይ ሆኖ ለእስራኤላውያን በመናገር ትእዛዛቱን ሰጣቸው። እግዚአብሔር፥ መልእክተኞቹን ወደ እስራኤልና ይሁዳ በመላክ መንገዶቹን እንዲያስተምሩና በኃጢአት ላይ ስለሚያመጣው ፍርድ እንዲያስጠነቅቁአቸው አድርጓል። እግዚአብሔር፥ አንዳንዶቹን መልእክተኞቹን ደግሞ ከእስራኤል ምድር አጠገብ ወደሚኖሩ ሌሎች ሕዝቦች ይልክ ነበር።

## ለ. እግዚአብሔር ለዮናስ እንዲያደርግለት የሚፈልገው ነገረው

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር፥ አንድ ቀን ዮናስ ለሚባል እስራኤላዊ ተናገረ። የእግዚአብሔርን መልእክት ነነዌ ወደተባለች አንዲት ክፉ ከተማ ይዞ እንዲሄድ ነገረው፤ ዮናስ 1:1፥ 2 አንብብ።

መምህር ሆይ:- በካርታ ላይ የነነዌን ከተማ አሳያቸው።

## ሐ. ዮናስ፥ እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ ቀረ።

ዋና አሳብ:- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

በነነዌ የሚኖሩት አሦራውያን ነበሩ። እነርሱም የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ ዝርያዎች አልነበሩም። የእስራኤላውያን ጠላቶች ነበሩ።

ዮናስ፥ የእግዚአብሔርን መልእክት ወደ ነነዌ ሕዝቦች መውሰድ ያልፈለገው ንስሐ እንዲገቡና ከእግዚአብሔር ፍርድ እንዲያመልጡ ስለማይፈልግ ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ ቀረ፤ ዮናስ 1:3-10 አንብብ።

መምህር ሆይ:- የምታነበው በግልጽ እንዲሰማ አድርገህ አንብብ። እያነበብክ ያለውን ነገር አዳማጮችህ መረዳታቸውን

ለማረጋገጥ አልፎ አልፎ በምንባብህ መሃል ጥያቄዎችን ጠይቃቸው።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

ዮናስ ከእግዚአብሔር ለመደበቅ ችሎ ነበርን? ባሕር አቋርጦ በመሄድ ከእግዚአብሔር ለማምለጥ ቻለን? እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የለምን?

እግዚአብሔር፥ የምድር ሁሉ ፈጣሪ ባለቤትና ተቆጣጣሪ ነው። እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው ቅርብ ነው። ማንም ከእርሱ ማምለጥ አይችልም። ሰይጣንና መናፍስትም ቢሆኑ ከእርሱ ማምለጥ አይችሉም። ሁሉንም ይቆጣጠራቸዋል።

ንጉሥ ዳዊት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ለሁሉ ሰው ቅርብ እንደሆነና ከእርሱ ማንም ማምለጥ እንደማይችል ተናግሯል። መዝሙር (139)፡ 1-18 አንብብ።

## መ. ዮናስ በትልቅ ዓሣ ተዋጠ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

አሁን በዮናስ ላይ ምን እንደተፈጸመ እናነባለን። ዮናስ 1፡11-17 አንብብ።

እግዚአብሔር፥ ዮናስን የሚውጥ ትልቅ ዓሣ አዘጋጀ።

በመጀመሪያ ሁሉን ነገር የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። ለእግዚአብሔር የሚሳነው አንዳችም ነገር የለም።

ዮናስ፥ በዚያ ትልቅ ዓሣ ውስጥ ለሦስት ቀናትና ለሦስት ሌሊት አደረ። ከዚያ መውጣት አይችልም ነበር። ሊያድነው የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነበር።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ተስፋ ቢስና ረዳት የለሽ የሆነው የዮናስ ሁኔታ እናንተ ኃጢአተኛ ሆናችሁ ከምትታዩበት ሁኔታ የተለየ አልነበረም። ዮናስ ከዓሣ ነባሪው

ሆድ ውስጥ በመውጣት ራሱን ለማዳን የማይችል እንደነበር፥ እናንተም በሰይጣን ኃይል ሕይወታችሁን ከሚቆጣጠረው ኃጢአትና ከእግዚአብሔር ፍርድ ራሳችሁን ነፃ ለማድረግ አትችሉም። ሊያድናችሁ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

## ሠ. ዮናስን፥ እግዚአብሔር ነፃ አወጣው።

ዋና አሳብ:- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

እግዚአብሔር፥ አፍቃሪ፥ ምህረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ዮናስ 2፡1 አንብብ። ዮናስ፥ ራሱን ማዳን እንደማይችል ከዓሣ ነባሪው ሆድ ሊያወጣው የሚችል እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ አምኖ ተቀበለ። ባለመታዘዙ ምክንያት ንስሐ በመግባት እግዚአብሔር ነፃ ያወጣው ዘንድ እርዳታ ጠየቀ። እግዚአብሔር፥ ዮናስን በዓሣ ነባሪው ሆድ ውስጥ ከሞት አዳነው። ዮናስ 2፡10 አንብብ።

እግዚአብሔር፥ ከእርሱ ጋር የሚስማሙትን፥ በእርሱ ላይ የሚደገፉትንና ከፍርዱ ማምለጥ እንደማይችሉ የሚያምኑትን ሁሉ ያድናል። እግዚአብሔር፥ ኖኅን ያዳነው በእርሱ ስለታመነ ነው። እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን ንስሐ ገብተው የእርሱን እርዳታ በጠየቁበት ጊዜ ሁሉ ያድናቸው ነበር።

## ረ. እግዚአብሔር ትእዛዙን ለዮናስ ደገመለት።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እግዚአብሔር፥ ዮናስ ባይታዘዘውም እንኳ አልተለወጠም። እግዚአብሔር፥ አሁንም በድጋሚ ዮናስን ወደ ነነዌ እንዲሄድ አዘዘው። ዮናስ 3፡1፥ 2 አንብብ።

እግዚአብሔር፥ ቃሉን ቸል ብንል እንኳ እኛን መቅጣት አይዘነጋም። እርሱ አይለወጥም። በዮናስ ዘመን እንደነበረው ዛሬም ያው ነው። መልእክቱን ለመስማት ፈቃደኛ ባለመሆን ከእግዚአብሔር ማምለጥ አንችልም። ኃጢአተኞችን በሙሉ ይፈርድባቸዋል፥ ይቀጣቸዋልም። ማንም ማምለጥ አይችልም። እግዚአብሔር አይለወጥም።

ሰ. ዮናስ ታዘዘ፥ የነነዌ ሰዎችም ንስሐ ገቡ።

ዋና አሳብ:- ሰው፥ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

በዚህ ጊዜ፥ ዮናስ እግዚአብሔርን በመታዘዝ የእግዚአብሔርን መልእክት ለነነዌ ሕዝብ ለመናገር ወደ ነነዌ ሄደ። ዮናስ 3፡3-5፥ 10 አንብብ። የነነዌ ሰዎች በዮናስ አማካይነት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን መልእክት አመኑና ንስሐ ገቡ። ከእግዚአብሔር ጋር በመስማማት ምሕረቱን ለመኑ።

እግዚአብሔር እንደ ነነዌ ሕዝብ እንድትሆኑ ይፈልጋል። መልእክቱን እንድታምኑ፥ ንስሐ እንድትገቡና ከእርሱ ፍርድ የምታመልጡበትን መንገድ እንዲያሳያችሁ በእርሱ እንድትታመኑ ይፈልጋል።

መምህር ሆይ:- ማቅ ብዙ ጊዜ ከፍየል ቆዳ የሚሠራ ጥቁር የሐዘን ልብስ እንደሆነ ግለጽላቸው። ለሞቱ ሰዎች ለሚደረግ ሐዘን ለግላዊና ለብሔራዊ ጥፋት ወይም በኃጢአት ለመጸጸት የሚለበስ ልብስ ነበር።

ሸ. የነቢያት መልእክት።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

እግዚአብሔር፥ ለእስራኤልና ለይሁዳ መልእክቱን የሚያደርሱ ሌሎች በርካታ ሰዎችን መርጦ ነበር። አንዳንዶቹ የእግዚአብሔርን መልእክት ለአካባቢው አገሮችም ይናገሩ ነበር። ታዋቂ ከሆኑት የእግዚአብሔር መልእክተኞች መካከል ኢሳይያስ፥ ኤርምያስ፥ ሕዝቅኤልና ዳንኤል ይገኙበታል።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

የእግዚአብሔር መልእክተኞች ነቢያት በመባል ይታወቃሉ። እነኝህ ነቢያት ለሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡ፥ ጣዖቶቻቸውን እንዲያጠፉና በእግዚአብሔር ብቻ እንዲታመኑ ይነግሯቸው ነበር። በቤተ መቅደስ

ውስጥ ያመልኩ ከነበሩት እስራኤላውያን አብዛኛዎቹ ጣዖታትንም ያመልኩ ነበር። እግዚአብሔር ፈጽሞ ከእነርሱ ጋር እንደማይስማማ ነግሮአቸው ነበር። ማንን እንደሚያገለግሉ መምረጥ ነበረባቸው።

እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሰዎች ከልባቸው ሊያደርጉት ይገባ ነበር፥ አምልኮአቸውም እንደ እግዚአብሔር ቃል መሆን ነበረበት። እውነተኛው አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሌላ መንፈስ ወይም ጣዖት ከሚያመልኩ ሰዎች የሚቀርብለትን አምልኮ አይቀበልም።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው። እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንዲሆን ደንግጓል።

የእግዚአብሔር መልእክተኞች እስራኤላውያንን በሙሴ በኩል የተሰጣቸውን ሕግጋት ያስታውሷቸው ነበር። እስራኤላውያን፥ እነዚህን ሕግጋት ተላልፈው ነበር። የእግዚአብሔር መልእክተኞች ሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡ አለበለዚያ ግን እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው ያሳውቁአቸው ነበር። ሆኖም ባለመመለሳቸው እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እንዲዋጉአቸው ይልክባቸው ነበር። እነዚህም ጠላቶቻቸው ተዋግተው ካሸነፏቸው በኋላ በምርኮኛነት ይወስዱአቸው ነበር። እስራኤላውያንም ቋንቋቸውን በማያውቋቸው ሕዝቦች መካከል ባሪያዎች ይሆኑ ነበር።

ኢሳይያስ፥ የሰሜኑን የእስራኤልን መንግሥት አሥር ነገዶች ንስሐ ካልገቡ እግዚአብሔር አሦራውያንን እንደሚልክባቸውና ድል እንደሚያደርጓቸው ተናግሮ ነበር። (እግዚአብሔር ዮናስን በላከ ጊዜ አሦራውያን ንስሐ የገቡ ቢሆንም የእስራኤልን አምላክ መከተል አልቀጠሉም) ኢሳይያስ 10፡5፥ 6 አንብብ።

ኤርምያስ፥ የኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ሕዝቦች እግዚአብሔር ባቢሎናውያንን ልኮ እንደሚያጠፋቸው በመናገር አስጠነቀቃቸው። ኤርምያስ 20፡5 አንብብ።

እግዚአብሔር አልተለወጠም። እውነተኛና ሕያው አምላክ እርሱ ብቻ ነው። እርሱ ፈጣሪያችን ነው፥ ከእርሱ ሌላ የሚያመልኩትን ወይም የሚያገለግሉትን ይቀጣል።

መምህር ሆይ፡- በካርታ ላይ ነነዌንና ባቢሎንን አሳያቸው።

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ሰዎችን መልእክተኞች እንዲሆኑት የሚጠራው ለምን ነበር? እግዚአብሔር ሕዝቦቹን ሁሉ ስለሚወድ እውነትን እንዲያውቁና ከሰይጣን፥ ከኃጢአትና ከሞት ነፃ እንዲወጡ ስለሚፈልግ ነው።

2. እግዚአብሔር፥ ዮናስ በአሦር ወደምትገኘው ነነዌ እንዲሄድ የፈለገው ለምን ነበር? ሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡና ከተማዪቱ ከመጥፋት እንድትድን ለማስጠንቀቅ ነበር።

3. እግዚአብሔር፥ ዮናስ ሳይታዘዘው ሲቀር ምን አደረገ? ዮናስን የሚውጥ ትልቅ ዓሣ አዘጋጀና እንዲውጠው አደረገ።

4. ዮናስ፥ ከዋጠው ዓሣ ራሱን ለማዳን ይችል ነበርን? አይችልም ነበር። ዮናስ ራሱን ለማዳን የማይቻለው ነበር።

5. ራሳችሁን ከሰይጣን ኃይል፥ ከኃጢአት ቁጥጥርና ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማዳን የምትችሉበት መንገድ አለን? ፈጽሞ የለም።

6. ዮናስን ሊያድን የሚችል ማን ብቻ ነበር? እግዚአብሔር።

7. ከሰይጣን ኃይል፥ ከኃጢአት የበላይ ቁጥጥርና ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያድናችሁ የሚችለው ብቸኛው ኃይል ማን ነው? እግዚአብሔር ብቻ ነው።

8. ዮናስ፥ ንስሐ በገባና በእግዚአብሔር በታመነ ጊዜ እግዚአብሔር ምን አደረገ? ዮናስን የዋጠው ትልቁ ዓሣ መልሶ ወደ ምድር እንዲተፋው አደረገ።

9. እግዚአብሔር፥ አሳቡን ለውጦ ዮናስ ወደ ነነዌ መሄድ እንደሌለበት ወሰነን? በጭራሽ! እግዚአብሔር አይለወጥም። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ትክክለኛውን ነገር ያደርጋል።

10. የነነዌ ሰዎች ዮናስ የእግዚአብሔርን መልእክት ባመጣላቸው ጊዜ ንስሐ ገቡን? አዎን።

11. እግዚአብሔር፥ የነነዌን ሰዎች አጠፋቸውን? አላጠፋቸውም። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር አልቀጣቸውም።

12. የእግዚአብሔር ነቢያት በዚህ ጊዜ ለእስራኤል የተናገሩት ምን ነበር? ንስሐ እንዲገቡ፥ ጣዖቶቻቸውን እንዲያጠፉና በእግዚአብሔር ብቻ እንዲታመኑ ይነግሯቸው ነበር።

13. ንስሐ ካልገቡ እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርጋቸው ተናገረ? ለአሦራውያን እስራኤልን እንዲወርሩና ባቢሎናውያን ደግሞ ኢየሩሳሌምን እንዲያጠፉ እንደሚፈቅድላቸው ተናገረ።

14. እግዚአብሔር ተለውጦአልን? በፍጹም። እግዚአብሔር አሁንም ያው ነው። ብቻውን እውነተኛና ሕያው አምላክ ከሆነው ከእርሱ ሌላ ማናቸውንም ነገሮች ወይም ማንኛውንም ፍጡር የሚያመልኩትን ሁሉ ይቀጣል።

## ትምህርት 41

የትምህርት ክፍል:- መዝሙር [16]:10፤ [22]:6-8፥ 16፥ 18፤ [27]:12፤ [41]:9፤ [68]፥ 18፤ [69]:4፤ ኢሳይያስ 7:14፤ 9:7፤ 11:2፤ 50:6፤ 53:3-5፥ 7፥ 9፥ 12፤ ሆሴዕ 11:1፤ ሚክያስ 5:2፤ ዘካርያስ 11:12፥ 13፤ ኤርምያስ 6:13፥ 14

አጠቃላይ ርእስ:- ስለሚመጣው ነፃ አውጪ እግዚአብሔር የገባቸው የተስፋ ቃሎች።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ዋና አሳቦች:-

ሀ. እግዚአብሔር ነፃ አውጪ እንደሚልክ የገባውን የተስፋ ቃል አልዘነጋም።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ለ. ስለሚመጣው አዳኝ የተነገሩ ትንቢቶች።

. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው

ሐ. እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር፥ ለነቢያቱና ለመልእክቶቻቸው የነበራቸው ዝንባሌ።

. ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ለማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው።

. ሰይጣን፥ እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው። ሰውን ይጠላል።

- ሰው፥ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

የትምህርት 40 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

### ሀ. እግዚአብሔር ነፃ አውጪ እንደሚልክ የገባውን የተስፋ ቃል አልዘነጋም።

ዋና ሀሳብ:- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ስለ ነፃ አውጪው የገባውን የተስፋ ቃል በዔደን ገነት ከሰጠ በሺህ የሚቆጠሩ ዓመታት ያለፉ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ሰይጣንን የሚደመስሰውንና ሰውን ነፃ በማውጣት እንደገና የእግዚአብሔር ወዳጅ የሚያደርገውን ይህን ነፃ አውጪ ለመላክ የገባውን ቃል ኪዳን አልዘነጋም። እግዚአብሔር ይህንኑ የተስፋ ቃል ኪዳን ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ በድጋሚ ሰጥቷል። ነፃ አውጪው የሚመጣው ከእነርሱ ዘር እንደሆነ ቃል ገብቶላቸው ነበር። እግዚአብሔር ለዓመታት ሁሉ ስለ ነፃ አውጪው የሰጠውን የተስፋ ቃል በተደጋጋሚ ለእስራኤል ያስታውሳቸው ነበር። እግዚአብሔር፥ ለዳዊት የሚመጣው ነፃ አውጪ ከእርሱ ቤተሰብ (የዘር ግንድ) እንደሚሆን ቃል ገብቶለት ነበር።

ዋና ሀሳብ:- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝና ሁሉን አዋቂ ነው። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

ታላቁ ነፃ አውጪ ከመምጣቱ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ስለ እርሱ በርካታ ነገሮችን ተናግሮ ነበር። ነፃ አውጪው ምን እንደሚደርስበት እግዚአብሔር ለመረጣቸው መልእክተኞች ለነቢያት ነግሮአቸው ነበር። እነዚህን ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገኙት መጻሕፍቶቻቸው ላይ ጽፈዋቸዋል።

እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ከመፈጸሙ በፊት አስቀድሞ ያውቃል።

ዋና ሀሳብ:- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

ምንም እንኳ አብዛኛው ሕዝብ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን በጐ ፈቃድና የገባላቸውን የተስፋ ቃል ቢዘነጉትም፥ እግዚአብሔር ግን ነፃ አውጪውን ለመላክ የገባውን ቃል ኪዳን አልተወውም። እግዚአብሔር፥ ዓለምን ስለሚወድ ማንም ሰው ወደ ዘላለም ቅጣት እንዲሄድ አይፈልግም።

አሁን፥ እግዚአብሔር ስለሚመጣው አዳኝ ለነቢያት የተናገራቸውን ነገሮች እንመለከታለን።

መምህር ሆይ:-

ሀ. በተለይ ለዚህ ትምህርት ባዘጋጀኸውና ስለ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ስለተነገሩት ትንቢቶች በሚያሳየው ሰንጠረዥ ተጠቀም። የዚህን ሰንጠረዥ አጠቃቀም ዝርዝር መመሪያ በዚሁ መጽሐፍ ምዕራፍ 2 ላይ ሥዕላዊ የመረጃ መግሪያዎች አዘገጃጀት በሚለው ክፍል ውስጥ ታገኘዋለህ።

ለ. እያንዳንዱን ትንቢት እያነበብክ በአጭሩ ግለጸው። እነዚህን የብሉይ ኪዳን ክፍሎች በአዲስ ኪዳን ጥቅሶች አትተርጉማቸው፥ ወይም በአዲስ ኪዳን የተፈጸሙበትን ሁኔታ አትግለጽ። ለምሳሌ:- የመዝሙር [22]፡16 «እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ» የሚለው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ አዳኙ በመስቀል መሞት እንዳለበት አትናገር። እነዚህ ትንቢቶች በሙሉ ግልጽ የሚሆኑት በክርስቶስ ሕይወት ስለመፈጸማቸው በምትገልጥበት ጊዜ ይሆናል። እነዚህ ትንቢቶች እንዴት እንደተፈጸሙ በቀላሉ ለማስረዳት የሚያግዙህ ጥቂት ምሳሌዎች በመቀጠል ቀርበዋል።

## ለ. ስለሚመጣው አዳኝ የተነገሩ ትንቢቶች።

ኢሳይያስ 9፡7 አንብብ። ከእግዚአብሔር መልእክተኞች አንዱ የነበረው ኢሳይያስ ነፃ አውጪው በቀደምት አባቱ በዳዊት ስፍራ ንጉሥ እንደሚሆን ተንብዮ ነበር። ይህ እግዚአብሔር ለዳዊት በሕይወቱ ሳለ ቃል የገባለት ነው።

ኢሳይያስ፥ በትንቢቱ ነፃ አውጪው ሰብአዊ አባት እንደማይኖረውና እናቱም ድንግል ሴት እንደምትሆን ተናግሯል።

ኢሳይያስ 7፡14 አንብብ። እግዚአብሔር፥ በዔደን ገነት ለሰይጣን በተናገረ ጊዜ ያለው ይህንኑ ነበር። እግዚአብሔር፥ ሰይጣንን የሚደመስሰው «የሴቲቱ ዘር» ነው በማለት ተናግሮ ነበር።

ሌላው የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሚክያስ፥ ነፃ አውጪው በቤተልሔም ከተማ እንደሚወለድ ተናግሯል። ሚክያስ 5፡2 አንብብ።

መምህር ሆይ፡-

ሀ. በካርታ ላይ ቤተልሔምን አሳይ፥ ደግሞም የቤተልሔምን ሥዕል (ፎቶ ግራፍ) አሳያቸው። በቅድመ የወንጌል ሥርጭት ትምህርት ይህን አሳይተሃቸው ከሆነ ይህንን ሥዕል ከዚህ ቀደም እንዳዩት አስታውሳቸው። ይህ ትምህርቱን ከጀመርክበት ጊዜ አንስቶ ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚገባ ለመከታተል እያዘጋጀሃቸው እንደነበር ለመገንዘብ ያስችላቸዋል።

ለ. ቀጥሎ በሰንጠረዥህ በግራ በኩል መስፈር የሚገባቸው ትንቢቶች ተዘርዝረዋል። የመጀመሪያዎቹን ሦስቱን ቀደም ብለን ስለገለጥናቸው አሁን ከሆሴዕ 11፡1 ጀምረህ ትቀጥላለህ።

## እግዚአብሔር በነፃ አውጪው ላይ እንደሚደርሱ የተናገራቸው ነገሮች

| | |
|---|---|
| ኢሳይያስ 9፡7 | ከዳዊት ዘር ይሆናል |
| ኢሳይያስ 7፡14 | ከድንግል ይወለዳል |
| ሚክያስ 5፡2 | በቤተልሔም ይወለዳል |
| ሆሴዕ 11፡1 | ወደ ግብፅ ይሸሻል |
| ኢሳይያስ 11፡2 | ከባሕርያቱ ጥቂቶቹ ተጠቀሰዋል |
| ኢሳይያስ 53፡4፥ 5 | ስለ ሌሎች መከራን ይቀበላል |
| መዝሙር (41)፡9 | ከወዳጆቹ አንዱ ይከዳዋል |

| | |
|---|---|
| ዘካርያስ 11፡12፥ 13 | በሰላሳ ብር ይሸጣል |
| መዝሙር (27)፡12 | ሐሰተኛ ምስክሮች ይመሰክሩበታል |
| ኢሳይያስ 50፡6 | ይተፋበታል፥ በጥፊም ይመቱታል |
| ኢሳይያስ 53፡7 | በከሳሾቹ ፊት ዝም ይላል |
| ኢሳይያስ 53፡3 | አይሁዶች አይቀበሉትም |
| መዝሙር (69)፡4 | ያለምክንያት በሰው ይጠላል |
| መዝሙር (22)፡16 | እጆቹና እግሮቹ ይቸነከራሉ |
| መዝሙር (22)፡18 | ልብሶቹን ይከፋፈሉታል |
| ኢሳይያስ 53፡12 | ከክፉዎች ጋር ይሞታል |
| መዝሙር (22)፡6-8 | ማላገጫና የተናቀ ይሆናል |
| ኢሳይያስ 53፡9 | መቃብሩ ከሃብታሞች ጋር ይሆናል |
| መዝሙር (16)፡10 | ከሞት ይነሣል |
| መዝሙር (68)፡18 | ወደ ሰማይ ያርጋል |

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ሉዓላዊ ነው።

እግዚአብሔር፥ በነፃ አውጪው አዳኝ ላይ እንደሚደርሱ ከተናገራቸው ነገሮች ጥቂቶቹ እነዚህ ናቸው። እግዚአብሔር ነፃ አውጪው አዳኝ ወደዚህች ምድር ከመምጣቱ በፊት እንኳ ምን እንደሚደርስበት አስቀድሞ ዐቅዷል።

## ሐ. እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር፥ ለነቢያቱና ለመልእክቱ የነበራቸው ዝንባሌ።

ዋና አሳብ፡- ሰው ኃጢአተኛ ነው። ራሱን ማዳን ስለማይችል እግዚአብሔር ያስፈልገዋል።

ከዚህ ቀደም ብሎ ባለው ትምህርታችን ውስጥ የእግዚአብሔር ነቢያት ሕዝቡ ንስሐ እንዲገባ፥ ጣዖታትን እንዲያጠፉና ብቸኛውን አምላክ እንዲያመልክ ይነግሩት እንደነበር ተመልክተናል። ይህን

ካልታዘዙ ጠላቶቻቸው እንዲያሸንፏቸውና ባሪያ አድርገው ወደሩቅ ስፍራዎች እንዲወስዷቸው እንደሚፈቅድ እግዚአብሔር ነግሮአቸው ነበር።

አብዛኛው የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ቃል ለመታዘዝ ሳይፈቅዱ ቀሩ። የእግዚአብሔርን መልእክተኞች አሳደዱ፥ ገደሏቸውም። ጣዖታትን ማምለካቸውን ቀጠሉ። የአካባቢያቸው አሕዛብ የሚከተሉአቸውን ክፉ መንገዶች ተከተሉ። የተቀሩት ደግሞ ወደ ቤተ መቅደስ በመሄድ ጌታን ማምለካቸውን፥ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን በሙሉ መፈጸማቸውን፥ መሥዋዕታትን ማቅረባቸውን የቀጠሉ ቢሆንም የእግዚአብሔርን ሕግ ግን አልታዘዙም ነበር። ስለ እግዚአብሔር ብዙ መልካም ነገሮችን የሚናገሩ ቢሆንም፥ የሚናገሩት ግን ከልባቸው ስላልነበረ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አላገኙም።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ሁሉን አዋቂ ነው።

እግዚአብሔርን ልናሞኘው አንችልም። ሰው ውጪአችንን ያያል፥ ቃሎቻችንን ብቻ ይሰማል። እግዚአብሔር ግን አሳባችንና ልባችንን ይመለከታል። በውስጣችን በእርግጥ ምን እንደምንመስል ያውቃል። ሁላችንም ኃጢአተኞች እንደሆንን ይናገረናል። ማንኛችንም ብንሆን በምናደርገው ነገር እግዚአብሔርን ደስ ልናሰኝ አንችልም።

አብዛኛዎቹ ካህናትና መሪዎች ክፉ ሰዎች ነበሩ። በእግዚአብሔር የማይታመኑና ትእዛዛቱን የማይጠብቁ ነበሩ።

ዋና አሳብ፡- ሰይጣን ከእግዚአብሔርና ከፈቃዱ ጋር ይዋጋል። እርሱ ውሸታምና አታላይ ነው። ሰዎችን ይጠላል።

ለእስራኤል ሕዝብ የሚናገሩ ሐሰተኛ ነቢያትም ነበሩ። የእግዚአብሔር መልእክተኞች እንደሆኑ ቢናገሩም እንኳ የሰይጣን አገልጋይ ነበሩ። ለሕዝቡ ውሸትን ይናገሩ ነበር። ሁሉም ነገር መልካም እንደሆነና እግዚአብሔር እንደማይቀጣቸው ይናገሩ ነበር። ኤርምያስ 6፡13፥ 14 አንብብ።

ሰይጣን ዛሬም ቢሆን ያው ነው። ሰይጣን በሰዎች በኩል የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንዳልሆነ ወይም እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደማይቀጣ አድርጐ ይነግራችሁ ይሆናል። የእግዚአብሔርን ቃል እንዳትሰሙና የቀደምት አባቶቻችሁን መንገድ መከተል እንድትቀጥሉ ይነግራችሁ ይሆናል። እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ወይም የሰዎችን ቃል ለማመን ምርጫ ማድረግ አለበት።

ዋና አሳብ:- ሰው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

በእስራኤል ውስጥ እግዚአብሔር በመልእክተኞቹ አማካይነት የሰጠውን ቃሉን የሚያምኑ ሰዎች ሁልጊዜ ጥቂት ነበሩ። እነርሱም በእግዚአብሔር ይታመኑበትና ትእዛዛቱንም ለመከተል ይጥሩ ነበር። በእርሱ ላይ በነበራቸው እምነት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አግኝተው ነበር። እንደ አቤል፥ ኖኅ፥ አብርሃምና ሌሎች ብዙዎች ኃጢአተኞች መሆናቸውን በማመን ለምሕረቱና ለይቅርታው በእርሱ በመታመናቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ ነበሩ። እግዚአብሔር ከሰይጣንና ከኃጢአታቸው ቅጣት እንደሚያድናቸው ተስፋ የገባላቸውን አዳኝ መምጣት ይጠባበቁ ነበር።

እናንተስ የትኞቹን ነው የምትመስሉት? እግዚአብሔርን ለማመን ፈቃደኛ ያልሆኑትን እስራኤላውያንን ወይስ ቃሉን አምነው በእርሱ የተደገፉትን?

መምህር ሆይ:- ዘካርያስ ከተናገረው በግልጽ የምንረዳው በዚያን ጊዜ የነበሩ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን የሚመጣውን አዳኝ የተቤዠነት ዓላማ በግልጽ የተረዱ ሰዎች እንደነበሩ ነው።(ሉቃስ 1፡76-79።)

## ጥያቄዎች

1. በሺህ የሚቆጠሩ ዓመታት ያለፉ ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር ነፃ አውጪ እንደሚልክ የገባውን የተስፋ ቃል ዘነጋን? በፍጹም! እግዚአብሔር አልዘነጋም ነበር።

2. ስለሚመጣው አዳኝ እግዚአብሔር የላቀ መረጃ የሰጠው ለማን ነበር? ለነቢያቱ ነበር።

3. እነዚህ መረጃዎች የሚገኙት የት ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው።

4. አብዛኛዎቹ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔርና ለነቢያቱ የነበራቸው ዝንባሌ ምን ነበር?

   ሀ. የእግዚአብሔርን ነቢያት አሳደዱ፥ ገደሉአቸውም።

   ለ. ጣዖታትን ማምለካቸውን ቀጠሉ።

   ሐ. በዙሪያቸው የነበሩ አሕዛብን ክፉ መንገዶች ተከተሉ።

5. እስራኤላውያን ወደ ቤተ መቅደስ በመሄድ፥ መሥዋዕት ማቅረባቸውንና እግዚአብሔርን ማምለካቸውን ቀጠሉን? አዎን፥ ቀጥለው ነበር።

6. እግዚአብሔር ደስ ተሰኘባቸውን? እግዚአብሔር አምልኮአቸውንና መሥዋዕታቸውን ተቀበለን? በጭራሽ አልተቀበለም።

7. እግዚአብሔር፥ የአብዛኛዎቹን እስራኤላውያንን አምልኮና መሥዋዕት ያልተቀበለው ለምን ነበር? እግዚአብሔርን በከንፈራቸው እያመለኩ በልባቸው ክደውት ስለነበር ነው። ንስሐ አልገቡም ነበር፤ በእግዚአብሔርም አልታመኑም ነበር።

8. አሳባችንን የሚመለከትና ልባችንን የሚያውቅ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው።

9. እግዚአብሔር፥ ስለ ሁላችን ምን ይላል? ሁላችንም ኃጢአተኞች እንደሆንን እግዚአብሔርንም ደስ እንዳላሰኘን ይናገራል።

10. እግዚአብሔር፥ የተቀበላቸው እስራኤላውያን ነበሩን? አዎን። ኃጢአተኞች መሆናቸውን በማመን ለምሕረቱና ለይቅርታው በእርሱ የታመኑትን ሁሉ እግዚአብሔር ተቀብሏል።

11. እነዚህ አማኝ እስራኤላውያን የሚጠብቁት ማንን ነበር? እግዚአብሔር፥ ከሰይጣንና ከኃጢአቶቻቸው ቅጣት እንደሚያድናቸው ተስፋ የገባላቸውን ነፃ አውጪውን አዳኝ ይጠብቁ ነበር።

## ትምህርት 42

የትምህርት ክፍል፡- 2ኛ ነገሥት 17፡1-8፤ 25፡1-12

አጠቃላይ ርእስ፡- እግዚአብሔር፥ እስራኤልንና ይሁዳን ቀጣ፥ ነገር ግን ቅሬታዎችን ከባቢሎን ታደገ።

የትምህርቱ አስተዋጽኦና የመሠረታዊ እምነት ትምህርት አሳቦች፡-

ሀ. የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤልና በይሁዳ ላይ (17፡1-8፤ 25፡1-12)።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ለ. የምርኮኞች ከባቢሎን መመለስ።

. እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

. እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ሐ. ግሪኮችና ሮማውያን።

መ. ጸሐፍት፥ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን።

ሀ. ጸሐፍት

ለ. ፈሪሳውያን

ሐ. ሰዱቃውያን

ሠ. የሕግ ትምህርት ማስተማሪያ ይሆን ዘንድ ምኩራቦች ተገነቡ።

ሰ. እግዚአብሔርን የሚፈሩ አይሁዳውያን አማኞች።

. ሰው፥ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና ለመዳን እምነት ያስፈልገዋል።

. ሰው፥ ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ብቻ ነው።

የትምህርት 41 ጥያቄዎችን ከልስ።

## የትምህርቱን አስተዋጽኦ ደረጃ በደረጃ ማቅረብ

### ሀ. የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤልና በይሁዳ ላይ

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው።

እግዚአብሔር ታጋሽ ነው። ኃጢአተኞችን፥ ወዲያውኑ አይቀጣቸውም። በኖኅ ዘመን የነበሩትን ሰዎች የጥፋት ውኃ ሳያጠፋቸው በፊት ለ120 ዓመታት እግዚአብሔር ሲያስጠነቅቃቸው ነበር። ለብዙ መቶ ዓመታት ለእስራኤላውያን መልእክተኞችን ልኳል። መልእክተኞቹም ንስሐ ካልገቡ የእግዚአብሔር ቁጣና ቅጣት እንደሚመጣባቸው በመናገር በሚገባ አስጠንቅቀዋቸዋል።

ዋና አሳብ:- እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

እስራኤላውያን፥ ጠላቶቻቸው ወደ ምድራቸው መጥተው በምርኮ እንዲወስዷቸው እግዚአብሔር ይፈቅዳል ብለው አላመኑም ነበር። ነገር ግን እስራኤላውያን ስላላመኑና ንስሐ ስላልገቡ ጠላቶቻቸው መጥተው እንዲወጉአቸውና እንዲያሸንፏቸው እግዚአብሔር ፈቀደ። አሦራውያን አሥሩን የሰሜኑን ነገዶች አሸንፈው በምርኮ ወሰዷቸው። 2ኛ ነገሥት 17፡ 1-8 አንብብ።

የዮናስን ታሪክ ታስታውሳላችሁን? አሦራውያን ዮናስ በእግዚአብሔር ተልኮ የሰበከላቸው ሕዝቦች ነበሩ። ዮናስ ወደ ነነዌ ከተማ በሄደና በሰበከላቸው ጊዜ ሕዝቡ ንስሐ ገብተው ነበር፥ ነገር ግን ወዲያውኑ የእስራኤልን አምላክ ከመከተል ወደኋላ ተመለሱ። በመጨረሻ አሦራውያን፥ ወደ ሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት በመምጣትና ሕዝቡን በመውጋት አብዛኛውን ሕዝብ ወደ አሦር ማርከው ወሰዱ። አሦራውያን ሌሎች ሕዝቦችን ከአገራቸው ወደ ሰሜኑ የእስራኤል ክፍል በማምጣት በዚያ እንዲኖሩ አደረጉ። እነዚህ ሕዝቦች ጣዖት አምላኪዎች ነበሩ። እውነተኛና ሕያው የሆነውን የእስራኤል አምላክ አያምኑም ነበር።

ከአሥሩ የእስራኤል ነገድ የተረፉትና ወደ አሦር ያልተወሰዱት አብዛኛዎቹ ሰዎች ከሌሎች አገሮች ከመጡት ከእነዚህ ሕዝቦች ጋር ጋብቻን መሠረቱ። የዚህ ድብልቅ ጋብቻ ውጤት የሆኑት ሰዎች

ዝርያዎች ሳምራዊያን በመባል ተጠሩ። ሳምራዊያን፥ እግዚአብሔርን ማምለካቸውን የቀጠሉ ቢሆንም አምልኮታቸው ግን እግዚአብሔር ለሙሴ በነገረው መንገድ ሳይሆን በራሳቸው መንገድ ነበር። እግዚአብሔርን ለማምለክ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ወደሚገኝበት ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፈቃደኛ ስላልነበሩ እግዚአብሔር አምልኮአቸውን አይቀበልም ነበር።

መመህር ሆይ፡- ዮሐንስ 4፡20-22 አንብብ።

እንደ ሰሜኑ ነገዶች ሁሉ ሁለቱ የደቡብ የእስራኤል ነገዶችና የኢየሩሳሌም ሕዝቦች ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። ስለዚህ ባቢሎናውያን መጥተው ወደ አገራቸው በምርኮ እንዲወስዷቸው እግዚአብሔር ፈቀደ። ባቢሎናውያን የኢየሩሳሌምን ቅጥር አፈረሱ፥ ንጉሥ ሰሎሞን የሠራውን ቤተ መቅደስ በማፍረስ አቃጠሉት። 2ኛ ነገሥት 25፡1-12 አንብብ።

እግዚአብሔር፥ እስራኤላውያን ንስሐ ካልገቡ እንደሚያመጣባቸው የተናገረውን ምርኮ አደረሰባቸው። ሕዝቡ ቃሉን ስላላመኑ ቀጣቸው።

እግዚአብሔር ሁልጊዜ ሊያምኑት ፈቃደኞች ያልሆኑትን ይቀጣል። የማያምኑት ሰዎች በሙሉ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው የቅጣት ስፍራ ይሄዳሉ። ከእግዚአብሔር ሊያመልጥ የሚችል ማንም የለም።

## ለ. የምርኮኞች ከባቢሎን መመለስ።

ዋና አሳብ፡- እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ምሕረትንና ጸጋን የተሞላ ነው። እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ ነው።

ከብዙ ዓመታት በኋላ፥ በባቢሎን ይኖሩ የነበሩ የይሁዳ ሕዝብ ንስሐ በመግባት እግዚአብሔር ወደ ምድራቸው እንዲመልሳቸው ጠየቁት። ለእርዳታ ያሰሙትን ጩኸት እግዚአብሔር ሰማና አብዛኛዎቹን ወደ ኢየሩሳሌም መለሳቸው። ኢየሩሳሌምንና የከተማዪቱን ቅጥር እንደገና ገነቡ። ቤተ መቅደሱንም ሠሩ።

ወደ ምድራቸው የተመለሱት እስራኤላውያን አይሁድ የሚል ሌላ ስም ተሰጣቸው። እስራኤላውያን እስከ ዛሬ ድረስ አይሁድ በመባል ይጠራሉ።

መምህር ሆይ:- አይሁድ የሚለው ስም የተገኘው ምናልባት ይሁዳ ከሚለው ቃል ይሆናል።

አብዛኛዎቹ አይሁዳውያን ከልባቸው ባይሆንም እንኳ እግዚአብሔርን ማምለካቸውን ቀጠሉ። ከመሥዋዕቶቻቸው ጋር ወደ ቤተ መቅደስ የሚሄዱ ቢሆንም ኃጢአተኞች እንደሆኑና የእግዚአብሔር ምሕረት እንደሚያስፈልጋቸው አያምኑም ነበር።

## ሐ. ግሪኮችና ሮማውያን

ስለዚህ እግዚአብሔር፥ አሁንም እንደገና ሌሎች ሕዝቦች እንዲወጉአቸው በመፍቀድ ቀጣቸው። ግሪኮች የአይሁድን ምድር ተቆጣጠሩና አይሁዳውያንን የግሪክ ቋንቋ እንዲማሩ አደረጓቸው።

መምህር ሆይ:- በካርታ ላይ ግሪክን አሳያቸው።

ከጊዜ በኋላ፥ ሮማውያን ግሪኮችን አሸነፉና ኢየሩሳሌምንና የአይሁድን ምድር ወረሩ።

መምህር ሆይ:- ሮምን በካርታ ላይ አሳያቸው።

ሮማውያን፥ አይሁዶች እንዲገዙላቸውና ግብር እንዲከፍሉ አደረጉ። የማይታዘዙ በሚሆኑበት ጊዜ ይቀጧቸው ነበር። ብዙ አይሁዶችን በጦርና በሰይፍ ይገድሉ ነበር። ሌሎቹንም አይሁዶች ይሰቅሉአቸው ነበር።

መምህር ሆይ:- ጦር፥ ሰይፍ፥ መስቀል የሚሉትን ቃሎች አብራራቸው።

የሮማውያን ንጉሥ የሚኖረው በሮም ከተማ ነበር። መጠሪያ ማዕረጉም ቄሣር ነበር። ቄሣር ያሸነፋቸውንና የተቆጣጠራቸውን ከተሞች የሚያስተዳድሩለት ሰዎች ይሾም ነበር።

ሮማውያን በርካታ ጣዖታትን ያመልኩ ነበር። ንጉሣቸውን፥ ቄሣርንም እንደ አምላክ ቆጥረው ያመልኩት ነበር። ሆኖም ለአይሁዳውያንም ወደ ቤተ መቅደስ በመሄድ እግዚአብሔርን ማምለካቸውን እንዲቀጥሉ ፈቅደውላቸው ነበር።

## መ. ጸሐፍት፥ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን

1. ጸሐፍት።